# ቁጥር ፬ - ነጸብራቅ

## በእርጋታ የተሞሉ ጭዉዉቶች





**ቅንብር**
ኦርዲነሪ ዛክ
አናኒያ ቲ.

**ገፀ ሽፋን**
ናይሳ ፓሪንቶን

**ታሪክ ገላጮች**
ሮቢን ኢዮዓብ
ቦኒቸ ቦና

አዘጋጅ: የዲ ሚድያና ህትመት

## ቀደም ሲል የታተሙ ስራዎች:

ኖር ቁጥር ፫ - ወዳጅነት፦
በጓደኛነት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ታሪኮች (2017)

ኖር ቁጥር ፪ - ሰንኖር፦
ሆን ተብለው የተዘነጉ ማንነቶች
(2016)

ኖር ቁጥር ፩፦
የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ፌሽታ
(2015)

# መታሰቢያነቱ

በዝምታ ውስጥ ድምፅ ለሆናችሁ፣ በጨለማ ውስጥ የታሪካችሁን ላምባ ለለኮሳቹ፤ ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ ‘ነበርን፣ አለን፣ እንኖራለን’ ለምትሉ የነገው ትውልድ ጀግኖች ይሁን!

YEDI

# መቅድም

ኖርን ለማዘጋጀት ስናጥን፤ “ከእኛ በፊት ምንም አልተሰራም፣ ሁሉንም ከዜሮ እንጀምር” የሚል የተሳሳተ እሳቤ አልነበረንም። ይልቁንም አካሄዳችን፤ ቀደምት አሻራዎችን ከአዳዲስ ድምፆች፣ የከተማን ሕይወት ከገጠር ገጠመኞች ጋር በማጣመር፣ አሮጌውን እውነት በአዳዲስ እጆች መከተብ ነበር። ኖር የተጸነሰችዉ እኛ ከደረስንበትና ከተቋደስነው ማዕድ ለሌሎችም እናካፍል ከሚል የታሪክ አደራ እና የኃላፊነት ስሜት ነው።

ኖር የጥቂት ቀናት የሆይሆይታ ወይም የጊዜያዊ ስሜት ውጤት አይደለችም። ስም ሳይወጣላት ለዓመታት በጓደኞች ወግ መሃል ስትብላላ፣ በሐሳብ ፍጭት ስትገራ የቆየች የረጅም ጊዜ ሕልም እንጂ። ዛሬ ጊዜና አጋጣሚ ተሳክቶላት በታሪኮች ተቀናጅታ ለአንባብያን ብትቀርብም፤ በአእምሮአችን ውስጥ ግን ከኖረች ሰነባብታለች።

ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ስም ያልሰጠናትን የታሪክ መድብል ለመጀመሪያ ጊዜ ስናቅድ፤ እቅዳችን አንድና ግልጽ ነበር፦ ምንም መከራ ቢመጣ የማይቋረጥ፣ ቢያንስ አራት እትሞችንና መቶ ታሪኮችን ለትውልድ መዝግቦ የሚያስቀምጥ የነጻነት ሰነድ ማዘጋጀት። የኖር ዓላማ የተኖረን የዜጋ ሕይወት ሳይበረዝ፣ ሳይደለዝ እና ሳይሰረዝ እንደወረደ መከተብና ለትውልድ ማስተላለፍ ነው!

ለምን ቢሉ? በየትኛውም አጋጣሚ ስለ እኛ ሲወራ “ወፍ ዘራሽ” እንደሆንን፣ ኢትዮጵያዊነት ውስጥ ቦታ እንደሌለን ስለሚነገረን ነው። ለዚህ ማረጋገጫ ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ “በጥንት የኢትዮጵያ ሥነ-ጥበብ ውስጥ ስለ እናንተ መኖር የተጻፈ ነገር የለም” የሚለው የተሳሳተ ድምዳሜ ነው። እውነታው ግን ሌላ ነው። አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም ሆነ እንጂ፤ ገና በ1952 የታደሰ ሊበን “ሌላው መንገድ”፣ በ1963 የኃይለሥላሴ ደስታ “የሚያቃጥል ፍቅር” እንዲሁም በጋሽ ሰብሃት ገብረእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች ውስጥ ስለ እኛ ሕይወት በጥቂቱም ቢሆን ለመግለጽ የደፈሩ ብዕሮች ነበሩ።

ታዲያ የዛሬው የመረጃ ዘመን ላይ ሆነን “አለን” ስንል “የላችሁም” የምንባል ከሆነ፣ በዚያ ዘመን ታሪኮቻችን መድረክ ማጣታቸው ምን ይደንቃል? የኖር ትልቁ ኃላፊነት ይሄው ነው፦ የትናንቱን ከአሁኑ እያያዘ “ነበርን፣ አለን፣ እንኖራለን!” የሚለውን እውነት ለነገው ትውልድ ማሳደር። ዛሬ፣ ነገ ወይም ከ20 ዓመት በኋላ፤ ማንነቱን ለመቀበል የታገለ አንድ ሰው ድረ-ገጻችን ላይ ጎራ ቢል፣ እሱን የሚመስሉ ከመቶ በላይ ሰዎችን እውነተኛ ታሪክ አግኝቶ መፅናኛና መመሪያ ቢሆነው፤ ያ ለእኛ ትልቅ ስኬት ነው።

እነሆ ዛሬ ያ እቅድ ፍሬ አፍርቶ፣ “ነጸብራቅ” የመጀመሪያው ጥራዝ መዝገያ ሆና በእጃችሁ ትደርሳለች። ነጸብራቅ ወደ ኋላ መለስ ብለን ያለፍንባቸውን ፅንሰ-ሃሳቦች በረቀቀ መንገድ የምናስላስልባት ብቻ ሳትሆን፤ ያለፉትን እትሞች ትርጉም ባለው መልኩ የመረመርንባት፣ የአዘጋጆቹን ፈታኝና ጣፋጭ ተሞክሮዎች ያካፈልንባት፣ እንዲሁም የወደፊቱን ጉዟችንን የዳሰስንባት ልዩ እትም ነች።

በዚህ እትም በኢትዮጵያ የኲዊር ንቅናቄ (Movement) ውስጥ አሻራቸውን ያሳረፉ እንግዶችን ጋብዘናል፦ የ’አለን ሾው’ ዋና አዘጋጅ ሮቤል ሃይሉ እና የ Zega Matters መስራች እንዲሁም የ’ዜጋ ማህበር’ አንዱ መስራች Happy Addis ካከበሩን እንግዶቻችን መካከል ናቸው። በተጨማሪም ስለ ሌዝብያን የፍቅር ግንኙነት ጥልቅ መረዳት እንዲኖረን ሁለት ፍቅረኛሞችን አውርተናል።

እኛ በጥንቃቄ እና በፍቅር የሰራነውን ይህን እትም እናንተም እንደምትወዱት ሙሉ እምነት አለን።

መልካም ንባብ!

# ማውጫ


መታሰቢያነቱ - - - - - - - - - - vi
መቅድም - - - - - - - - - - - viii
ቆይታ ከ Happy Addis ጋር - - - - - - - 2
ስለ ሌዝብያን ፍቅር ጥልቅ እይታ ከጆይ እና ሃኒ ቢ ጋር - - - 20
The Weight of a Moment - - - - - - - 36
የልብ ለልብ ወግ፦ ከሮቤል ሃይሉ ጋር - - - - - - 46
Reflections on love and relationship - - - - 72
N’or: Design Process - - - - - - - - 104
Afterword - - - - - - - - - - 112
ምስጋና - - - - - - - - - - - 117



# ቆይታ ከ Happy Addis ጋር

ኖር፦ እንኳን ደህና መጣህ!

ሃፒ፦ እንኳን ደህና ቆያችሁኝ!

ኖር፦ በዚህ ኢንተርቪው መዳሰስ የፈለግነው ኦንላይን እና ኦፍላይን እክቲቪዝም ምን እንደሚመስል ነው። መጀመሪያ አከባቢ በኩዊር ሰዎች መሃል የነበረው የኦንላይን መስተጋብር እንዴት እንደነበር፣ የኩዊር ሰዎች የኦንላይን ገፅታ ምን ይመስል እንደነበር እንዲሁም አሁን ያለውን ሁኔታ በተመለከት ውይይት ለማድረግ እና ስላንተም ልምድ ለማውራት ነው።

ቀለል ብሎን እንድንጀምር አራት ቃላት እንነግርሃለን ከዛ አንተ ቃላቱን ስትሰማቸው ቀድመው ወደ እእምሮህ የመጡትን ነገሮች ትነግረናለህ። እንቀጥል?

ሃፒ፦ እሺ

ኖር፦ ፌስቡክ

ሃፒ፦ ኦው! ፌስቡክ ስልኬ ነው ትዝ ያለኝ

ኖር፦ ፕራይድ

ሃፒ፦ ፍርሃት! ለመጀመሪያ ግዜ ፕራይድ ላይ ስሳተፍ ፈርቼ ነበር።

ኖር፦ ኢትዮጵያ

ሃፒ፦ Really? ይሄ ነው መልሴ

ኖር፦ ኖር

ሃፒ፦ ከሽሩ ነው የመጣልኝ ሰዎች ተቀምጠው ያለው ቢጫ ከሽር ነው ትዝ ያለኝ

ኖር፦ ይሄን ያህል ፈታ ካልን ይበቃል በቀጥታ ወደ ዋናዉ ጥራቄያችን እናምራ። ራስህን እክቲቪስት ነኝ ብለህ ታስባለህ?

ሃፒ፦ አንዳንድ ሰዎች እንደዛ ነህ ብለው ያስቡኛል። እኔ ግን መጀመሪያ የዜጋ ጉዳዮች ላይ መንቀሳቀስ ስጀምር አክቲቪስት ልሁን ብዬ አልነበረም የመጣሁት። ራሴን ለማወቅ፣ ማንነቴን ለመረዳት

የመጣሁበት ግዜ ነበር። በሂደት ሰዎች አክቲቪዝም ሊሉት የሚችሉት ደረጃ ላይ ደረስኩ። አሁን ላይ ሁሉም ሰው አክቲቪስት ነኝ የሚልበት ግዜ ላይ ስለሆንን እኔ ራሴን አክቲቪስት ነኝ ብዬ አልጠራም። የበለጠ ይገልፀኛል ብዬ የማስበው በፌስቡክም ይሁን በአካልም ሳደርገው የነበረው ነገር ኦርጋናይዘር ወይም ሰብሳቢ የሚለው ይገልፀኛል። እዚህም ባለሁበት ኩዊር ኮሚኒቲ ማደርገው ሰዎችን ማሰባሰብ፣ ሰዎችን ማገናኘት ነው።

ኖር፦ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁለተኛ ጥያቄዬ ራስህን ኢንፍሉዌንሰር ወይም ተፅዕኖ-ፈጣሪ ነኝ ብለህ ታስባለህ የሚል ነው

ሃፒ፦ ነገሮችን ኦርጋናይዝ በምታደርግበት ግዜ በዛውም በውስጡ ተፅዕኖ የመፍጠር ሂደትም አለው። አንተ ሃሳቡን ስታነሳና ስታመጣ፣ ከዛ ስታዘጋጅ የዛ አይነት መልክ መያዙ የማይቀር ነው። እኔ ያኔም ግን ተፅዕኖ ፈጣሪ ልሁን በሚል አልነበረም የማደርገው። ለምሳሌ ድሮ ፌስቡክ ላይ በነበርኩበት ግዜ መወያያ ርዕሶችን ሳስነሳ ወይም ጥያቄ ሳሰባሰብ ምናምን ይህም ተፅዕኖ የመፍጠር መንገድ ነበር። ያኔ ቃሉ ብዙ ተጠቃሚ አልነበረውም። ብዙ ሰውም በዛ መንገድ አይጠቀመውም ነበር።

በፈርንጅ አቆጣጠር ከ 2011 እስከ 2015 ባለው ግዜ ኦንላይን በጣም አክቲቭ ነበርኩ። በዛ ግዜ ተፅዕኖ እየፈጠርክ ነበር ወይ? ከሆነ አዎ ነዉ መልሴ። የፌስቡክ ግሩፖች አድሚን በመሆን ውይይቶች በማስነሳት እንቀሳቀስ ነበር። ወደ ኋላ ተመልሼ ሳስበው ለእኔ ጥሩ ነበር። ብዙ የተማርበኩበት እና ራሴን እንድረዳ ያገዘኝ ግዜ ነበር። ጥሩ ጓደኛነቶችን የመሰረትኩበት፣ ጥሩ ሰዎች እንዳገኝ ያገዘኝ ግዜ ነው። ሰዎች ላይ ተፅዕኖ አድርጌያለሁ። እኔም በሌሎች ሰዎች በመልካም መንገድ ኢንፍሉዌንስ ተደርጌያለሁ።

ኖር፦ እውነት ነው! ምንም እንኳ ብዙ ግዜ በአንድ አቅጣጫ የሚደረግ ቢመስለንም አክቲቪዝም እና ተፅዕኖ መፍጠር በተመሳሳይ ሰዓት ራሣችንንም ተፅዕኖ ስር የሚያደርግ ተግባር ነው።

ቀደም ብሎ የገለፅክልን ፌስቡክ ላይ የነበረው ማደራጀት እንዳለ ሆኖ በተለየ የምታስታውሰው ክስተት አለ? ማለትም ኦርጋናይዝ ማድረግ አለብኝ ብለህ እንድታስብ ያደረገህ

አይነት? ሰዎች ራሳቸውን መሆን ሚችሉበት፣ ራሳቸውን መግለፅ የሚችሉበት መንገድ መፍጠር አለብኝ ብለህ እንድታስብ ያደረገህ የተለየ የምታስታውሰውን፣ ምክንያት ነው የምትለው ነገር አለ ወይስ እንዲሁ ከራስህ ከውስጥህ የመጣ ነው?

ሃፒ፦ እዚህ ላይ የተወሰነ ስለራሴ ለመናገር ያህል ዜግነቴን መጠየቅ በጀመርኩበት ግዜ ስለራሴ ለማወቅ ኦንላይን ነበር የሄድኩት። በዛን ግዜ Yahoo group የሚባል ዌብሳይት ነበር ዌብሳይቱ ላይ ጌይ ኢትዮጵያንስ የሚባል ግሩፕ ነበር። እዛ ነበር ሀበሻ ለማግኘት የሄድኩት። ከዛ በፊት ኢንተርኔት ያለ ቢሆንም መረጃ ማግኘት ቀላል አልነበረም። በተለይ ስለተመሳሳይ ፆታ ብዙም መረጃ አልነበረም። ሆሞሴክሽዋሊቲ ምን እንደሆነ ቢበዛ ኢንሳይክሎፒዲያ ላይ ታነባለህ። ያኔ ጎግልም በትክክል ነበር ማለት አይቻልም። የተለያዩ ፎረም የሚባሉ ዌብሳይቶች ነበሩ እነዛ ውስጥ ገብተህ ታነባለህ።

በዚህ መሃል ሳለው ነበር ሀበሻ ደግሞ የታለ? የእኔን አይነት ጥያቄ የሚጠይቅ፣ በእኔ መንገድ ያደጉ፣ እንደኔ የመጡ የሚሉ ሃሳቦች ነበሩ። የት ይገኛሉ ብዬ ስጠይቅ ኢትዮጵያን ጌይ ግሩፕ የሚባል አገኘው። ወደ ሁለት መቶ ሰው አከባቢ ነበረው እና ሰዉ እዛ ውስጥ ገብተው ለመገናኘት “አዲስ አበባ ያለ” “ኒውዮርክ ያለ” እያሉ ይፖስታሉ። ጥያቄ ያላቸው ስለ ሃይማኖት ሊሆን ይችላል ስለ ባህል ሊሆን ይችላል ይጠይቃሉ። የመኖር ጥያቄ የሚጠይቁም ነበሩበት። ራስህን ለማግኘት ጥያቄቆች የምትጠያየቅበት፣ ሰው አግኝተህም የምትማማርበት ግሩፕ ነበር።

ከዛ በኋላ እንደማንኛውም ቴክኖሎጂ ግዜው ደርሶ አሁን Yahoo እስኪረሳ ድረስ ፌስቡክ መጣ። አብዛኛውም ሰው ወደ ፌስቡክ ዞረ። ወደ ፌስቡክ ስገባ እንደ Yahoo አልነበረም። እዋ ገፅታው ደስ ይላል ለሰው የጓደኝነት ጥያቄ መላክ ትችላህ። እስከ አሁን ድረስ በሰፋት ቆይቷል ግን አሁን ላይ እሱም እየቀዘቀዘ እንደመጣ ተመልክቻለው።

እኔ ወደ ፌስቡክ ስመጣ ብዙ ሰዎች ፌስቡክ መጠቀም ጀምረው ነበር። ነገር ግን ምንም እንቅስቃሴ አልነበረም። አንድ ለአንድ ልታወራ ትችላለህ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሊሆን ይችላል ግን የሆነ ማዕከል የነበረ ነገር አልነበረም። ከፍተኛ ክፍተት ነበር። እኔ ደግሞ እዛ የነበረውን ውይይት ፈልገዋለሁ። ሰዎችን መተዋወቅ

ፈልጋለሁ ከዛ በላይ ግን ራሴን መረዳት፣ ማወቅ እና ሰዎች እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖሩ የበለጠ መረዳት እፈልግ ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻህን ሆነህ ነገሮችን እንዴት መወጣት እንደምትችል ለመረዳት እና ራስህን በሚገባ ለማወቅ የምትችልበትን ቦታ ፈለግኩ።

እውነት ለመናገር በሰዓቱ ግሩፖች ነበሩ ነገር ግን ቀልድ፣ ፌዝ፣ ጫዋታ እና መገናኛ እንጂ ሰውን የሚለውጡ ውይይት ያለባቸው መድረኮች አልነበሩም። ስለዚህ እኔ ደግሞ ሰው ስለራሱ የሚማማርበት፣ ልምዳቸውን የሚያጋሩበት ቦታ ፈለኩኝ። ምን ልበለው አልኩኝ የዜጋ ጉዳዮች - Zega Matters በሚል ስም ፈጠርኩት። ቀስ እያለ ሰዎች መቀላቀል ጀመሩ።

Zega Matters በዋናነት ሰዎችን መጋበዝ፣ አንድ ለአንድ የሚደረጉት ቁም ነገር አዘል ንግግሮች በቡድን እንዲደርሱ ከማሰብም የመነጨ ነበር። ስንበዛ ከሌሎች ሰዎች ልምድ ታገኛለህ፣ ትግልህንም የሚረዳ ነገር ትቀበልበታለህ በሚል ቁጥብ በሆነ አቀራረብ የዚህ አይነት ግሩፕ ተፈጠረ። ለረዥም ግዜ የቀጠለ ስኬታማ የሆነ ግሩፕ ነበር። ብዙ ሰዎችን ያሰባሰበ፣ ራሳችንን እንድናውቅ እና በግል ደግሞ ወደ ፊት እንድንሻገር ያደረገን ሰፍራ ነበር። ስለዚህ ያኔ የተመለከትኩት ክፍተት ነው ያነቃቃኝ እኔ ስለጎደለብኝ እኔ ስለፈለኩት ፈጠርኩት እንዳጋጣሚ ደግሞ ብዙ ሰው ይህን ይፈልገው ነበር።

ኖር፦ እንደምናውቀው ስለ ኩዊር ጉዳይ ስናወራ የሁላችንም የግል ተሞክሮ ቢኖረንም፣ በጋራ የምንጋራቸው ስሜቶች ግን አሉ። ለምሳሌ፦ የመገለል፣ የብቸኝነት እና ‘በዚህ አገር ውስጥ እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት’ የሚል ስሜት በሁላችንም ውስጥ አለ። ራሳችንን ለማወቅ ኢንተርኔትና ማህበራዊ ሚዲያ ስንጠቀም ደግሞ እዛ የምናገኘው ነገር ራሳችንን በምንመለከትበት እና ከማህበረሰባችን ጋር በምንገናኝበት መንገድ ላይ የራሱን ተፅዕኖ ያሳርፋል።

በአጠቃላይ አንተ የጠቀሰከው ያ ክፍተት በደንብ ይገባኛል። በአንድም ይሁን በሌላ ሁላችንም የተሰማን ነገር ይመስለኛል። ከዛ ባለፈ ደግሞ ያንን ክፍተት ተመልክተህ ካንተ ጋር ከሚመሳሰሉ ሰዎች ጋር መገናኘት መቻልህ ትልቅ ነገር ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀጣዩ ጥያቄዬ የሚሆነው ተቀባይነቱ እንዴት ነበር? ሰዎች መቀላቀል ሲጀምሩ ውይይቶች እንዴት ነበሩ? በግሩፑ ላይ 'ይህ የክርክር ቦታ አይደለም' የሚል መግለጫ ነበረው።

ሰዎች ነፃ ሆነው እንዲወያዩ ግንዛቤ የሚያሰጨብጡ ውይይቶችን ለመጀመር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የምንፈልገው የሚያዝናናን ቀለል ያለ ነገር ነው። ቅድም የጠቀስከው ክፍተት ሌላኛው ገጽታ፣ እንደ ማህበረሰብ ያጣነው የጓደኝነት እና የመገናኘት ዕድል ነው። ሰዎች dating ቅድሚያ የሚሰጡትም ለዛ ይመስለኛል። ታዲያ Zega Matters በተመሰረተባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሰዎች እንቅስቃሴና ውይይቶች ምን ይመስሉ ነበር? በዋናነትስ ትኩረታቸው በምን ላይ ነበር?

ሃፒ፦ ቆንጆ ጥያቄ ነው! የግሩፑ መግለጫ ላይ "የመከራከሪያ ወይም ዴቲንግ ግሩፕ አይደለም" እንደሚል አሁን ላይ ረስቼዋለው። ቆይቻለው ገብቼ ካየውት። እዚህ ጋር አንድ እንዲታወቅልኝ የምፈልገው ነገር እኔ ዴቲንግን ተቃዋሚ ሆኜ አይደለም ነገር ግን የፆታዊ ጉዳይ እንደመሆኑ ከማንነት ጥያቄ በፊት ሰው ይህን ወሲባዊ ፍላጎቱ ለሟማት ነው የሚያስቀድመው።

ስሜቱ ነው ከየት መጣ ብሎ ወደዛ የሚገፋፋን። ስሜት ደግሞ በጣም ትልቅ ሃይል ነው። የሆነ ሰው የሆነ ሰውን ሊፈልግ ይችለል መጥፎ ነገር አይደለም። ግን ጌይ ወይም ሌዝቢያን ኩዊር መሆን ስለ ወሲብ ብቻ አይደለም ከዛ በላይ ብዙ የሚከተለው ነገር አለ። የደህንነት ጉዳይ፣ ራስህን ጠብቀህ መኖር ይኖራል፣ የጤና ጉዳይ፣ የቤተሰብ ግንኙነት፣ ማህበራዊ ህይወት ጠቅላላ ኑሮህ በዚህች አንድ የማንነትህ ክፍል በሆነች ስሜት ተከትሎ የሚመጡ ነገሮች ናቸው። በሰዓቱ እነዛ ነገሮች ሽፋን እየተሰጣቸው አልነበረም።

በጊዜው አብዛኛው ሰው ፌስቡክን ለዴቲንግ ነበር ሲጠቀመው የነበረው። Yahoo ግሩፕ ላይ የነበረው ምንድነው ሁሉንም አይነት ነገሮች ይነሱ ነበር። እንደ ኮሚኒቲ እንዴት እንሰባሰባለን? ደህንነታችንን እንዴት እናስጠብቃለን? ዴቲንግም ቢሆን እንዴት ይፈጠራል? ጓደኝነት እንዴት ይጠነክራል? የጤና ጉዳይ ቢሆን ወይም ማህበረሰብ እንዴት ይመሰረታል? ብቸኝነት የሃይማኖት ጉዳይ በተለይ የማንነት ጥያቄ ኢትዮጵዊ ሆነህ ይህን ማንነት

እንዴት ታካትታለህ የሚሉ ነጥቦች ይንሸራሸሩ ነበር።

ፌስቡክ ላይ ደግሞ እንደዛ አልነበረም hi ይልህና ቁመትህ ስንት ነው? ቶፕ ነህ ቦታም? የሚሉ የተለመዱ ጥያቄዎች ይበዙ ነበር። እኔ የፈለኩት ከእነዚህ የተለየ ነበር። አንድ ለአንድ ከፈለክ ማውራት ትችላለህ። ለዴቲንግም ከሆነ ሌሎች ግሩፖች ነበሩ። ለእነዛ የሚሆኑ ስፍራዎች ነበሩ። ምንድነው የሚሆነው ቁም ነገር አዘል ወሬዎች ሲወሩ በመሃል አንዱ "ከባህርዳር እየመጣው ነው አዲስ አበባ ያለ ምናምን" ሲል መልዕክቶቹን እናጠፋቸው ነበር። ይህን የምናደርገው የግሩፑን ማንነት በደንብ ለማሳወቅ ነው።

ተቀባይነቱን ስንመለከት ሁለት አይነት ነበር። በአንድ በኩል ይህ መድረክ በመገኘቱ በጣም ደስ ያላቸው ነበሩ። እኔም በግሌ የማውቃቸው ሰዎች በስሜት ነበር የምንሳተፈው ።

አዲስ ነገር አልነበረም የፈጠሩኩት Yahoo ግሩፕ ላይ የነበረውን ነገር ስፍራውን ነው የቀየርነው። ሌላው ደግሞ ሳናውቀው የተፈጠረ ባህል ነበር ገና ሃይ ስንባባል ቁመት ሮል መጠያየቅ። እኔም የሆነ ግዜ ሳለውቀው እንደሱ ነበር ከሰዎች ጋር ስግባባ የነበረው። እሱን ባህል ማስቀረት ነበር ዓላማችን። ይህ ነገር ሲቀር ግሩፑ ላይ ብዙ ሰው ግር ብሎት ነበር እና "እፈንከን" የሚል አይነት አስተሳሰብ እና ምላሽም ነበረ።

እንደዛ ያደረግንበት ምክንያት እነዚህ ነገሮች ሌላ ቦታ ነበራቸው ፌስቡክ በሙሉ እንደሱ ነበር። እኛ ግሩፑን ስንከፍተው እቅዳችን ከዛ የተለየ ነገር መፍጠር ነበር፤ የማንነት ጥያቄዎችን ለመመለስ ራሳችንን ለማወቅ እና ለመረዳ ነበር ሆን ብለን የከፈትነው።

ዓላማችን እያደግን የተሻለ አንድነት ያለው የተደራጀ ኮሚኒቲ መፍጠር ነበር። አንዳንድ ሰዎች ግን ርቆባቸው ይህ ነገር ለእኔ አይሆንም ብለው የሄዱ አሉ። ሌሎቻችን ደግሞ እየተጠራራን ነበር የምንገባው። ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ ወደ ግሩፑ የመግቢያ ጥያቄዎች ነበሩት። ተጣርቶ ነበር የሚገባው። ሲገባም ፖስት የሚያደርገው ነገር እየተጣራ ነበር። ብቻዬንም አልነበርኩም ከእኔ ጋ ስድስት ወይም ሰባት አድሚኖች ነበርን።

የማይሆን ፖስት ምስል ወይም ፅሁፍ ሲሆን እናጠፋ ነበር። በዛ ምክንያት የራሱን መልክ ይዞ ሰው ጥያቄ ሲኖረው የሚመጣበት

መረጃ ሲፈልግ የሚመጣበት ስፈራ ሆኖ ነበር። ስለዚህ ሲጀመር ሁለት አይነት አቀባባል ነበረው። ከተለመደ በኋላ ግን አሪፍ ነበር።

በጣም ወግ አጥባቂ የተባልንበት ምክንያት በተቻለ መጠን የአሁኑን ግራይንደር ሆኖ ወሬዎች በሙሉ ጠበው እንዳይቀሩ ስለፈለግን ነው። ሰፋ ያለ ሃሳብ የሚነሳበት፣ ማንነትን መረዳት የሚያስችል ስፍራ መሆን እንዲችል ስንሠራ ስለነበር ነው።

በማህበራዊ ኑሮ ብዙ ነገር እውቀናል ነገር ግን ይህን ስሜታችን የነገረን ማንም አልነበረም። ጨለማ ውስጥ ሆነን የኖርነውን ሕይወት ለማንም ሳናጋራው የኖርነው ነገር ነበር። እንደ አስፈላጊነቱ ወሲባዊ ዝንባሌያችን ጨለማ ውስጥ ፈልገን እኔ ማነኝ? ይህ ስሜት ምንድነው? ብለን መመለስ የምንችልበት መድረክ አልነበረውም። ራሳችንን ማወቅ እንድንችል እና ቁም ነገር አዘል ነገሮችን መናጋር እንድንችል ቁጥጥር መኖር ነበረበት።

ኖር፦ ትንሽ ያልከውን ለማስፋት ያህል መጀመሪያ ላይ ዴቲንግን ወይም ወሲብን የምቃወም ሆኜ አይደለም ብለኸናል እና የበለጠ ለመረዳት በዛ ግዜ Zega Matters ላይ ይጋሩ የነበሩ መረጃዎችን ብንዳሰሳቸው ወሲብ ቀስቃሽ መረጃዎች ባይሆኑም ፆታዊነት ላይ ግንዛቤ አስጨባጭ መረጃዎች ናቸው። ነገር ግን ጠበብ ያሉ አልነበሩም እና ዋናው ነጥብ የነበረው በምናደርጋቸው ነገሮች ደህንነታችንን የሚጠብቁ ነገሮች እንዲኖሩ እንደነበር አስባለሁ አንተ ምን ትለናለህ?

ሃፒ፦ በትክክል እኛ የፈለግነው መረጃውን ነበር። መረጃውን ማግኘት፣ መረዳት እና ራሳችንን ስለማወቅ እንጂ አዳማ ስላለ ቦተም ወይም ቶፕ ስለማግኘት አልነበረም። ያገናኘን ፆታዊነታችን ነው። አዎ ስለ ወሲብ ይወራል ሰው ታገኛለህ። ግን ምን አይነት ሰው ታገኛለህ? ስትገናኝስ ምን አይነት ጥንቃቄ ትወስዳለህ? የሚለው መረጃ ነበር እኛ የምንፈልገው። ሆክአፑን ነበር እኛ ስንከላከል የነበረው። ሰዎች እዛ አውርተው ሌላ ቦታ ሊገናኙ ይችላሉ እሱ የእኛ ጉዳይ አልነበረም። ግሩፑ ሰው ማገናኛ ከሆነ እኛ እንዲነሱ የፈለግናቸው ጥያቄዎች ቦታ አያገኙም ነበር። ስለ ኃጢአት ጨንቆኛል ማማከር ፍልጋለው ሲል ከጎኑ ያለው ሰው ሁክአፕን ሚያሰብ ከሆን መግባባት አይኖርም። ለእነዛም ቦታ አላቸው ስለዚህ ለእነዚህ ጥያቄዎች ነበር ቦታ የሰጠነው።

ኖር፦ እነዚህ የፌስቡክ ግሩፖች ማህበረሰቡን በመገንባት ረገድ ትልቅ ተፅዕኖ ነበራቸው ብዬ እሰባለሁ። በወቅቱ የነበሩ ሰዎች እርስ በእርሳቸው የሚወያዩት ጓደኝነትን ፈልገውም ጭምር ነበር። ግሩፑ ከወሲብ ወይም ከዴቲንግ ባለፈ፣ እውነተኛ ግኑኝነት መፍጠር የተቻለበት ስፍራ ነበር።

ሃፒ፦ በትክክል

ኖር፦ እነዚህ በኦንላይን የነበሩ ጓደኝነቶቸ እንዴት ነው ወደ መሬት ወርደው አካላዊ ሊሆኑ የቻሉት? በግልህ ሊሆን ይችላል ወይም Zega Matters ላይ ባወራሃቸው ሊሆን ይችላል እንዴት ነበር ጠንክረው ወደ መገናኘት ሊደርሱ የቻሉት እሱን ትንሽ ብትገልፅልን?

ሃፒ፦ በመጀመሪያ ኦንላይን ስትተዋወቅ በባህሪ ሊሆን ይችላል። በማውራት በፍላጎት የሚገጥሙህን ሰዎች ታገኛለህ። ስትወያይ ስታወራ ምን አይነት አስተሳሰብ እንዳለው ትመለከታለህ ከማን ጋር ምን እንደምታደርግ ታያለህ። በአካል ለመገነኘት ፍላጎት ያድርብሃል ስትገናኝ ኦንላይን ያለው ማንነት ተመሳሰሎ ካገኘኸው ወደ ጓደኝነት እየጠነከረ ሊሄድ ችላል ከግዜ ብዛት እየተጠናከረ ወደ ቤተሰባዊነት ያድጋል።

መጀመሪያ ለመተዋወቅ መድረክን ፈጠርን፣ ከዛ መተማመን ሲፈጠር በአካል መገናኘት ይመጣል። ሰውን ለማግኘት ቀላል መድረክ ያደረገው እሱ ነበር። ድንገት ወተህ ትምህርት ቤት ሄደህ ወይም ኳስ ስታይ ወይም እድር ውስጥ ሰፈር ውስጥ ሄደህ ሰውን የምትገናኝበት ነገር አልበረም። ሁሉም ጥጉን ይዞ ተደብቆ ነው ያለው ወይ ግንባሩ ላይ “እከሌ ዜጋ ነው” የሚል አይተህ ሄደህ የምትተዋወቀው ነገር አልነበረም። ስለዚህ ኦንላይን በጣም ወሳኝ ነበር።

እንዴ ፌስቡክ ላይ ተገናኝተህ መተማመን ከፈጠርክ በኋላ በአካል ትገናኛለህ፤ ነገሮች እየጠነከሩ ሲሄዱም ሰዎች ወደ ቁም ነገር ይገባሉ። ጓደኛሞች ይሆናሉ፣ በፍቅር ይወድቃሉ። ለምሳሌ እኔ እዛው የተዋወኳቸው የሃያ ዓመት ጓደኞች አሉኝ፤ እዛ ባይሆን ኖሮ በጭራሽ ላገኛቸው አልችልም ነበር። በወቅቱ እኔንም ቢሆን ራሴን እንዳውቅና እንዳውቅበት ረድቶኛል። እንዴ

ራስህን ከተቀበልክ በኋላ ደግሞ ሌሎች ፍላጎቶችህ ግልጽ ይሆኑልሃል፤ ይህም በራሱ ወደ መደራጀትና ማህበረሰቡን ወደ መገንባት ይመራሃል። ዋናው ነገር ግን መጀመሪያ ሰውን የምንተዋወቅበትን መድረክና ዕድል መፍጠሩ ነበር።

ኖር፦ እዋ፣ መተማመንና መግባባት ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ። ይህ ሐሳብ ደግሞ አንድ ነገር እንድጠይቅ አነሳሳኝ፤ ከኦንላይን ትውውቅ ባለፈ በአካል ወደ መደራጀት እንዴት ተሸጋገራችሁ? አሁን ላይ ባለህ የማስተባበር ሥራ ተሞክሮ፣ ከማህበራዊ ሚዲያ ውጪ ያለው እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ብታጋራን?

ሃፒ፦ እሺ ኦንላይን ሲሆን የትም የምትገናኝበት ስፍራ ስላልነበረ ነገሮች የሚቀሉ ናቸው። ግን ሁላችንም ኦንላይን የምንኖር ሰዎች አይደለንም። በአካል መገናኘት መቀራረብ ትፈልጋለህ። ኦንላይን የሚኖረው ግንኙነት የራሱ ጥቅም ቢኖረውም በአካል መገናኘት ደግሞ ከፍተኛ ጥቅም አለው። በተለይ ኢትዮጵያ ስትኖር መተማመኑን ለመመስረት ግዜ ይፈጃል። ከዛ በኋላ በዜጋ ስም ነው የምትገናኘው። የት እንደምትኖር አትተዋወቅም እና በጊዜ ሂደት ትግባባለለህ።

ኦንላይን እንደ መሳሪያ ነው። ወደ ዋናው ቦታ የሚያደርስ መዳረሻ ነው። አዲስ አበባም ሳለን ይህ ተከስቷል። ኦንላይን የተዋወቅን ሰዎች ነን ተሰብሰበን የጓደኛ ቡድኖች የተፈጠሩት። ከዛ በግዜ ሂደት ሰዎች ተሰባሰበው እንደ ድርጅት የሆነው። ከዛ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የወሲባዊ ጤና ትምህርቶች፣ ሰው መርዳት፣ የታመመን ማሳከም የተጀመረው ኦንላይን በመተዋወቅ ተጀምሮ ነው ወደ ድርጅት የተለወጡት።

እዚህ ሃገር ከመጣሁ በኋላ ደግሞ ከሃገር ቤት በተሻለ ደህንነት ያለው ነው። ምንም እንኳ እንደ ሃገር ቤት መንግስት ይከሰኛል ማህበረሰቡ ያጠቃኛል የምንለው ዓይነት ፍርሃት ባይኖርም ሀበሻ እንደመሆናችን መጠን ይዘነው የመጣነው ብዙ ኮተት ያለን ኮሚኒቲ ነን።

በዋናነት የራስህን ሰው ማግኘት እዚህም ይከብዳል እንደሌላው ኮሚኒቲ የተዘጋጁ መድረኮች የሉንም። ፈረንጆቹ ከብዙ ትግል በኋላ ባሳኩት ነፃነት የራሳቸውን የጌይ ባር

ወዘተ አላቸው። የዲያስፖራው ኮሚኒቲ ከተባለ የበዓል ፕሮግራም የሚያከብሩበት ቸርች ወይም መስጊድ አላቸው። ብቻ የራሴ የምትላቸውን ሰዎች የምታገኝባቸው ቦታዎች አሉ። የሚመስልህን ሰው ትፈልጋለህ። ጥቂት ነን ግን ሃገርህን ቋንቋህን የሚጋራ የሚረዳህ ሰው ትፈልጋለህ ኮሚኒቲ ትምስርታለህ።

የድሮዎቹም ይህን ያደርጉ ነበር። ባልሳሳት Yahoo ግሩፕ ራሱ በፈረንጆቹ 2000 ወይም 2001 አከባቢ የነበረ ነው። ከእርሱ በፊት በ1994 ደግሞ ኢንተርኔት ፎረሞች ላይም ይገናኙ የነበሩ ሰዎችም ነበሩ። በዓመት አንዴ ተገናኝተው ኮሚኒቲ ለመመስረት ጓደኝነት ለመፍጠር ይሞክሩ ነበር።

በግዜ ሂደት ሰዎች ይጓዛሉ የራሳቸውን ጓደኛ ቡድኖች ይመሠርታሉ። በቀስታ እነዛ ነገሮች ይበተናሉ። ያ በኦንላይን እንዳለ በአካል ለመቀየር ሞክረው ነበር። የእኛ ዘመን ደግሞ የዚህ አይነት ነገር አልነበረውም። መሰባሰብ መገናኘት እንፈልጋለን ግን መድረኩ አልነበረም። ይህም ሌላ ክፍተት ነበረው። እኔና ጓደኞቼም ለምን ይህን መድረክ እኛ አንመስርተውም በሚል አራት ሆነን አመታዊ ፕሮግራም እናዘጋጅ በሚል እንደ ቀላል ተጀመረ። በየዓመቱ እያደገ እያደገ መጣ።

ለምሳሌ በዚህ ዓመት ወደ መቶ ያህል ሰዎች የተገኙበት ነበር። ከዛ በፊት ጥቂት ጓደኞች ነበርን የምንገናኘው። ለበዓል ሲሆን ከአስር በላይ ሆነን ነበር የምንገናኘው። አብዛኞቻችን የምንተዋወቀው ኦንላይን ነው። በተለያዩ ግዛት ነው የምንኖረው ርቀቱ እንዳለ ሆኖ አካላዊ መገናኘት ግን ያስፈልገን ነበር።

ስንረዳው አንድ ሰው ሁለት ሦስት ሰው ያውቃል እና ብዙ ኔትወርክ እንዳለን ተረዳን። የመጨረሻ ግቡም ያለውን ሰው ማሰባሰብ እና ማገናኘት ስለሆነ ሁሉም የማህበራዊ ሚዲያ ስፍራዎች ወደ አካላዊ መተዋወቅ የሚያመጡ መገልገያ መሳሪያዎች ናቸው።

ኖር፦ በትክክል የተረዳሁህ ይመስለኛል! እኔም በመጨረሻ የገባኝ የምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉም ነገር ስለነበረን ክፍተት ነው ወስጣችን ስለነበረ ባዶነት ነው።

ባጠቃላይ ማደራጀትን ማስተባበርን ስናስብ ወይም አክቲቪዝምን ለወደፊት ስለሚመጣው ሰው ወይም ለሌላ ሰው የሚል ክፍል አለው ነገር ግን ሰንገነዘበው ሰዎችን የሚገፋፉት አሁን ላይ ያሉ ክፍተቶች ናቸው።

ለራሳቸው ሆነ በዙሪያቸው ላሉ ሰዎች መፍጠር ስለሚፍልጉት ስፍራ ነው። ከዛ እሱ ነው እየሰፋ ወደ ብዙ አቅጣጫ የሚሄደው። ይህ የባዶነት ስሜት ሁሉም ቦታ አለ ብዬ እሰባለው። ሃገር ቤት ሳለን የብቸኝነት፣ የመገለል ስሜት፣ የደህንነት እጦት ይህን ክፍተት እና ባዶነት ሊፈጥር ይችላል። ከዛ በላይ ከሚመስለን ጋር የምንፍልገውን ህብረት ባለማግኘታችንም ሌላ ጫና ያለው ነገር ነው።

በተመሳሳይ ሰዓት ከሃገር ስንወጣ የምናስበው ይህ ሁሉ ነገር የሚጠፋ ነው የሚመስለን። ልክ ነው በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይ ችግሮች ላይገጥሙን ይችላሉ። ነገር ግን ትተህ የምትመጣው ነገር አለ። ስለዚህ ትትህ የመጣኸውን ኮሚኒቲ ልትፈልግ ትችላለህ።

እዚህ ሃገር ኩዊር ወዳጆች ሊኖሩህ ይችላሉ ግን ሙሉ ለሙሉ አይረዱህም። ያንተን ቋንቋ የሚረዳ አመለካከትህን የሚጋራህ ሰው ትፈልጋለህ። ከማስታውሳቸው ነገሮች አንዱ ለሌሎች ሰዎች እየተናገርኩ መተርጎም የሚኖሩብኝ አማርኛዎች አሉ። እንግሊዝኛው ላይ ትርጉም ሊሰጡ የማይችሉ ማለት ነው። ለኩዊር ኢትዮጵያውያን ቢሆን መተረጎም አይጠበቅብኝም ነበር። ይህን ክፈተት እኔም እረዳዋለው ለማለት ያህል ነው።

ሃፒ፦ በትክክል። ሁላችንም እዚህም እንሁን ኢትዮጵያ የምንፈልገው ነገር የሚረዳንን ሰው ማግኘት ነው። ማንንም ልታገኝ ትችላለህ ነጩንም ጥቁሩንም እዚህ ካለው ኮሚኒቲ የምትጋራው ነገር ይኖራል። ግን ያንተን አይነት ሰዎች ስታገኝ በራስህ ቋንቋ ስታወራ፣ ተሰብሰበህ እንጀራ ስትበላ፣ ኢትዮጵያዊ ሆነህ ጌይ መሆን አትችልም ተብለህ የተገፋኸው ሰው አብረኸው ስትቋደሰ የግድ ከሁለቱ አንዱን መምረጥ እንደሌለብህ ትረዳለህ። ዜጋም ኢትዮጵያዊም መሆን ትችላለህ።

በሃይማኖትህ እና በወሲባዊ ፍላጎትህ መሃል በባህል

እና በወሲባዊነትህ መካከል ምርጫ መኖር እንደሌለበት ያስገነዝብሃል። የራስህን ሰዎች ማግኘት ነገሮችን ያስታርቅልሃል።

አገር ቤት ሳለሁ ይረብሸኝ የነበረው ነገር 'አንተ ብቁ አይደለህም፣ መኖርም የለብህም' የሚለው እሳቤ ነበር። 'እየኖርኩ ነው፣ ተፈጥሬያለሁ፤ ታዲያ እንዴት ልኑር?' ስትል፣ 'ዜጋ ሆነህ ኢትዮጵያዊ መሆን አትችልም! ሃይማኖትህ አይፈቅድም፣ ገሃነም ትገባለህ፣ መጥፋት አለብህ' ይልሃል። ነገር ግን የራስህን ዓይነት ሰው አግኝተህ ስታወራ ብቁ እንደሆንክ ትረዳለህ።

አሁን ላይ ሆነን መለስ ብለን ስናየው 'እንዲህም አስብ ነበር እንዴ?' ብለን ልንስቅ እንችል ይሆናል። ነገር ግን ያኔ ታዳጊ ሆነህ ራስህን መረዳት በጀመርክበት ሰዓት፣ 'ልክ አይደለህም፣ ብትሞትም ግድ የለም' የሚለው ነገር በጣም ያስፈራ ነበር።

ብቻህን ስትሆን ነገሩ ይከብዳል። ሌሎች ካሉ ግን አቅም ይሰጥሃል። ያኔ ስሜቱ 'ገሃነም እንኳን ብንሄድ ተሰብስበን እንሄዳለን፣ እዛም ቢሆን አስደሳች እናደርገዋለን' የሚል ዓይነት ነው (ገሃነም እንሄዳለን ብዬ አስቤ ሳይሆን ነገሩን ለመግለጽ ያህል ነው)። መገለል በጣም ከባድ ነውና።

ከአገር ወጥተህ የአንተን ዓይነት ሰው ብታገኛም እንኳ፣ ስሜትህን መግለጽ ስትፈልግ የግል ማንነትህና አስተዳደግህ የራሱ የሆነ ልዩነት ይፈጥራል። የመጣንበት ሰፍራና አስተዳደጋችን ራሳችንን የምናይበት እንደ መስታወት ነው። ስለዚህ የሚመስልህን ሰው ማግኘት መቻልና ብዙ ነገሮችን በጋራ መጋራት በራሱ ሰውን ያረጋጋል። ከሰዎች ጋር ሕብረት መፍጠር ደግሞ ተፈጥሮአዊ የሆነ ሰዋዊ ባህሪ ነው።

ከሰዎችም ብዙ ትማራለህ፤ እንዴት ራሳቸውን እንዳወቁ፣ ሃይማኖተኛ ሆነው ሳለ ደግሞ እንዴት ራሳቸውን ወደ መቀበል እንደመጡ ትረዳለህ። በሃይማኖት ውስጥ አድገህ ኩዊር (Gay) መሆንህን ስትረዳ፣ 'ከሁለቱ አንዱን መምረጥ አለብህ' የሚል ድምፅ ይሰማሃል፤ ያ ደግሞ በጣም ያማል።

ሁለቱንም መተው አልፈልግም! ሳልወድ ማንነቴን በውስጤ አገኘሁት፤ ሳልመርጥና ሳልፈቅድ ሙስሊም አድርጋችሁ አሳደጋችሁኝ፤ ሳልፈቅድ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወለድኩ። እንጀራ እፈልጋለሁ፣ የሐበሻ ምግብ ቤት እፈልጋለሁ። ነገር ግን ማንነቴ ከታወቀብኝ ከእነዚህ ቦታዎች ሁሉ እባረራለሁ። ማንነትህ ታውቆ ባለህበት ቦታ ምቾት ካጣህ ግን፣ የተፈጠረልህ ቦታ ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን የሚመችህን ሰፍራ ራስህ መፍጠር አለብህ!

ልጅ ሳለህ ሳትፈልግ የመረጡት ቸርች፣ የመረጡት ትምህርት ቤት ይወስዱሃል አሁን የራስህን ሰፍራ መምረጥ ያለብህ አንተ ነህ። ይህ በእድሜ የሚመጣ ነው እንጂ ልጅ ሳለው ማሰበው አልነበረም። የተሰመረልንን ነው የተከተለነው። የሀበሻ ዜጋ ሰብሰብ ፈጥረን ሁሉም እንደ ፈለጉት የሚሆኑበትን ሰፍራ መፍጠር መቻል ነው። እንደ “ድራግ” መልበስ የሚፈልግ ካለ እንደዛ ለብሶ፣ መደነሰ የሚፈልግ ደንሶ ሰው ራሱን የሚሆንበት ነው። ኢትዮጵየ ውስጥ ካለህ ላይገባህ ይችላል ምክንየቱም እዛ ስትሆን ምትሄድባቸው ቦታዎች ራስህን እንድትሆን የማይፈቅዱ ናቸው።

እዚህም ቢሆን እንደ ሰርግ ወይም የዘመድ ሰብሰብ ያሉ የቤተሰብ ፕሮግራሞች ላይ ሰትገኝ ያን ያህል ነፃነት አይሰማህም። ለዛም ነው የራሳችንን ሰፍራ ፈጥረን ከምንመርጣቸው ቤተሰቦቻችን ጋር የምንቀራረበው። የቀስተ ደመና ባንዲራችንን ይዘን፣ ከሚመስሉን ሰዎች ጋር ተሰባሰበን ጊዜ ማሳለፍ ትልቅ ትርጉም አለው።

ከቤተክርሰቲያን ብትገፋ እንኳ፣ ራስህን መደበቅ የማይጠበቅብህ ሌዝቢያን ወይም ጌይ የሆኑ ፓስተሮችና ቄሶች ያሉበት፣ የተገፋ ሰዎች ተገንጥለው የመሰረቱት የራሳቸው ማኅበር እዚህ አገር አለ። በእኔ ሁኔታ ደግሞ መስጊድ ላይኖር ይችላል፤ ነገር ግን ሰዎች የራሳቸውን ቦታ ፈጥረው ረመዳንን አብረው ያፈጥራሉ፣ ኢድንም አብረን እናከብራለን። ያውም የትኛውንም ማንነትህን ሳትደብቅ!

ራሰን መሆን በራሱ በሰነ-ልቦና ረገድ ሰውን ያረጋጋል፤ ማህበረሰብህንም ትገነባበታለህ። በአጠቃላይ Community መፍጠር የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎት ነው። በውስጣችን

የሚስማንን ክፍተትና ባዶነት የሚሞላ ስለሆነም፣ ማህበረሰብ መፍጠር እጅግ እርካታ የሚሰጥና አስፈላጊ ነገር ነው።

ኖር፦ የነገርከን ነገር በትክክል ትርጉም የሚሰጥ ነው። እኛ ሰዎች ብዙ ጊዜ ተቃርኖዎችን በውስጣችን ይዘን ነው የምንኖረው። ብዙውን ጊዜ ማህበረሰቡም ሆነ እኛ ራሳችን መጀመሪያ ላይ ኩዊር (Queer) መሆንን ከአንድ ነገር ጋር ብቻ እያይዘን እናስብ ነበር። ይህ የዴቲንግ (Dating) እና የሁካፕ (Hookup) ባህል ብቻ እንደሆነ ተደርጎ መታሰቡ ማንነታችንን አጥብቦታል። ይህም ማህበረሰቡ እኛን እንደ 'ሴሰኛ' ብቻ አድርጎ እንዲስለን አድርጓል።

አሁን ግን ከእኛ ማህበረሰብ ውጪ ያለውን ያን የተሳሳተ እይታ ሰብረን፣ ከራሳችን ጋር የምንታረቅበትና በውስጣችን ያሉ ብዙ ተቃርኖዎችን የምናስታርቅበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

ሃፒ፦ ልክ ነው። ነገር ግን እነዚህ ተቃርኖዎች የሚኖሩት ሰው በእኔ መንገድ ሂድ፣ እኔ ያደረኩትን አድርግ ብሎ ስለሚያስቸግርህ ነው እንጂ በራሱ ተቃርኖ ላይሆን ይችላል እኮ። በሁካፕ ወሲባዊ አጣማሪህን እያረካህ፣ በዚህ በኩል ደግሞ ሥራህን እየሰራህ፣ ጓደኝነትህ ላይ እየሰራሁ፣ ፓርቲ እያደረክ መኖር ትችላለህ። ዞሮ ዞሮ ሰውን እስካልጎዳህ እና ራስህን እስካልጎዳህ ድረስ ነፃነት መኖር አለበት። ግን በእኛ ባህል አንዱ አንዱን የመጫን ባህል ስላለ ተቃርኖ ሊታይ ይችላል። ምክንያቱም ሌላን ሰው እየመሰልክ የተወሰነውን ማንነትህን እየደበክ አስመስለህ እንድትኖር ልትገደድ ትችላለህ። ዞሮ ዞሮ መጨረሻ ላይ ሁላችንም ለራሳችን ነው የምንኖረው። በዚ ግባ በዚ ውጣ ይላሉ እንጂ ሰው ለራሱ መወሰን ይችላል። የውሳኔያችንን ዋጋ እንከፍላለን ስለዚህ የማደርገው ነገር ልክ ነው ብለህ ካሰብክ እና ከወሰንክ እና ተቀብለህ እስከኖርክ ድረስ እሱ ነው ዋና ነገሩ።

ኖር፦ ውሳኔህን ከሌሎች ከሚጋሩህ ሰዎች ጋር ስታደርገው ደግሞ ቀለል ሊል ይችላል

ሃፒ፦ በትክክል ለዛም ነው ኮሚኒቲ የሚያስፈልግህ ማንነትህን ውሳኔህን ያፀድቃል።

ኖር:- መጨመር የምፈልገው ሌላ ጥያቄ ስለ ኖር እና ዜጋ ማህበር ነው። ዜጋ ማህበር ፕሮግራሞችን ስታዘጋጁ የኖር መጽሃፍ እትሞችን ታስተዋውቃላቹ። ይህ እንደ ድልድይ ነው ብዬ እስባለው። በኢትዮጵያ በኦንላይን የሚገኝን ነገር እናንተ ከሃገር ውጭ በምትሰባሰቡበት ስፍራ መኖሩ ያለው ተቀባይነት እንዴት ነው? በተጫማሪ የዚህ አይነት ስራዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰርተው እናንተ ባላቹበት መገኘቱ ሰዎች ላይ ምን አይነት ስሜት ፈጥሯል?

ሃፒ:- ሰው የራሱን ታሪክ ተንፀባርቆ ማየት ይፈልጋል። ኖር ደግሞ ይህን ነው እየሰራ ያለው። ኖር ላይ እንደዚህ የሰዎች ታሪኮች ተጽፈው ስታይ ከሰው ታሪክ የምትማርት ወይም አንተ ውስጥ ያለውን ልትገልፀው ያልቻልከውን ነገር የምትመለከትበት እንዱ መንገድ ነው። ኖር ሆነ ሌሎች ኢትዮጲያ ውስጥ ያሉ ኩዊር ሚድያዎች የሚያዘጋጁት ሌሎች መጽሔቶች ላይ ተንፀባርቆ መታየት ጥሩ ነው። የሆነ ግዜ ሰዎች ኢንስታግራም ላይ ፎቶዋቸውን አድርገው የተወሰነ ታሪካቸውን ሚያጋሩበት ነገር ነበር ። ይህ አንድ እይታን የሚፈጥር መንገድ ነው። አለን የሚል ልዕክት ማስተላለፍ ነው። አዳዲስ ጓደኞች ይኖሩሃል፣ ሩቅ ያሉ ሰዎች ምን አይነት ታሪክ እንዳላቸው ያሳይሃል፣ እንደ ዘገባ እንደ ፊልም ማንነትህን ሊያስረዳህ የሚችል ነው።

እኛ እንደ ሀበሻ ታሪካችን የምንለው የሰማነውን ነው። እንደ ኖር እናንተም እየሞላችሁ ያላችሁት ኮሚኒቲው መካከል የነበረውን ክፍተት ነው። አስፈላጊ ነገር ነው። ሰናድግ ሰምተን ያደግናቸው ታሪኮች አሉ። የነገሥታት፣ የጀግኖች፣ የሃይማኖቶች ታሪክ አለ። እነዛ ውስጥ ምንም አይነት የኩዊር ታሪክ የለም። ቢኖርም ጭራሽ አይነገርም። ኖር ይህን ትይታ ለመፍጠር ነው የሚጠቅመው። ታሪክ አስተሳሰባችንን ይቀርጻል። ይህን ባዶነት ለመሙላት እየተጋቹ ነው። የፈጠራ ታሪኮች አይደሉም ትክክለኛ ታሪኮች ናቸው ይህ ደግሞ ከእኛ ጋር የሚገናኝ ነገር ነው። ሰዎች ከእነዛ ታሪኮች ይማራሉ። ለሚገጥማቸው ችግር መፍትሄ ያገኙበታል፣ ተስፋን ይሰጣል፣ ነገሮች ቢገጥሙን ልንቋቋምበት የምንችላቸው ነገሮች ናቸው። ትግላችንንም ያቀላል ብዬ እስባለው።

ኖር:- ታሪኮቻችን መውጣታቸው እና በራሳችን ቋንቋ መነገራቸው እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ያሉብንን ክፍተቶች ለመሙላት ይረዳሉ። አንት እያደረኩ ያለኸው ነገርም የሚደነቅ ነው። በመጀመሪያ

በዚህ ቃለመጠይቅ ስለተገኘህ እናመሰግናለን። ላለፉት አሥራ አምስት አመመታት ይህን ስታደርግ ነበር። ታሪክህን ልታጋረን ስለተገኘህ እናመሰግናለን።

ሃፒ፦ አንድ ነገር ለመጨመር ያህል የዚህ አይነት መጽሐፍት ማውጣት በራሱ አንድ የአክቲቪዝም መንገድ ነው። ስናድግ ስምተን ያደግነው የተዛባ አመለካካት ስለማንነታችን ራስን መጥላቱን ራስን አለመቀበሉን የፈጠረው ከሀይማኖት ይምጣ ከማህበረሰቡ ትግል ውስጥ እንድንገባ ያደረገው የተነገረን መጥፎ ታሪኮች ናቸው።

የሚሰማው ዜና በሙሉ ወንጀለኞች እና ደፋሪዎች ናቸዉ ተብሎ ነው የሚዘገበዉ። የራሳችንን ታሪክ በራሳችን መናገሩ ነገሩ ሙሉ ለሙሉ ባያጠፋው የሆነ ሚዛን መፍጠር ይችላል ብዬ አስባለው። አስተዋይ ሰው መጥቶ ይህን ነገር ሲመለከት የማገናዘብ ነገር ይሰጠዋል። ከዛ በተጨማሪም ለዜጋው ራሱ ከፈተኛ ጥቅም ይሰጣል። እኔም በግሌ ዜጋነቴን ስረዳ በጥላቻ ነበር የተነሳውት። ዬ…ይ ደስ ሲል ብዬ አልነበረም። ፌስቡክ ላይ ሰው ስናወራ ጥሩ ሰው ነው ይቺ ብቻ ናት ችግርህ (ዜግነት) ምንለው ከሰማነው ጥላቻ ነው። ግን የሰው ታሪክ ስንሰማ ደግሞ ይለውጠናል። የሚገጥማቸውን መከራ የሚያሳይ መሆኑ አሸናፊነታቸውን ሚያስተምር ነው። የዚህ አይነት ታሪኮች ባህላችንን፣ ሃይማኖትን የሚሞግት ጥላቻን የሚቃወም ነው። እንደ ሰው ተፈትነው እንዳለፉ እና ክፉ ሰዎች እንዳልሆኑ የሰዎች ታሪክ ሲነገር ነው ማወቅ የሚቻለው። የተማርነው ሃገርን የሚገለብጥ ቤተሰብን የሚበትን ተደርጎ እየታሰብን ነበር። ስንሰማ ያደግነው እንደ ታዳጊ ከባድ ነበር። ይህ ግን ከእኛ በፊት የነበሩ እንደነበሩ ሰሰማ እና ኖረው እንዳለፍ እንዲሰሙ ማድረግ አንድ የትግል መንገድ ነው።

ኖር፦ በጣም እናመሰግናለን፡ አንተም በዚህ ሁሉ ተስማምተህ ስለተገኘህልን ድጋሚ ምስጋናዬን መግለፅ ፈልጋለሁ።

ሃፒ፦ ይህ ስራ የቅብብሎሽ ነው እኔን አክብራችሁ መጥራታቹ በራሱ ለኔ ትልቅ እድል ነው። በተጨማሪ እየሰራቹት ያላቹት ነገር በጣም የሚደነቅ ነው። ሰው ማሰባሰብ ማደራጀት ከፍቅር የተነሳ ምታደርጉት ነገር እንጂ ማንም አስገድዷችሁ አይደለም። አራተኛ እትም መልቀቅ ቀላል ነገር አይደለም በርቱ!



# ስለ ሌዝቢያን ፍቅር ጥልቅ እይታ
# ከጆይ እና ሃኒ ቢ ጋር

(አንቺ/ እሷ)

ኖር፦ እንኳን ደህና መጣችሁ

በህብረት፦ እንኳን ደህና ቆያችሁን

ኖር፦ ራሳችሁን እንድታስተዋውቁ ዕድሉን እንሰጣችሁ።

ጆይ፦ እሺ እኔ ጆይ እባላለሁ she/her

ሃኒ፦ ሃኒ ቢ she/her

ኖር፦ መልካም! የመጀመሪያ ጥያቄያችን የሚሆነው ጆዬ ካንቺ እንጀምር እስኪ ስለ ሃኒ በጣም የምትወጂውን ሶስት ነገር ትነግሪናለሽ። ከዛ በኋላ ሃኒም ስለ ጆዬ የምትወጂውን ሶስት ነገሮች ትነግሪናለሽ።

ጆይ፦ ይሄማ ቀላል ነው! ሺህ የሚጠቀስ ይኖራል። ነገር ግን ሶስት ከተባለ… አንደኛ ሃኒ በጣም positive ቅን ልብ ያላት ሴት ነች። ሁለተኛ በጣም አፍቃሪ ነች እሱን ነገር ወድላታለሁ። ሶስተኛ ደግሞ ቆንጆ ነች።

ኖር፦ አይተናል እኛም… ፈገግታ። በተቆራረጡ ፎቶዎችም ቢሆን የተወሰነ ውበት አይተናል። እሺ ሃኒስ ከጆዬ ምንድነው የምትወጂላት?

ሃኒ፦ እኔ የምወድላት ብዙ ነው። አንደኛ ነገር በጣም መልካም ነች! ስልህ በቃ በጣም መልካም ነች። በጣም ቻይ ነች! እኔ ትንሽ አስቸጋሪ ነኝ እሷ ደግሞ ቻይ ነች። መረዳቷን ወድላታለሁ፣ ከዛ ደግሞ ንፁህ ልብ ነው ያላት የምትፈቀር አይነት ሰው ነች።

ኖር፦ በጣም ደስ ይላል… ይህ ኢንተርቪው በአካል ቢሆን አስባችሁታል እንዴት ሊሆን እንደሚችል ስትሽኮረመሙ ማየት?

ሁለታችሁም ተመሳሳይ ባህሪ ቢኖራችሁም የተለያዩ ኳሊቲዎቻችሁን ነው የወደዳችሁት። ብዙዎቻችን relationship ውስጥ ስንገባ አንደኛችን የጎደለንን ነገር ነው አንደኛችን የምናሟላው። ብዙ ግዜ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ሳይሆን በእርግጥ ተመሳሳይ የሆኑ ሰዎችንም እንመርጣለን ግን አንድ አይነት ሰዎች አይደለንም። አንደኛው የሌለውን ነገር እያሟላ ስለምንሄድ ማለት ነው።

ከዚህ አስከትለን ሁለታችሁንም የምንጠይቃችሁ የተገናኛችሁበትን አጋጣሚ እንድትነግሩን ነው። ስትመልሱ መረዳዳት ይቻላል።

ጆይ፦ እኔ ልጀምር። የተገናኘነው የሆነ ግሩፕ ላይ ነው። Rare የሆነ መገናኘት ነው የተገናኘነው። የቴሌግራም ግሩፕ ነበር እዛ ግሩፕ ላይ ወጣ ገባ ስትል እንዲሁ ዝም ብለን ማውራት ጀመርን። ከዛ በኋላ ትንሽ ግዜ አውርተን፣ ስሜታችንን ግልጽ አደረግን። አንዳችን ለአንዳችን ለመውደቅ ብዙ ግዜ አልፈጀብንም but at the same time ደግሞ challenging ነበር። ትንሽ ቆይተን በአካል ለመገናኘት በቃን። አንድ ከተማ ስላልነበርን ቶሎ በአካል አልተገናኘንም ነበረ... በአካል ስንገናኝ ከጠበኩት በላይ ነበር የሆነብኝ ሁሉም ነገር ስለዚህ እንዴት ነው የተገናኛችሁት የሚለውን ጥያቄ የምመልሰው ቴሌግራም ላይ ነው የተገናኘነው።

ኖር፦ ስለዚህ ኦንላይን ነው የተገናኛችሁት ማለት እንችላለን። ሃኒን የምጠይቀው ደግሞ በአካል ልትገናኙ ስትሄጂ የነበረውን ስሜት ንገሪን። ምን ጠብቀሽ ነበር?

ሃኒ፦ እውነት ለመናገር በአካል ስንገናኝ ብዙ ነገር አልጠበኩም ነበር።

ኖር፦ ማነው ቀድሞ ቦታው ላይ የደረሰው?

ሃኒ፦ Obviously እኔ ...(ሳቅ) እኔ ነኝ በጉልበት ታግዬ ታግዬ አልመጣ ብላኝ… ሃገር … ከተማ አላቅ ብላኝ…ሰው ሃገር ላይ ጠርታኝ ነበር የሄድኩት።

ከጠበኩት በላይ ነው ያገኘሁት። የምወደው ዓይነት ሆና ነው ያገኘኋት። እንዲሁ አይተህ ምናምን አለ እይደል ታይፕህ የሆነ ሰው... እና ስሄድ ሙሉ ለሙሉ እሱን ነው ያገኘሁት... እኔ ነኝ ደግሞ ያሽኮረመምኳት... (...ሳቅ)

ኖር፦ አንቺ ነበርሽ ቀድመሽ ቦታው ላይ የደረሽው?

ሃኒ፦ አዋ

ጆይ፦ Normally እኔ ያለሁበት ከተማ መጣች። አላመንኩም ነበር። የምትመጣም አልመሰለኝም። ከነበረው ነገሮች አንፃር እና

መጣው ስትለኝ እኔ ብዙም ሳላምንበት ነበር የሄድኩት። ቁጭ ብላም አይደለም የጠበቀችኝ ከተማውን ስለማታውቅ የሆነ ቦታ ቆማ ነበር የጠበቀችኝ። እሰካያት ድረስ አላመንኩም ነበር። በጣም የሚገርምህ ነገር ያወራነው ነገር እንዳለ አሪፍ ሆኖ.. ምናልባት ካልሰራ ብላ ነው መሰለኝ የለበሰችው አለባበስ (...ሳቅ) ባላቃትም አላልፋትም ነበረ...

ኖር፡- አንቺ የምትወጂውን አለባበስ ነበረ የለበሰችው ነው?

ጆዬ፡- በጣም!! ካልሆነ ሁለተኛ አማራጭ ለመጠቀም ይመስለኛል... ሳቅ

ኖር፡- በፍቅር አብራችሁ ከሆናችሁ ምን ያህል ግዜ ሆናችሁ?

በህብረት፡- አምስት ዓመት

ጠያቂ፡- ወዲያው ነበር relationship የጀመራችሁት ወይስ ትንሽ ጊዜ ከቆያችሁ በኋላ ነው? ብዙ ግዜ ለምሳሌ ሶስት ወር አራት ወር ወይም ለአንድ አመት ምናምን ወጣ ገባ እያልን you know like serious የሆነ committed የሆነ relationship ሳይኖረን ይቆይና ከዛ የሆነ ሰዓት ላይ ይህ ነገር እየሰራ ነውና ለምንድነው ትክክለኛ relationship አድርገን ስም ሰጥተነው የማንቆየው አይነት ነገር እንላለን... so የእናንተ እንዴት ነበር ወዲያው ነው ስም የሰጣችሁት ወይስ ከቆይታ በኋላ ነው ለግንኙነታችሁ ስም የሰጣችሁ?

ጆዬ፡- ኦንላይን ማውራት ከጀመርን በኋላ ብዙም ሳይቆይ ነው ግንኙነታችን ወደ ፍቅር የተቀየረው። ወደ ፍቅር አይነት ወሬ ማለት ነው። ያኔም ኦንላይንም እያወራን ሳንገናኝ ለመገናኘት የፈለግንበት ምክንያትም ይሄው ነው። ለRelationship ነው እንጂ እንዲው ዝም ብለን እንተያይ ምናምን ብለን አይደለም የተገናኘነው። So almost ኦንላይን እያወራን ነው relationship ውስጥ መግባት የሚባለው ነገር የመጣው።

አሁን እኔ በግሌ ሰው በአካል ካላገኘው በስተቀር ኦንላይን ላይ ያለን ነገር አንዳንዴ እንደ እውነት consider አላደርግም። እሷን ያገኘኋት ቀን ግን እርግጠኛ ሆንኩ። መጀመሪያም ስናወራ የነበረ ነገር አለ በዛው ነው የቀጠለው... ማውራት ከጀመርንበት ግዜ ጀምሮ በቃ relationship vibe ነበረው።

ኖር፡- የሆነ stereotypes አለ አይደል የሊዝቢያን relationship እና gay relationship መካከል ብዙ ሰዎች አፋቸውን ሞልተው የሚናገሩት አንድ ነገር ሴቶች relationship ውስጥ ለመግባት በጣም ይፈጥናሉ። ወደ ጌይ relationship ጋር ስንመጣ ደግሞ አንዳንድ ግዜ ሁለት ዓመት አውቀሽው date እያደረጋችሁ acknowledge አይደረግም በጣም ብዙ ግዜ ይቆያል ከመወሰኑ በፊት እናንተ ጋር ግን ቶሎ ነው ሚጀመረው የሚባል ነገር አለ ። እውነት ነው?

ጆዬ፡- አዎ ትክክለኛ stereotypes ነው ብዬ ነው የማስበው። Mostly ሴቶች እንደመሆናችን ለፍቅር ልባችን ቅርብ ነው ብዬ ነው የማምነው። በተጨማሪም ደግሞ ያለውን ብዙ ነገር አልፈህ በዛ መልኩ አንድን ሰው ማየት ከጀመርክ በሌላ መንገድ entertain ማድረግ ይከብዳል፣ እና አብዛኛው ሴቶች የፍቅር ልብ ነው ያላቸው so yeah ትክክለኛ stereotypes ነው።

ኖር፡- አሁን ላይ አምስት ዓመት አብራችሁ ቆይታችኋል አንድ ከተማ መኖር ከጀመራችሁስ ምን ያህል ግዜ ሆናችሁ?

ሃኒ፡- አንድ ከተማ መኖር ከጀመርን ዓመት ከምናምን ያህል ይሆንናል። ቋሚ ስራ ላይ ከሆነች እና እዚ ከመጣች። ከዛ በፊት ያው የተለያየ ከተማ ነበርን። እሷም በሥራ ምክንያት ብዙ ቦታ ነበረች ከዛ ውጪ ያው በምትሄድበት እሄዳለሁ እመጣለሁ አይነት ነገር እንደዛ ነበር በፊት አሁን አመት ከምናምን አንድ ቦታ ነን።

ኖር፡- ከዚህ ጋር እያይዤ የምጠይቀው ነገር ልክ አብራችሁ አንድ ከተማ ላይ ስትሆኑ ብዙ ጊዜ አብሮ ማሳለፍ ይመጣል አይደል? በፊት ለምሳሌ በሁለትም በሶስት ሳምንትም ወይም በወር ከዛም በላይም ይሆናል የምትገናኙትና የተወሰነ ክፍተት ነበረው። አሁን ላይ ግን አንድ አከባቢ ወይም ከተማ ስትኖሩ በተደጋጋሚ መገናኘት፣ ብዙ ግዜን አብሮ ማሳለፍ እስከ አብሮ መኖር ይደርሳል እና ይህ ነገር ደግሞ ብዙ ግዜ የሰው ዓይንን ይስባል ማለትም ሁለት ሴቶች አብረው ሲኖሩ፣ ሲያድሩ፣ አብረው ሲገቡ እና ሲወጡ ምናምን የእኛ ማህበረሰብ ብዙ ጊዜ ሰዎችን በአይነ ቁራኛ መመልከት ነገር አለውና እሱን ነገር እንዴት ነው የምታሳልፉት ፍርሃት አለው ወይ? ይሄ የሰዎችን አይን የመፍራት ነገር አለ ወይ?

ጆዬ:- እንዳልከው የሚታወቅ ነው። አብዛኛው የእኛ ማህበረሰብ ዓይኑ ሰዉ ላይ ነው ያለው። ከእራሱ ነገር በላይ ማለት ነው እና ፍርሃት አለው በጣም አለው ወይ? አዎ! በጣም ያስፈራል almost everybody concerned የሆኑ ይመስልሃል። ደግሞም የመሆን ፕሮባብሊቲውም high ነው። እኔ አሁን እንደዚህ ደረሰብኝ የምለው ክፉት የምለው ቀጥታ የመጣብኝ አደጋ ወይም እስጊ ነገር የለም። ግን almost everyday እጅ ለእጅ ልትያያዝ ስትል ወይም ሰላም ልትባባል ስትል መፍራትህ አይቀርም።

አብረህ ስትኖር ደግሞ ሰዎች ይኖራሉ በዙሪያህ አብረው ባንተ ህይወት involve የሚያደርጉ ምንድነው ብለው ሊጠይቁህ የሚችሉ ይኖራሉ ይሄ ይሄ ደግሞ ያስፈራሃል። ምንም ቢሆን ይሄ ነገር እንዳያስነቃ almost act እያደረክ ነው everyday ህይወትህ ይሄ ነገር እንዳይታይብህ act እያደረክ ነው የምትኖረው ብዬ ነው የማስበው yeah ስለዚህ በጣም ፍርሃት አለው... ጨምሪለት እስኪ....

ሃኒ:- በጣም አለው! በተለይ ደግሞ femme እና femme ካልሆንክ አይነት ነገር አለው ለእይታ ራሱ የሚሰብ ነገር አለው። ሰው ራሱ ገፋ ብሎ መጠየቅ የሚፈልገው ነገር ይኖራል ምናምን ከዛ ውጪ እንደውም አብዛኞቹ ከሚያጋጥማቸው እንጻር እኛ እድሎች ነን ብዬ ነው የማስበው። አብዛኛው ሰው በመጥፎ ነገር አይረዳውም ለማወቅ ይሞክራል ምናምን ግን ብዙም አይገፋም ወደ እኛ... ብዙም ግልፅ አይደለም ይከብዳል እና እውነት ለመናገር ደስ የሚለው ምንድነው ትንሽም ቢሆን በእኛ እህቴ ናት የእክስቴ ልጅ ናት መባሉ ነው ያቀለዋል እንጂ ለእይታ የሚሰብ ነገር ሲኖር ይከብዳል እንደልብህ አትሆንም

ጆዬ:- ለእይታ የሚሰብ ነገር ማለት masculine presenting ሰው ሲኖር መጀመሪያም ጥያቄ ያስነሳል። ከዛ ደግሞ ከሆነ ሰው ጋር ስትሆን ወጣ ብለህ ትታያለህ። ምንም ያህል ብትደብቀው relationship ካለህ ሰው ጋር፣ ከምትወደው ሰው ጋር act ምታደርገውና ሌላ ቦታ act የምታደርገው ከፈገግታህ ጀምሮ ያስታውቃል። ሁኔታህ ጀስቸርህ፣ የሰውነት እንቅስቃሴህ ምናምን ያስታውቃል። ካዛን የሆነ obvious የሆነ ነገር አለ። ግን ደግሞ ፈርቶ መኖር ስለማይቀር ደስተኛ ሆነን እየኖርን ነው።

ኖር፦ የፍቅር አንደኛው ነገር እሱ ይመስለኛል አንዳንድ ግዜ እውር እንሆናለን አይደል? በጣም ስትወጂ አንዳንድ ግዜ በጣም ሪስክ ያላቸው በታዎች ላይ ራሱ act አለማድረግ አይቻልም። አንዳንድ ግዜ በጣም ከምትወጂው ሰው ጋር ስትሆኚ እጅሽ ወይም አይንሽ አያርፍም ብቻ የሆነ ነገርሽ አያርፍም እና እነሱን ነገሮች አንዳንድ ጊዜ መቆጣጠሩ ከባድ ይመስለኛል

ጆዬ፦ Yeah yeah, እኔም እሱን ነው ያልኩህ። የፈለገ ነገር ቢሆን act ብታደርግ ይህ ሰው አብሮህ ሲሆን እጁን መያዝ ትፈልጋለህ። እኛ በዚህ ጉዳይ ሁሌ እንደተወቀሰን ነው የእኛ relationship በጣም ነው በታክሲ ላለፈ ሰው ራሱ በጣም ነው የምታሳዉቁት የሚሉን ጓደኞቼ አሉን... እንዳለችው እሷ femme representing ነች እኔ ደግሞ masculine ነኝ እና የሰዎችን እይታ ይሰባል ለሰው እንደዚህ አይነት perspective ይሰጣል

ጠያቂ፦ የሚቀጥለውም ጥያቄዬ ይኼኛው ነበረ masculine and feminine ስለሚለው ነገር እና ነካ ነካ አድርጋችሁ አልፋቹታል ግን በደንብ እንድትመልሱልሰኝ ሁለታቹም የተለያየ self expression ነው ያላችሁ ጆይ አንቺን በድንብ አቅሻለዉ ሃኒ ደግሞ በተለያዩ በተቆራረጡ ፎቶዎች አይቻለሁ እና እስኪ ከምታስታውሱት ነገር ላይ በጣም መጥፎ የምትሉት አጋጣሚ እና or ደግሞ ራሳችሁን ለአደጋ ያመለጣችሁበት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ መጥፎ የምትሉት ማንኛውም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል masculine በሆነ representation የመጣ ወይ ደግሞ በጣም ጥሩ የምትሉት ነገር ካለ ምንድነው እሱን ነገር ማወቅ ብንችል

ጆዬ፦ መጥፎ ከሚለው ጥሩ ከሚለው ልጀምር... እኔ በጣም ይገርመኛል አጋጣሚ ነውና... የሆነ ጊዜ የሆኑ አባት ናቸው መንገድ ላይ ብር ምናምን ጠይቀውን በቃ እሺ ምናምን ብለን ስተናቸው እና ምርቃታቸው እንደ ሌላው ጊዜ እደጉ ምናምን አልነበረም of course አንቺ ብሎ ነው ያወራን እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንሄድ እያዩ ነበር... በቃ ተጋቡ ትዳር ይሁንላችሁ ለሰርጋችሁ ያብቃን ምናምን ብሎ መርቆናል... እና እንደዚህም አይነት አጋጣሚ አለ...

ግን ደግሞ ጥሩ ያልሆነ እይታ በጣም በብዛት ያለው እይታ

ነው... ሰው ምን ሊያስብ እንደሚችል ገፍቶ ባይመጣ እና boundary ገፍቶ ሌላ ነገር ባያደርስብህም እይታ አለው... አለፍ ሲል ደግሞ መንገድ ላይ የሆነ የለከፋ ነገሮች አንተ እንደዚህ አንተ ምናምን አይነት ነገር ባልሽ ነው የማለት አይነት ሙድ አለ በብዛት ግን ደግሞ personal lifeን እግዚአብሔር ይመስገን personal life አልፎ መቶ affect ያደረገ ነገር የለም ብዙም አላስታውስም... እስኪ አንቺ የሆነ ነገር በይው

ሃኒ፦ ብዙ የምጨምረው ነገር የለም። ትንሽ የማስታውሰው የሆነ ቅርብ ሰው የነበረች። እህትማማቾች እንደሆንን ነው የምታውቀውና የሆነ እላፊ የሚጠይቅ አይነት ሰው ነች። የሆነ አለ አይደል ሳይጠየቅ አስተያየት የሚሰጥ ሰው እንደዛ ነች። ፀጉሯን እንደዚ ብታደርግ እንደዛ ብታደርግ ታበዛለች። የሆነ እንደ ምክርም አይነት ነገር አድርጋ እንዲህ አድርጊላት እስኪ ትቀየር እያለች አላስፈላጊ የሚያስጠላ አስተያየት ትሰጣለች። የእምነትም ሰው ነች። የማስታውሰው ትንሽ ገፍቶ የመጣ ሰው እሷን ነው። ከዛ ውጪ ብዙ መጥፎ ነገር አላጋጠመንም። ለእይታ ምናምን መንገድ ላይ ደስ የሚል አስተያየት ይኖራል ግን ገፍቶ የመጣ የለም።

ጆይ፦ እኔ መጨመር የምፈልገው ከቤተሰብም አንዳንድ ደስ የማይሉ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ masculine ስትሆን ሰው የሚጠብቅህ ቦታ አለ በዚህ ደረጃ እንኳ መታሰብ ባይቻል የሆነ ዱሩዬ ምናምን ተደባዳቢ አድርጎ የማሰብ ነገር አለ። ይህ አመለካከት እንዳችን በእንዳችን personal life involve እንዳትሆን ይይዝሃል። እከሌ ብለህ ስታስተዋውቅ ግንኙነታችሁ ከየት ነው? አብራችሁ ነው የተማራችሁትን? ከየት ተገኛችሁ? የሚለው ነገሮችን መመለስ ቀላል አይደለም።

ኖር፦ ይገባኛል! በሴቶች በኩል ያለው ማህበረሰብ ለmasculine ሴቶች ያለው አመለካከት በእኛ ጋ ደግሞ በጣም feminine ለሆኑ ወንዶች ያለው ነገር ተመሳሳይ ይመስለኛል። ፌሚኒን የሆኑ ሴቶች ብዙም ዓይን ውስጥ አይገቡም አይደለ? ማስኩሊን የሆነች ሴት ነች ብዙ ግዜ ዓይን ውስጥ የምትገባው ለወንዶቹ ደግሞ ፌሚኒን የሆነ ወንድ ነው ብዙ ጊዜ attention የሚሰበው።

እሁን ደግሞ ወደ social media እና self expression

እንምጣ። ከ2023 ጀምሮ ጥላቻው እስከፊ ሆኗል። ሰዎች በቀላሉ ታርጌት ይደረጋሉ። ለእኛ ኮምዩኒቲ ደግሞ የከፋ ነው። ለምሳሌ እኔ አሁን ከጓደኞቼ ጋር መውጣት እስክተው ድረስ ያደረገኝ ነገር ነው። ስልክ የያዘ ሰው ሁሉ ነው የሚያስፈራኝ። አሁን ላይ ማንንም አላምንም። እናንተ ደግሞ relationship ውስጥ እንዳለ ሰው ይሄ ነገር ስጋት ላይ ይጥላችኋል ወይ?

ጆዬ፦ በጣም ነው የሚሰማን። እንዳንዴ በቀልድ cope up እድርገህ ታልፈዋለህ እንጂ ይህ በግንኙነታችን መሃል ያለ ትልቅ ስጋት ነው። አሁን ላይ እንደምታየው ቲክቶክ ላይ ሰውን ከጀርባው ቀርፀው እየለቀቁ ነው። ብዙ ነገር አለ። ያስጋል። ለግልም ሆነ ለሥራ ማህበራዊ ሚድያን መጠቀም ከባድ ነው ብዬ ነው የማስበው። እንተ ሃገር ሰላም ነው ብለህ ተኘተህ ጠዋት ስትነሳ እንደዚ እንደዛ ተብሎ በቃ ቃላቶቹ እንቺ እንደዚህ ተብሎ ኮሜንት ተደርጎ 12 ሰዓት ቆይቶ ልታየው ትችላለህ።

ማህበራዊ ሚድያ በጣም አስፈሪ ነው። የትም ቦታ ስትንቀሳቀስ target ልትሆን ትችላለህ። ፎቶህን ለጥፎ አንድ ቃል ጨምሮበት ቢለቅ ሰዉ እንደ መንጋ ከመቀበል ውጪ ወደ ኋላ የሚልበት ግዜ ላይ አይደለንም። እንዳልኩህ ደግሞ ይህ ሕይወቴ ነው። የሆነ ነገር ስለተፈጠረ እና ስላልተፈጠረ የሚቀር ነገር የለም። እየቀለድን በቃ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ ታደርጋለህ ግን ደግሞ ከማንነትህ የትም መሄድ ስለማትችል በተቻለ መጠን አደጋ እንዳለ ራሳችንን እያስታወስን ነው እየኖርን ያለነው።

ሃኒ፦ እውነት ለመናገር በጣም ያስፈራል! እሷ እንዳለችው እጅ ለእጅ መንገድ ላይ ተያይዘን ስንሄድ ሰው ካየን ያስፈራናል። አሁን አሁን ስልክ ይዞ የተቀመጠ ሰው ፊትለፊቴ ሳይ በጣም ተሳቅቄ ነው የማየው። ድንገት አታቅም የሆነ ሰዓት ላይ የምታደርገው ነገር ያመልጥሃል። በጣም ትስጋለህ ለማውራት እንኳ የሚከብድህ ሰዓት አለ። በተለይ ደግሞ እንደዚህ ግርግሮች ሲነሱ ፍለጠው ቁረጠው የሚል ሰው ሲበዛ በጣም ያስፈራል፣ በጣም ያሳቅቅሃል normal lifeህን እንኳ ለመኖር ያስፈራሃል።

ኖር፦ እህህ…

ጆይ፦ እዚ ላይ የምጨምርልህ ሌላው ነገር ሰው ባህሌ፣ ሃይማኖት ብሎ አይደለም የሚያደርገው። አድኖህ ለፌም ለማግኘት ግርግሩን ለመቀላቀል እራሱን ቫይራል ለማውጣት ነው የሚጠቀመው። አሁን ላይ ሰዉ ከአስተሳሰብህ ጋር የሚጋጭ ነገር ቢሆን አንዳንዴ አውርተህ ወይም ምን አገባኝ ብለህ የምትተወው ነገር አለ አሁን ግን እንደ ገቢ ምንጭ ነው የሚያዩህ የሆነ ብርቅዬ አራዊት አይነት ነገር…ሳቅ

ኖር፦ እውነት ነው። ይሄን አካሄድ በጣም በብዛት እያየነው ነው። ላለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት ተመሳሳይ ነገር ይመስለኛል። ሰዎች ሆን ብለው ነው ሰውን ለፌም እያደኑ ያሉት። ልክ ዝነኝነቱን ሲያገኙት እነሱ ይተዉታል የእኛ ህይወት ግን ይበላሻል።

ሃኒ፦ አዋ አዋ… እሱ ነው የሚከብደው

ኖር፦ የማህበራዊ ሚድያ ጥላቻ ሌላው ሚያስጠላው ነገር ደግሞ ራሳችንን መከላከል እንዳንችል ነው የምናደርገው። እኛ አይደለንም ከዛ በኋላ መልስ የምንሰጠው እኛ አንካተትም። ሰዎች ሲያወሩ ሄደን ሀሳብ የምንሰጥባቸው ቦታዎች ብዙ የለም ቢኖርም ሴፍ አይደለም። በዛ ላይ ፍርሃቱ አለ። ፍርሃታችንን አሸንፈን እንኳ እዛ ቦታ እንገኝ ቢባል አስገብቶ ሀሳባችንን የሚቀበል የሚሰማን ሰው የለም። የሆነ እጃችንን ታስረን ውሃ ውስጥ ተከቶ ግን ተንፍሱ እንደማለት ነውና አንዳንዴ እሱ part ትንሽ የሆነ አቅመቢስነት እንዲሰማን የሚያደርገው ነገር አለው መሰለኛ እዛ ቦታ ላይ ስንደርስ

ጆይ፦ በጥሩ ገልፀኸዋል ምንም ነገር ዲፌንድ ማድረግም አትችልም። ሁሉም ሰው ጠላትህ ነው ሊሆን የሚችለው። አስበው የተቀናበረ ነገር ቢለቀቅብህ? ስራ ቦታ አትል የት አትል ሁሉም ሰው homophobic ነው። የምትንቀሳቀስበት ቦታ ፋምሊ ጋር ወዴትም መሸሸጊያ አይኖርም። እንደዛም ብለህ የምታስረዳው ነገር አይደለም። ያልሆነ ሰው እንኳን ቢለጥፍህ ጀስቲፋይ ማድረግ የማይችልበት ሁኔታ ነው አሁን ላይ ያለው።

ሃኒ፦ እና ደግሞ ካንተ አይደለም መልስ የሚጠበቀው የሌሎች memers መጫወቻ ትሆናለህ። ይቀባበሉሃል እንጂ አልፎ መጥቶ አንተን check የሚያደርግህ ሰው የለም።

ኖር፦ አዎ የዳር ተመልካች ነው የሚያደርጉን። ጉዳዩ የእኔ ጉዳይ ነው ግን እኔ ዳር ተመልካች ነው የምሆነው። ሁሉም ሰው ያወራል እኔ ብቻ የማላወራበት ጉዳይ ነው የሚሆነው እና እሱ ፓርት ደሰ የማይል ነገር አለው። ኮንቨርሴሽን መክፈት ቢቻል ጥሩ ነበር ሰዎች እንዲያወሩበት እድል ቢሰጥ ጥሩ ነበረ ግን እዛጋም እንደርሰም።

አሁን ወደ ማገባደዱ እየሄድን ነው። ለእናንተ የመጨረሻ ጥያቄ የሚሆነው በተመሳሳይ ፆታ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ እንደ role model የምናያቸው ኢትዮጵያዊያን ብዙ ጊዜ በዙሪያችን የሉም ወይም ቢኖሩም በድብቅ ያለ ነገር ነው። ይሄ እኛ አውቀነው እነሱም በራቸውን ከፍተው የምናየው ብዙ ነገር የለም እና በእናንተ ግንኙነት ውስጥ እንደዚህ አይነት role model አለመኖራቸው ክፍተት ፈጥሯል ወይ? በግንኙነታችሁ የሆነ ዓመት ላይ ስትደርሱ እነ እንትናን አይተን ነው የምትሉት አለ? አምስት ዓመት በጣም ረጅም ግዜ ነው።

በግንኙነን ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመቶች የሃኒ ሙን ዓመታት ናቸው። መዋደድ ብቻውን በቂ ሊሆን ይችላል። ሦስተኛ ዓመት ጀምሮ ግን ከዛስ፣ ከዚህ ቀጥሎ ምንድነው ያለው የሚል የወደፊት ጥያቄ ይፈጥራል። እዚህ ጋር አንዳንዴ ፍቅር ብቻውን ለጥያቄዎቹ መልስ አይሆንም።

አንዳንድ ጊዜ future እንፈልጋለን ሰዎች ስለሆንን ከዚህስ በኋላ እንላለን ከዚህስ በኋላ ሲባል መልስ የለንም ወይም አይተነው እንደነ እንትና የምንለው ነገር የለምና ይሄ ነገር እንዴት ነው affect አላደረጋችሁም ወይ እስከ አሁን ድረስ ?

ጆይ፦ በጣም affect ያደርጋል በተለይ ደግሞ ገና ልጅ ሆነህ ስታየው ሀሉም የሆነ የhookup ነገር ነው ሚታይህ። የፍቅር ግንኙነቶች ቶሎ ሲሚያበቁ ታያለህ። አጠገብህ ብዙ ነገር አይቶ ብዙ የቆየ የፍቅር ግንኙነት አለማየትህ ምናልባት አይቻልም እንዴ ሁሉ እንድታሰብ ሊያደርግህ ይችላል። ለምንድነው ብዙ ሰው የፍቅር ግንኙነት ውስጥ እየገባ ይወጣል ለምንድነው ረጅም ግዜ ያስቆጠረ ግንኙነት የማላየወየ? የእኔም relationship ከዚህ የተለየ ነገር አይኖረውም የሚል ነገር ያመጣል።

ለዚህም ነው ሮል ሞዴል የሚያስፈልግ ነው ብዬ የማስበው። የተወሰነ ዓመት አብሮ የቆየ ሰው ሳይ በጣም ነው ደስተኛ የምሆነው። እንደውም አጋጣሚው ደርሶኝ ጎደኞች አፍርቻለሁ በrelationship ብዙ ግዜ አብረው የቆዩ። እኔ ልጅ ሆኜ ስፈልገው የነበረውን ነገር አሁን ላይ እኔ ለጓደኞቼ እያሳየው መሆኑ በራሱ በጣም ነው የሚያኮራኝ። እንደዛ አይነት model መሆናችን በጣም ነው ደስ የሚለኝ። ያው ክፍተት ለመሙላት ምናምን አይደለም የምንኖረው ላይፋችንን መኖራችን አይቀርም እሱ ምሳሌ መሆን መቻሉ ደስ ይላል።

በህይወታችን ያለው pressure ተደራራቢ ከመሆኑ የተነሳ እኛ ህይወት ላይ ያለው ነገር አብዛኛው ነገር workout አያደርግም። እንዳይሰራ የሚያደረገው የህይወት ምንነት ሳይሆን በቃ ትግላችን በጣም ተደራራቢ በመሆኑ ነው። ብዙ ነገር አለብን ከቤተሰብ ጫና አለብን፣ የራሳችን የህይወት ጥያቄ አለብን፣ ከማህብረሰብ ጋር ተቀላቅለህ መኖር እንኳ ይከብዳል። ብዙ ነገር ሰላለ ይሃን ነገር በብዛት ላታይ ትችላለህ ግን ደግሞ ብዙ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች አሁን ላይ አንድ ላይ ሆነው እየኖሩ እያየን ነው። ክፍተት መሙላት ባይባልም እኛም አንዱ እየሆንን ነው ብዬ አስባለሁ።

ኖር፦ እንዳይሰራ ከሚያደርገው ነገር አንዱ support system አለመኖሩ ይመስለኛል

ጆይ፦ በትክክል

ኖር፦ ለምሳሌ የአንቺ እና ሃኒ አብራችሁ ይህን ግንኙነት እንዲሰራ ለማድረግ ከማንም በላይ ሆነ ከምንም ነገር በላይ 100% የእናንተ ጥረት ብቻ ነው የሚሆነው። አዎ የጓደኞቻችሁ ጥረት ሊኖር ይችላል ግን ከዛ አያልፍም በሚሰጥር የተያዘ ነገር ስለሆነ። ነገር ግን የአንድ ሴት እና የአንድ ወንድ ጓደኛነት ወይም ፍቅረኛነት በቤተሰቦች፣ በእህት፣ በወንድም፣ በማህበረሰብ በቤተክርስቲያን፣ በቸርች፣ በመስጊድ በሃገር እና በሕግ ሳይቀር ድጋፍ ያገኛል።

ምንአልባት የኛ ግንኙነት ብዙ ግዜ ቶሎ የሚቋጨው፣ ስለማይሰራ ወይም ስለማንወድ ስለማናፈቅር ብቻ ሳይሆን

አንዳንድ ግዜ ምንም አይነት support system ስለሌለን ይሆናል። ምክንያቱም እኔ ከጓደኛዬ ጋር ያለን ነገር በጣም ሚስጥር ነው ከተለያየን በቃ በሬን ዘግቼ ነው የማለቅሰው እንጂ ሄጄ ለቤተሰቦቼ ተናግሬ ሽማግሌ ሰብስቤ አስታርቁኝ ማለት እንኳ አልችልም። ሁሉም ነገር ያለው በእኔ እና በእሱ መሃል ብቻ ነው። በእኔ እና በእሱ መሃል ያለው ነገር ካልሰራ አልሰራም ማለት ነው... አይነት ነገር ነው ያለው መሰለኝ በእኛ ኮሚኒቲ ውስጥ

ጃይ፦ አዎ ልክ ነህ የሚደግፍህ ምንም ነገር የለም። አብዛኛውን ሥራ የምትሰራው ራስህ ነህ። ሁልግዜ ብዙ ትግል አለ። አንተ ብትዘናጋ ተው ብሎ የሚመክርህ ምናልባት ዜጋ ጓደኞች አጠገብህ ካሉ እንጂ ምንም ነገር የለም። የሚመራህ የሚያማክርህ ሰው በዙሪያህ ብዙ የለም። ከቀጥም ሰው ጋር እንዳታወራ እዚ relationship ውስጥ እንደሆንክም አይታወቅም relationship አለህ እንዴ ልትባል ሁሉ ትችላለህ ነገሮችን በተለያየ perspective ማየት አትችልም ሙሉ ለሙሉ የራስህ ጥረት ነው የሚሆነው ለዛ ልክ ነህ... በጣም support system ወሳኝ ነገር ነው።

ኖር፦ እሺ በጣም እናመሰግናለን! ኢንተርቪውን በዚህ መጨረስ አልፈለኩም ተስፋችሁን ንገሩኝ እስኪ ምን ይታያቹሃል ከዚህ በኋላ

ጃይ፦ ድሮ አታስበውም ነበር። ከአምስት አስር ዓመት በፊት እንደዚ ኖሮኝ እንደዚህ ሰው አውቄ ጓደኛ ኖሮኝ የራሴ ህይወት ኖሮኝ ምናምን ብለህ በፍፁም አታስበውም። ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኜ አደርገዋለሁ ብለህ የምታስበው ነገር አልነበረም። በፍፁም የማይሳካ ነገር ነው ብለህ ነበር የምታስበው ግን አሁን ላይ ብዙ ሰዎች አውቀን ጥሩ ሰዎች አውቀን የራስህ ሕይወት መስርተህ እየኖርክ ነው።

ስለዚህ ያኔ በፊት ላይ ያሰብከው ነገር ከተሳካ አሁንም ሰፋ አድርገህ ብታስብ የመሳካት probability አለው ብዬ ነው የማስበው። ቢዘገይም Still አለን! እየኖርን ነው። ግን ደግሞ ወደፊት ነፃ ሆነን ከቤተሰብ ጋር ያለን ነገር ተስተካክሎ ማየት ይናፍቀኛል። አብዛኛው ሰው ከቤተሰብ ጋር ያለው

ነገር ነው የሚያስጨንቀው፣ ከቤተሰብ ጋር አስተዋውቀህ at least በጣም official ባይሆን የቅርብ የምትለው ሰው አሳውቀህ ኑሮዬ ብለህ መኖር ብትችል ቤተሰብ መመስረት ከፈለክ የተወሰነ ልጅም የምትፈልግ ከሆነ እንደልባችን ሆነን በመጠኑም በጣም የተጋነነ ነገር ማሰብ ልብ ሊሰብር ስለሚችል የራሳችን የምንላቸውን ሰዎች አውቀውልን እና አክብረውልን እንኖራለን ብዬ ነው የማስበው።

ኖር፦ ስለ ሃኒ እርግጠኛ ሆኜ መናገር ባልችልም ጃይ ግን ማህበራዊ ሚድያ ላይ እንቅስቃሴ ታደርጊያለሽ፣ ብዙ ሰዎችም ያውቁሻል ከእሱስ የምታገኙ support አለ ወይ? ከሥጋ ከቤተሰብ ያጣችሁትን ድጋፍ የምታገኙበት support system አለ ወይ? ከኛ ኮሚኒቲ ለእናንተ relationship ወይም ለማንኛውም relationship የሚሆን support system አለን ብላችሁ ታስባላችሁ?

ጃይ፦ የምንኖረው ህይወት ይታወቃል። አብዛኛውን ግዜ አንድ ላይ አትኖርም ከተለያየ ቦታ ነው የምትመጣው የሚያገናኝህ አንድ common ነገር ነው። ሌላ ህይወትህ ሁሉ የተለያየ ነው በጣም ጎን ለጎን ለመሆን የተወሰነ ነገር ይቀረናል ብዬ አስባለሁ። ግን የራሳችን የምንላቸው አብረው ቅዳሜ ተገናኝተህም ተዝናንተህ ተጫውተህ የምትሄዳቸው ጓደኞች አሉን። ይህ ማለት ብዙ ዓመት ከሚያስቆጥር ከሌላው ጓደኝነት ትልቅ ነገር ነው ብዬ ነው የማስበው። ራስህን ሆነህ ግልፅ ሆነህ ማውራት የምትችልበት ቦታ ማለት ትልቅ support system ነው ብዬ ነው የማስበው። ኮሚኒቲው ጥሩ ነገር ነው ያለው ብዬ ነው የማስበው። ጥሩ ይሰባሰባል ድራማው ቀንሷል የተወሰነ ማለት positive የሆነ energy ማለት አንተ የምትፈልገው ነገር አብዛኛው ሰው ያጣው እና የሚፈልገው ነገር ነው የሚሆነው እና ከኮሚኒቲው ጥሩ support system አለኝ ብዬ ነው የማስበው። እንደ ቤተሰብም እርኪ ባይሆንም የተወሰነ ነገር ይኖራል ግን ደግሞ ብዙም ተሰፋ ማድረግ አይቻልም... ጥሩ ነገር ነው ያለው አሁን ላይ... አንቺስ ምን ትያለሽ?

ሃኒ፦ አሁን ላይ አለ። እውነት ለመናገር እንዳለችው አጥጋቢ ባይሆንም አሁን ላይ ያሉን ጓደኞች የምናቃቸው በቅርባችን ያሉ ሰዎች እውነት ለመናገር መልካም ናቸው። የምርም ቁም

ነገረኛም የሆኑ ሰዎች በዙሪያችን አሉ።

ኖር፦ መልካም! የነበረን ቆይታ በጣም ደስ ይላል። በኔ በኩል ጥያቄዬን ጨርሻለሁ በእናንተ በኩል መካተት አለበት የምትሉት ነገር ካለ መድረኩን ልስጣችሁ።

ጆይ፦ በቂ ነው ብዬ ነው የማስበው። እኛም እናመሰግናለን።

...

...ፈገግታ የታከለበት ስንብት...



# The Weight of a Moment

**Anania T.**

(He/They)

Sometimes a single moment can define our lives. For Robel Hailu, one of the first openly gay Ethiopians, it is his participation in the Mr Gay World competition in 2012. He knows it too. A faint smile appears on his face as I mention that is the topic of our interview.

“Without acknowledging it, this competition has become the most relatable thing for many people,” he tells me. “Even though you feel like you have moved on, many people relate to this one thing.” His smile flickers between pride and unease, the expression of someone who knows both the cost and the power of that moment. Because sometimes, certain moments can be just as restrictive as they can be freeing.

“It’s also a reminder of how old I am,” he adds, jokingly.

I’ve known of Robel’s for years, through video snippets of the competition, vague memories of the controversy his participation caused in Ethiopia, and through his continued human rights advocacy work. Now, we speak over a video call, thousands of miles from each other, but connected through our collective experience of navigating life as a queer person in/from Ethiopia. For more than an hour, he recounts his journey: his childhood, his questions of identity and self-discovery, political awakening, and the choices that led him to Mr Gay World. Even through the emotional moments of our conversation, his expression remains warm, and his voice never falters.

“Before we get to the competition,” he says to me, “I have to give you some background. Otherwise, it wouldn’t make sense.”

Robel grew up in Addis Abeba, spending much of his childhood in the Ethiopian Orthodox Church, where he sang in the choir. As he grew older, he noticed the

quiet difference inside him, though he couldn't yet name it. It's something we are all too familiar with. The awareness of feeling different from those around us and the inability to fully articulate or understand its implications

"I knew I liked boys," he recalls. "But when I finally found the word for it, it was in the story of Sodom and Gomorrah. I used to fast and pray, I even went to monasteries to be healed from this 'sin.'"

The word healed hangs heavily between us.

Listening to him, I remember my own confusion, believing, like many other queer people, that I was the only one in the world who felt this way. That isolation was perhaps the hardest part, made worse by not having a frame of reference to see myself in. For someone coming of age in the late 2000s, the internet was my refuge. I think of those early days on Facebook, a world of torsos and cropped face profiles and usernames that read like code. A secret network shrouded in anonymity but built out of need.

For Robel, self-discovery came through television screens. "I remember seeing a news segment on 120 (*መቶ ሃያ*) about two men getting married in Mexico," he says. It wasn't positive coverage and was meant to shock the audience but had the opposite effect on him. He credits it as one of the points that allowed him to understand that it is possible to be and live as he is, albeit somewhere far away from home.

While entertainment shows served as an important moment of recognition, it was other programmes such as Yesetoch Admas (*የሴቶች አድማስ*) that contributed to his political awakening. He was enamoured by the work feminists and women's rights activists he saw on

TV. This was also during the 2005 (1997 EC) elections, when the country was going through a massive shift in its political landscape.

To be politically conscious means to recognise how our social, economic, and political systems influence the way we live. It's a way of seeing, caring and acting, one that leads to confronting several existential questions about ourselves and our surroundings. For Robel, poverty reduction campaigns and talking points during the election were the first triggers of these painful realisations.

"If the poor are treated as third-class citizens," he remembers thinking, "then queer people must be fourth or fifth."

*Or not at all,* I say to myself. I can't help but think on the appropriation of the term Zega as a code word to self identify by queer Ethiopians, and how it challenges the conception of citizenship and belonging.[1] But I digress.

After graduating from the university, Robel began working at a hospital, digitising paper-based patient records. He would once again be confronted with another painful truth: a dearth of data on the queer community's struggle with HIV and lack of access to essential care. "That was my wake-up call," he admits. "We weren't only pushed away socially; we were facing serious health risks."

One of the main challenges, he tells me, was the lack of condoms and lubricants. Sadly, a challenge that still persists today. Through small networks and gatherings, like the Laba community-centred events, he and a few friends started a peer group discussion about HIV

1 For more information about the origins of the term, check out *ታሪክ'* from Volume I of N'or

prevention. He smiles, remembering: “We didn’t have the word for it then, but it was basically peer groups.” The act of taking care of each other when the system that is designed to do so, fails you.

Not long after, he moved to South Africa to pursue graduate studies. There, he found something unfamiliar: *visibility*. Gay bars. Activist groups meeting in daylight. Queer churches. Even so, his desire to help people back home never waned, although he would at times be discouraged by local organisations’ lack of awareness on the lived realities of LGBTI+ communities in Ethiopia.

It was in South Africa that he stumbled upon the Mr Gay World competition, almost by accident, as it was taking place near his University. “One of the organisers asked, ‘why don’t you join? You can help people by creating visibility.’” He describes his hesitation, laughing softly. “This guy is crazy,” he remembers thinking and did not respond to much of the follow up messages he received urging him to sign up.

But then something happened that changed everything.

“One of my closest friends was discovered by his family,” Robel begins slowly. “Not sure if someone informed them or if they saw something on his computer. But they found out he was gay. I checked in with friends, but no one knew where he was.” He would later find out that his family took his friend to tesbel. When his friend came back months later, he was... a shell of himself. “He had bruises on his arms and legs. They had chained him so he wouldn’t run!”

He stops for a moment, breathing through the memory.

He was shocked how a family could do something like that to their own child. He recounts, with tears in his

eyes, telling his friend to fake it and do whatever he can to hold on until they could find a way to get him out of the country. A few days later, he would hear that his friend had taken his life.

“I still to this day can’t believe it,” he says, quietly wiping his tears. “I thought it was fake, a cruel joke”

LGBTI+ individuals across the world face disproportionately high risks of suicide. This is not necessarily because of sexual orientation or gender identity in and of itself but rather due to stigma and discrimination within society. Conversion therapy, in particular, remains among the most harmful practices. Often disguised as “healing,” it inflicts a deep psychological and spiritual trauma.

“That was a critical moment for me,” he says quietly. “And yes, I am in South Africa at least I have a right to speak about this..” He signed up for Mr Gay World soon after.

I can feel the emotional impact of discussing this sensitive topic on him, so I ask if he wants to pause the conversation for a moment. “No, I am good,” he responds. “I have not previously discussed this subject extensively, so it is genuinely a positive experience for me. I kept it for a while, but it needed to be told; it needed to be said.”

We resume our conversation, this time focusing on the pageant itself. I have often wondered what went on behind the scenes, what was going through his mind as he got ready for the competition, and how he navigated the space as one of the only two Black participants. I have wondered how he approached sharing the news with his family and if he was ever ready for the storm that would ensue as a result of his participation.

"I thought I'd have time to tell my family first," he explains, but his failure to read the terms and conditions on the sign-up form meant that the organisers announced his participation online before he could talk to them. He smiles, but the smile doesn't quite reach his eyes. "I'd clicked the box giving them consent to use my name and my photo from the moment I signed up." It's a shocking twist, one that gives me deeper insight into his story and puts my wondering to rest.

The truth is, you can never be prepared for your face to be plastered on social media, for your life to be reduced to a headline, and for your character to be scrutinised in public. Nobody can prepare you for the disintegration of relationships and family connections. But Robel isn't bitter. "I can't blame anyone," he says. "Sometimes life takes the choice out of your hands."

When I ask how he endured the aftermath, the disownment by his family, and the media scrutiny, and the feeling of loneliness in a foreign land, he doesn't hesitate in his answer. "My faith," he says simply. "Many people expected me to break, but my love for God is what kept me going." He tells me that he no longer subscribes to any institutionalized religion but that his relationship with God has not changed.

This is an important demonstration of how often queer people are pushed to disavow religion once we begin to question the contradictions that exist within it. Our identity is perceived as conflicting with culture or religion, making it difficult for us to embrace both our queerness and our beliefs simultaneously. But our relationship to God is personal, whether we call it faith or spirituality. Sometimes, the very thing that we are told rejects us can provide comfort and healing.

He remains cheerful as he speaks, even when the conversation turns to painful subjects. “My friends tell me that despite everything I have gone through, I am still laughing and maintaining a positive attitude,” he continues, answering my question before I even get to pose it. I find myself wondering how someone can hold so much grace and gentleness after enduring such pain. *How does he not grow bitter?* “What can being angry give me?” he asks, almost reading my thoughts.

As our conversation winds down, Robel’s energy lightens. We discuss his work on The Alen Show, an online space where he engages in insightful conversations with queer Ethiopians in and outside the country. This serves as a segue to discuss the complicated role social media is currently playing in shaping public dialogue on LGBTI+ issues in Ethiopia. TikTok, in particular, has been instrumental in both creating visibility and causing harm to our community. I ask how he navigates the space.

“There are people who come online just to insult me,” he answers, “but there are also people who listen and who ask questions.” He emphasises the importance of meeting people where they are and understands that the ordinary Ethiopian struggles to grasp the nuanced concepts of identity and sexuality. He approaches that gap with patience, offering education without judgement. While there is a warmth to him, however, beneath that gentleness lies a quiet determination, a resolve never to let openness be mistaken for submission nor kindness to mean tolerating disrespect.

By the end of our conversation, I’m filled with so much joy and gratitude. I feel closer to him, seeing my own personal story mirrored in his. Most of all, I’m reminded that a single moment carries multitudes but it doesn’t stand on its own. Our life experiences make up our

lifeworld and shapes who we are.

A moment in our life may at times feel heavy, but the trick is to not let it weigh us down.

***This article provides a summarized version of a discussion with Robel Hailu. The complete conversation can be found in the next page of this issue.***



# የልብ ለልብ ወግ፦ ከሮቤል ሃይሉ ጋር

(አንተ/ እሱ)

ኖር:- ሮቤል ስለመጣህ በጣም ደስ ብሎናል

ሮቤል፦እንኳን ደና ቆያችሁኝ

ኖር:- እንግዲህ በዚህኛው እትም ጭብጥ ያደረግነው reflection ላይ ነዉ። ያም ማለት እስከ አሁን ድረስ ባወጣናቸው እትሞች ላይ ባነሳናቸው ጉዳዮች ላይ reflect ማድረግ እና ደግሞ አስፈላጊ ናቸው ብለን ባሰብንባችገው ጉዳዮች እንዲሁም ሰዎችን ብናወራቸው ብለን ባሰብናቸው ጉዳይ ላይ ሃሳብ ማንፀባረቅ ፈልገናል። በተለየ ግን ካንተ ጋር ዛሬ ማውራት ከምንፈልጋቸው ርዕሶች አንዱ Mr gay world pageant ላይ ስለነበረህ ተሳትፎ እና ቆይታ ነዉ። እናም for particular reason to know more...በ queer movement ላይ የተላያዩ research እንደመሰራቴ መጠን ያንተንም pageant ላይ መሳተፍ በደንብ አውቃለሁ። እንዲሁም ያ ጉዳይ አሉታዊ ተስትኖዎችም እንድነበሩት፣ ከ ቤተሰቦችህም ex-communicated ሆነህ እንደነበርና ሌሎችም ችግሮች እንደገጠሙህ ለሌሎች ታሪክህን ስታጋራ ሰምቻለሁ። የህይወት ታሪክህ ትልቁ አካል እንደሆነም አምናለሁ፣ ግን እኔ personally ለማወቅ የጓጓሁት emotional side of the pageant እና ልምዶችህን ነው። I am not sure if I am explaining myself clearly, ተረድተኸኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እናም በዚሁ እያይዤ ምናልባት አንዳንድ ጥያቄዎቼ ምቾት ይስጡታል ወይ የሚለዉን እርግጠኛ ልሁን ብዬ ነው።

ሮቤል:-yeah it makes sense ……እናም በመሃል መመለስ የማልፈልገው ጥያቄ ካለ ነግርሃለሁ.... የ ኢትዮጵያዊ ይሉኝታ ከተወኝ ቆይቷል አትጨነቅ።

ኖር:- የመጀመሪያ ጥያቄዬ የሚሆነው ስለዛ ጊዜ ስታስብ ምን ይሰማሃል የሚለው ነው። አሁን ለምሳሌ ቅድም ስለ pageant ነዉ የምናወራው ስልህ ፈገግ አልክ፣ ስለ ዉድድሩ ስታስብ አይምሮህ ዉስጥ ሚመጣው የመጀመሪያዉ ነገር ምንድነው?

ሮቤል:-ያሳቀኝ ነገር ምንድው መሰለህ ሁሌ የቁንጅና ዉድድር በተነሳ ቁጥር ይህ ነገር ሳላውቀው የማንነቴ አንዱ አካል ሆኗል። አንዳንዴ አንድን ነገር አርገህ You don’t acknowledge

አይደል መሆኑን? አድርገኸዋል ግን but it has been a while፤ አንተ ወደሌላ የህይዎት ምዕራፍ ተሸጋግረሃል ሰዎች ግን አሁንም relate የሚያደርጉት፣ የሚያሰቡት፣ የሆነ ነገር የሚያስታውሱት እዛው ቦታ ላይ ቆመው ነው እና አንዱ ፈገግ ያሰባለኛ እሱ ነው።

ሌላው በሰበቡ ላሰቃቹ እንዴት እደምትፅፉት አላቅም፣ its funny for me that ማርጀቴንም የማውቅበት  መንገድ ነው አሁን….(ሮቤል ረጅም ሳቅ ይሰቃል)።  ለምንድነው እሱን ያልኩት Tik Tok አካውንት ነበረኝ ግን እንደዚህ active ሆኜ መግባት አልጀመርኩም ነበር የጀመርኩትም በ pride ጉዳይ ላይ ነበረና… there was one child..child ብለው ይቀላል 21 አመቱ ነበር። እናም “እዚህ ሰለመጣህ  ፖሰት ማድረግ ሰለጀመርክ thank you” ብሎ መልዕክት ፃፈለኝ። አክሎም ሀበሻ እንደሆነና እዚህ ከ ኢትዮጵያዊ እናት እና አባት እንደተወለደ ነገረኝ። ብቻ we texted back and forth እናም ከዛ “ለመጀመሪያ ጊዜ አንተን ያየውህ የቁንጅና ውድድሩ ላይ ነው፣ እኛ ቤት ሲወራ እክሰቴ ሰታወራው  የሰማውት በጣም ትንሽ ልጅ ነበርኩ” አለኝ። what do you mean ትንሽ ልጅ ነበርኩኝ (ረዘም ያለ ሳቅ....) I think he was 10-11 like that ትንሽ ልጅ ነበር እና ለራሴ wow አልኩ እና እና አሁን ሰንት አመትህ ነው? ሰለው 21 አመቴ ነው አለኝ። I was like በጣም አርጅቻለሁ ማለት ነው በቃ አልኩኝ!  ማለትም እሱ በዛ እድሜ የሚያሰታውሰው ነገር ለእኔ አሁን ሩቅ ነው ሀያ ቤቶች ውሰጥ ሆኜ ያደረኩት ነገር ነው እና አሁን እዚ ላይ መድረሴ  ከወጣት ሮቤል ወደ አቶ/ጋሼ ሮቤል ላይ እየደረሰኩ ነው የሚለውን ነገር አሰታወሰኛና  በጣም ጋሸነቴ ዘመን ዛሬም ይህ pageant እንደ አንድ ጉዳይ መነሳቱ ሌላኛው የፈገግታዬ ምክንያት ነው።

ኖር:- ሌላኛው ጥያቄዬ፣ ውድድሩን ለመሳተፍ የወሰንከው ዉሳኔ እንዳለ ሆኖ ውድድሩም ያንተን ህይወት በሆነ መልኩ የለወጠና ላንተም ትልቅ ትርጉም ያለው ነው ብዬ አሰባለሁ። And without you realizing it, it has changed a lot of people’s life, perceptions about themselves and their experiences.... Of course ከዛም በላይ የሆኑ ብዙ ሰራዎችን ሰርተሃል እናም አሁንም ብዙ ሰራዎችን እየሰራህ እንደሆነ አውቃለሁ። አሁን ላይ የተላዩ ሰራዎችን ትሰራለህ በ

queer ጉዳይ ላይ አክቲቪስት ነህ ነገር ግን በውነቱ ያ ውድድር ታሪካዊ እና pivotal point ነበር ብዬ አምናለሁ። አሁን እኔን ብትወስደኝ ገና ፌስቡክ መጠቀም በጀምርኩበት እንዲሁም teenager እና ገና ከማንነቴ ጋር እየተዋወኩ በነበረበት ወቅት ነው ያንተን ታሪክ የሰማሁት። በርገጥ facebook ላይ የሌሎችም ሰዎች ታሪክ ቢኖርም at that time I saw myself reflected through your story። Actually it’s a testament on how special that time was and that moment is for a lot of people till this day. And you know people do reference that. እና ወደ ጥያቄዬ ስመለስ እንዴት ለመሳተፍ ወሰንክ?

ሮቤል:- አጠር ያለ ሳቅ ከሳቀ በኋላ.... how do i decide? How የሚለው ላይ ከመግባታችን በፊት context እንዲኖረዉና ስሜት ይሰጥ ዘንድ I need to give you some background። ኢትዮጵያ ዉስጥ ተወልዶ ከማደግም ባሻገር፣ ያደኩት በጣም ሃይማኖትን የሚያጠብቅ ቤተሰብ ዉስጥ ነው። እኔም እንዲሁ በጣም ሃይማኖተኛ እና ወግ አጥባቂ እንዲሁም በ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ያደኩኝ ዘማሪ ነበርኩኝ። ሁሉ ነገሬ ከ እግዚአብሔር ጋር የተገናኘ መልሶ ደግሞ እራስን በመፈለግ ሂደት ዉስጥ የማንነት (identity) ጉዳይ ደግሞ ሁሌ የሚያስጨንቀኝ ሰው ነበርኩ። ስለዚህ በፆም፣ በፀሎት፣ በስግደት፣ ገዳም በመግባት እድናለሁ ብዬ እሰብ ነበር። ይህ እየሆነ ታድያ ጥሌ ከሰው ጋር ሳይሆን ከ ፈጣሪ ጋር መሆን ጀመረ። ገና ልጅ እያለሁ ወንድ እንደምወድ አውቃለሁ፣ ነገር ግን የሆነ እድሜ ላይ ስትደርስ ስለ ሰዶም እና ገሞራ ታሪክ መስማት ትጀምራለህ፣ እነሱም ሰዶም እና ገሞራ ቀጥታ ወንድን ከመውደድ ጋር የተገናኘ ኃጢያት ነው ብለው ያሳምኑሃል።

ከዛም ከቤተሰብ ጋር የነበረኝ በጣም ጥብቅ የሆነ ግኑኝነት ጥያቄ ዉስጥ ይገባ ጀመር። ይህን ብነግራቸው አደጋ ላይ ይጥለኛል ብዬ ስላሰብኩ አሁን ሳስበው ለራሴም የሚገርመኝን ዉሳኔ ወሰንኩ፣ እሱም avoid ማድረግና ስሜቴን አለማዳመጥ ነበር። ከዛ እድሜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ነው የምጣላው። ለሰዎች አልነግራቸውም። ኢትዮጵያ ዉስጥ ይህ አይነት ስሜት የሚሰማው ብቸኛው ሰው ነኝ ብዬ አስብ ነበር። እና በዛ ትንሽ

በነበርኩበት እድሜዬ መፍትሄ ነው ብዬ የማስበው ሁሌም ከኢትዮጵያ መውጣትን ነበር።

አሁን credit ልስጣቸው፣ የምታስታውሱ ከሆነ 120 ዜና ላይ የግርምት ዜና ተብሎ ሜክሲኮ ዉስጥ እና ሌሎችም አገሮች ላይ ወንዶች ተጋቡ ተብሎ ይቀርብ ነበር። Obviously I was excited ግን ዘመዶቼ ጉድ ነው ሲሉ እሰማለሁ፣ ለኔ ግን it is possible ብቻዬን አይደለሁም ብዬ እንዳስብ አደረገኝ። እንደዛም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ውስጥ እኔ ብቻ የሆንኩ ነው የሚመስለኝ የነበረው። so long story short የእራሴን identity ካወኩ እና this is who I am ካልኩ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ጓደኞች የማፍራት ዕድል አገኘሁ።

አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆኜ ነው በትክክል ከሰዎች ጋር link ማድረግ የጀመርኩት እናም campus ገብቼ ነበር ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያገኘሁት። ይመስለኛል campus ከመግባቴ በፊት 1997 ምርጫ ነበረ አስራ ሁለተኛ ክፍል ሆኜ፣ ታዲያ ለምን ድሮ ላይ እንደማይ አሁን ብትጠይቁኝ ምክንያቱን አላውቅም ግን ማየቴ በጣም ጠቅሞኛል ብዬ የማስበዉን እንደ ፋና ወጊ ብዬ ከማሰባቸው በነ ወ/ሪት መዓዛ ስለ ሴቶች ጉዳይ እና ህግ ሲወራ፣ የነ ካሚላ ታሪክ፣ የነ ሄርሜላ ታሪክ እናም የሴቶች እድማስ ላይ የምሰማቸው ጉድ የሚያሰብሉ ታሪኮች እንዲህም ይደረጋል ብዬ እያሰብኩ ያስገርሙኝ ነበር። ከዛም 97 ምርጫ ሲመጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ፖሊቲካ debate መስማት ጀመርኩ። ነገር ግን politically ብዙ ጥያቄዎች ያድሩብኛል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር።

በዛ ወቅት በነበረው ክርክር ላይ ደሃው ሰው የሀገሪቱ ሶስተኛ ዜጋ ነው ብለው ሲያወሩ ሰማው እና ድሃው ሰው ሶስተኛው ዜጋ ከሆነ ኩዊር ሰው አራተኛው ወይም አምስተኛ ነን we are in trouble እያልኩ ምናምን አሁን እዚህ ላሉት ያኔ እዛ(ኢትዮጲያ) አብረን ለነበርኳቸው ጓደኞቼ አወራቸው ነበር።

ለምንድነው ግን ሀገሬ ላይ እኔ ከምወደው ሰው ተፋቅሬ ሁለታችንም ተስማምተን እና እድሜያችን ከአስራ ስምንት አመት በላይ ሆኖን ፈቅደን ለተዋደድነው ለምንድነው ህገወጥ የሆነው? በተለይም ክርስቲያን ነኝ ለምትል ሀገር ሰዎችን

መበደል፣ ሰዎችን መጨቆን፣ ሰዎችን መግፋት መደብደብ እንዴት ልክ ሊሆን ቻለ? እያልኩ በግርምት እራሴን እጠይቀው ጀመር። It's not fair! እላለሁ።

እግዚአብሔርን እኔ እኔን መሆኔ ስህተት ነው አይደለም እያልኩ እጠይቀዋለሁ። እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ ጥያቄዎቼ ነበሩ።

ከዛ ለኔ pivotal moment የምለው ተመርቄ ከወጣሁ በኋላ አንድ ድርጅት ውስጥ ስራ ተቀጥሬ ገብቼ ነበር። እዛም ገብቼ የነበረው HIV/AIDS ፕሮግራማቸው ላይ database assistant በመሆን ነበር። በመሰረታዊነት ሲሰተማቸው ምንድነው የ ኤች አይ ቪ መድሃኒት ኢትዮጵያ ውስጥ ይሰጣል እናም ስራው የነበረው በወረቀት የሚሰሩ የታካሚዎችን data ወደ ኮፕምዩተር መቀየር ነበር።

ይህን እያደረግን በወቅቱ ያስደነገጡኝን ዳታዎች ማየት ጀመርኩ። ያው ወደ ኮምፒዩተር ከመዘዋወሩ በፊት የታካሚዎች ፋይል ካርድ ክፍል ስለሆነ ይቀመጥ የነበረው አቀማመጡ ጥንቃቄ የጎደለው እንደመሆኑ መጠን ብዙ የሰዎችን ፋይል ከነ ፎቶዋቸው እመለከት ነበር።

ብቻ ታሪኩን ሳሳጥረው ብዙ የእኛን ማህበረሰብ ሰዎች ለማየት በቃው። በተለይ አንድ ሆስፒታል ስሰራ መድሃኒት የሚወሰዱበት ቢሮ እና እኛ የምንሰራበት አጠገብ ለአጠገብ ነበረ ጠዋት ማታ ለስራ ሰወጣ ሰገባ የማቃቸው ዜጎች መተው medication ሲወሰዱ አየሁ። እናም I was asking myself do people know about this? አንድ የማውቀው ሰው ነበረና relationship ላይ ነበረ I was wondering do people know about this person እሱ ቢናገር ሰዎችስ ይቀበሉታል ወይ የሚለው ነገር አለኚ.... on top of that አጠገቡ ላለው ሰውስ ምን ያህል እየተጠነቀቀ ነው? የሚለው ጥያቄ አሳደረብኝ።

የእኛ ኮሚኒቲ relationship ደግሞ binary tree (ትንሽ ስለሆነ) አንድ ሰው ገባ ማለት ሌላው ጋር ቶሎ ሊደርስ የሚችልበት ዕድል በጣም ሰፊ ነው። እናም ለመጀመሪያ ጊዜ አለቃዬን ለኢትዮጵያ ኩዊር ሰዎች lubricant (ማለስለሻ)፣ ኮንዶም የሚገኝበት እና ዶክተሮች ስለኤችአይቪ

የሚስተምሩበት መንገድ ይኖር ይሆን ብዬ ጠየኩት። እናም ትዝ ይለኛል ይህን ስጠይቀው “you came out to me” አለኝ። እኔ በዛ ጊዜ coming out ምን እንደነበረ አላውቅም። አሜሪካዊ ስለነበረ ይመስለኛል ዝምብዬ የነገርኩት። እና በዛ ሰዓት ላይ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ከላባ ግሩፖች ጋር አወራሁኝ እና ዉሳኔ ላይ ደረስን። ዉሳኔውም ማህበረሰባችን የነበረው የተለያየ ግሩፕ እንደመኖሩ መጠን ሁሉም ግሩፕ መሪ አላቸው እና እነሱን ሰብሰበን ማውራት እና እንዴት መጠንቀቅ እንዳለባቸው ማስተማር ነበር።

በወቅቱ እንደ wake up call የሆነኝ የመጀመሪያው positive መሆኑን ያላወቅነው አንድ ዜጋ ወንድማችን ህልፈተ ሂዎት እንዲሁም ምንም የመንግሰት ጥበቃ አለመኖሩ እና ጉዳዩ በጣም dangerous መሆኑ ነበር። ስለዚህ ኩዊር ኮሚኒቲው በማህበረሰቡ መገፋቱ ብቻ ሳይሆን የጤና ጉዳይም ትልቁ ሪስክ ያለው ነገር እንደሆነ ተማርኩኝ። የመጀመሪያ ሰብሰባችንን ከየ ግሩፑ መሪዎች ጋር በመሆን ቦሌ አከባቢ አደረግን።

ከዛም እዛ ድርጅት ውስጥ ለ ሰድሰት ወር ከሰራሁ በኋላ ከ ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ መውጣት ነበረብኝ። እዛ ስሄድ I said to myself “okay so I started something there I have to continue that, I need to help my people out”. እዛ ላሉት ጓደኞቼ ከዚህ እንዴት ነው lubricant መላክ የምንችለው? እንዴት ነው ኮንደም መላክ የምንችለው? እንዴትስ ነው ማግኘት የሚቻለው? የሚለዉን navigate ማድረግ ጀመረኩ።

So I started navigating different LGBTQ+ organizations and everyone was looking at me like crazy. “Ohh there was two people from Ethiopia who came to attend meetings” ምናምን ይላሉ። ከኢትዮጵያ የመጡ አንድ ጌይ እና ሌዝቢያን የሆኑ ሰብሰባ ይገኛሉ ከማለት የዘለለ ስለ እኛ ምንም መረጃ አልነበራቸውም። So when I am saying I am gay the question “how do I know?” follows. Whenever I joined an LGBTQ+ organization what they used to say was “we never heard about you guys”።

በዛ ሰዓት ስለኛ ምንም አይነት መረጃ የለም። ስለኛ ምንም የሚያወሩ ድርጅቶች አልነበሩም። ስለ ኬንያ እና ዩጋንዳ እና ስለተወሰኑ ሌላ አፍሪካ ሀገሮች ግን መረጃዎች ነበሩ። መሪዎቻቸው በጣም bold ናቸው movement ሲያደርጉ። እኔም ለራሴ እንዲህ ነው ማደርገው ብዬ ቃል ገባሁ! እናም ስትታገል ተደብቀህ እንደማይሆንም ገባኝ "you are in closet and you are fighting for the closeted people, so who is gonna help you!? ብዬ እራሴን እንድጠይቅ ሆንኩኝ። ግን ደግሞ ኢትዮጵያ ተመለሼ መሄድ እፈልጋለሁ። እሱን እንዴት ሪስክ ላደርግ የሚለዉም ጥያቄም ነበር። ግን በንዲህ አይነት ጥያቄዎች ዉሰጥ እያለፍኩ ይህ አሁን ያለኝ ማንነቴ እየተገነባ መጣ።

ደቡብ አፍሪካ የሄድኩት በ 2011 በፈረንጆቹ አቆጣጠር ነበር እና በዚህ አይነት ዉጣ ዉረድ ዉስጥ ሆኜ ስድስት ሰባት ወር ሆነኝ። የተለያዩ ተቋማትን ስሞክር እኛ ደቡብ አፍሪካ እንጂ ምስራቅ አፍሪካን አንረዳም ይሉኛል። በተጨማሪም በዚህ አይነት ሁኔታም ልትቀርባቸው ስትሞክር ሰውቹም limited ይሆኑብሃል እና open up አያደርጉም ነበር። LGBTQ+ ድርጅቶች የሆነ አሳማኝ ታሪክ ከሌለህ አያምኑህም እና ትንሽ ተቸገርኩ። በምማርበት ትምህርት ቤት ግን LGBTQ+ Ally እና የራሱ የኮሚኒቲ ሰዎች ያሉበትን ስብሰብ attend አደርግ ነበረ እና እነሱም አንዳንድ information ያጋሩኝ ጀመር።

በፈረንጆቹቹ 2012 አካባቢ ይመስልኛል ፕሪቶሪያ ውስጥ Mr Gay South Africa ውድድር ነበራቸው። ውድድሩም የነበረው እኔ የምኖርበት ከተማ Pretoria ውስጥ ነበር እና እሱን የመመልከት ዕድል ገጠመኝ። ወድድሩን ስመለከት ግን አብዛኞቹ ተወዳዳሪዎች ነጮች ነበሩ። ካልተሳሳትኩኝ በዛ ሰዓት ከነበረው 12 ተወዳዳሪ አንድ ወይም ሁለት ጥቁር ነበር። So I said to myself "In this country, 90 percent of the population is Black or none whites, and many Black South Africans are also facing this issue?" This has become my learning curve.

ኢትዮጵያ እያለን የዛ አይነት መድሎዎችን አላየንም። የዛ አይነት አለም ላይ አልነበርንም። እኔ አዲስ አበባ ነው የተወለድኩት

እና ብዙ የዛ አይነት ነገር አላስታውስም። ከዛም የ Mr. GAY south Africa መስራች እንዲሁም የ አረብ ሃገራት እና የ አፍሪካ ተወካይ የነበረን ሰው በ Mr Gay World program ላይ ሌላ አፍሪካ ሀገሮች አይወዳደሩም ወይ ብዬ አወራሁት። ምክንያቱም ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ ውድድር አፍሪካ ውስጥ በደቡብ አፍሪካ አዘጋጅነት ሊዘጋጅ ነው። እሱም ይህን ስለው “ohh why don’t you join” አለኝ and I was like huh.... ሳቅ... አሁንም ደግሞ “you are good looking and it can also help people by getting visibility” አለኝ፣ በ ሆዴ “this guy is crazy” እያልኩ እሺ አሳውቅሃለሁ ብዬው ተመለሰኩኝ።

እናም ይህ በንዲህ እንዳለ ደቡብ አፍሪካ ኑሮዬ ብዙ ነገሮችን በነፃነት አደርግ ጀመር። መጀምርያም ሆን ብዬ ነው ማንም የቅርብ የምለው ሰው የሌለበትን ሀገር እና የ ጌይ መብት ሚከበርበትን ሀገር ስለፈለኩ ደቡብ አፍሪካን የመረጥኩት። በደንብ ነፃነት ኖሮኝ ጌይ ቸርች፣ ጌይ ክለብ መሄድ በመቻሌ ራሴን በደንብ ማስተማር እና ብዙ ነገሮችን ማወቅ ጀመርኩኝ። So long story short ውድድሩ ተመዝገቡ ምናምን እያሉ አራት አምስት ወር ነበራቸው፣ ያ ሰውዬ ደግሞ ብያወራኝም ምንም መልስ አልሰጠሁትም እናም ስለውድድሩ ምንም ለማድረግ አልወሰንኩም።

በዚህ መሃል ኢትዮጵያ እያለሁ የማቀው አንድ ዜጋ ጓደኛ ነበረኝ እኔ ስድስት ኪሎ ሰማር እሱ አራት ኪሎ ነበር የተማረው፣ ጥሩ ሥራ የነበረው እና በሰላም ህይወቱን ይኖር የነበረ ሰው ነው። ኋላ ግን ሰው ነግሯቸው ይሁን ኮምፒዩተሩን አይተው ባላውቅም ቤተሰቦቹ ዜጋ እንደሆነ አወቁ። እናም ቤተሰቦቹ ሥራ አስቁመው አንድ ቀን ብድግ አድርገው ካልተሳሳትኩኝ ፃድቃኔ ማርያም የሚባል ፀበል ወሰዱት። ፀበል ሊሄድ አንድ ቀን ሲቀርው ግን አውርቼዋለሁ Skype ላይ ...የድሮ ሰዎች መሆናችን የሚያሳውቅ ሌላ ነገር.....ሳቅ። ቀጣይ ግን ምንም ላገኘው አልቻልኩም የተወሰኑ ጓደኞቹንም ስጠይቅ ማንም የት እንደሄደ ሚነግረን ጠፋ። በጣም የቅርቤ ጓደኛዬ ስለነበር መጥፋቱ አስጨነቀኝ። በየ መሃሉ የራሴ ህይወት እየያዘኝም ቢሆን ቤተሰቦቹ ጋርም ብደውል ምንም መልስ አጣሁ።

ከሁለት ወር ምናምን በኋላ ከሰራተኛቸው ፀበል ወሰደውታል የሚል ወሬ ሰማን። ታሞ ይሁን ምን ሆኖ እንደሄደ ግን አሁንም ምንም ልናውቅ አልቻልንም። ከዛም ይመስለኛል ከ 3 ወይ ከ 4 ወር በኋላ ተመለሰ... እንዴት ብዬ እንደምነግራቹሁ አላውቅም ያ ረጅም ሎጋ እጅግ መልከ መልካም የነበረው ልጅ ሲመለስ ጥቁር ጥላሸት መስሎ ነበር የተመለሰው። የማልረሳው በሰንሰለት አስረውት ነበር ሲያስጠምቁት እንዳይጠፋ እያሉ እናም እጁና እግሩ በልዟል በመታሰሩ እና በመታገል ብዛት። የዛን ቀን በ skype ያየሁትን ሰው መቼም አልረሳውም! ሌላ ሰው ሆኖ ነበር ያገኘሁት “are you okay?” ስለው “yes i’m fine” አለኝ።

እዛ የነበረዉንም ሁኔታ ሲያስረዳኝ በሶስተኛው ወር ይሁን አራተኛ ወር ላይ ነው በቃ ሰይጣን ነኝ እወጣለሁ ምናምን ብሎ ማስመሰል ስለነበረበት ያንን አይነት ድራማ ሰርቶ ነው እምነው የለቀቁት። ሌሎች ተጠማቂዎች ሲያደርጉ አይቶ እራሱን ነፃ ለማድረግ ያደረገዉን ሲነግረኝ በቃ በጣም ተሰማኝ! የወለዱህ ቤተሰብህ ወንድም እህቶችህ በዛ ልክ ሊጎዱህ እንደሚችሉ ሳይ ዉስጤ በጣም አዘነ። ይህ ጓደኛዬ ደግሞ የት ይደርሳል የተባለ እጅግ በጣም ብሩህ አእምሮ ያለው ልጅ ነበር እና ይህን በመሰለ ሰው ላይ ያን አይነት ጭካኔ እንዴት ይደረጋል ብዬ በጣም ተሰማኝ። በቃ እጁን እና እግሩን ሲያሳየኝ በጣም ተጎድቶ ስለነበር መልሶ ያገግማል ብዬ ለማመንም ከበደኝ። “እይዞህ ፀልይ ደህና ትሆናለህ ግን ከዛ ሀገር መውጣት ስላለብህ ስኮላርሺፕ ምናምን ሞክር እኔም እዚህ እፈልግልሃለሁ አልኩት፣ አሁን ላይ ግን ያምኑህ ዘንድ ያሉህን አድርግ የሴት ፍቅረኛ መያዝ ሚኖርብህ ከሆነም ያዝ እና እንደምንም አስመስለህ እራስህን ጠብቅ አልኩት።

ያው መቼም እኛ አለም ላይ ስንኖር ፊልም ሰርተን ነው እየዋሸን ነው የኖርነው። እናም እሱንም ይህ ቀን እስኪያልፍ አስመስል girlfriend ያዝ ካሉህም  አይናቸዉን ካንተ ላይ እንዲያነሱ ከረዳህ አደርገው። እይዞህ በርታ አልኩት። እሱም አንተም በርታ ጠንክር አለኝ እና የመጨረሻው የማስታውሰው ንግግራቺን እሱ ነበር። በቀጣዩ ቀን ክላስ ገባሁ እና በሁለተኛው ወይ በሶስተኛው ቀን  አንድ ኃደኛችን ፌስቡክ ሜሴንጀር ላይ “ሮቢ ወደ ቤት እንደተመለስክ ንግረኝ የምነግርህ ነገር አለ” የሚል መልዕክት

ደረሰኝ። ከዛ እሺ አልኩና ቤት ገብቼ ደወልኩለት ከዛም ጓደኞችን እራሱን እንዳጠፋ ነገረኝ! ውሸት ነበር የመሰለኝ! ዛሬም ድረስ እውነት አይመስለኝም! ግን የሆነው እውነት ነበር አርፏል በቃ!። ደጋግሜ ኡህህ አምላኬ አልኩኝ በጣም ሃዘን ዋጠኝ!። እናም ይህ ነበር ሌላኛው እና ትልቁ critical moment የነበረው ለእኔ፣ ስለዚህ ጉዳይ ካላወራን እና እራሳችንን ካልረዳን አይኔ እያየ ብዙዎቻችን ትያይዘን እንሞታለን አልኩኝ።

And yes, I am in South Africa at least I have a right to speak about this... የቅርብ ጓደኛዬ እራሱን ሲያጠፋ እያየሁ፣ ድሮ እንዲህ ተደርጎ ነበር... የሆነ ሰው እራሱን አጠፋ... እየተባለ ሲወራ የሚሰማው ታሪክ አሁን ደጄፌ ድረስ ደርሶ የገዛ ጓደኛዬ እራሱን ሲያጠፋ ሳይ እኔ ድምፅ ካልሆንኩ ማን ድምፅ ሊሆን ነው? ስለዚህ እኔ ይህን ማድረግ ይኖርብኛል ብዬ ወሰንኩኝ።

እኔ ፈቅጄ ጌይ አልሆንኩም! ጌይ መሆኔም ኢትዮጵያዊ ከመሆኔ ምንም የሚያሳንሰኝ ነገር የለውም።

ከእግዚአብሔር የሚያርቀኝ ነገር አይደለም። እናም “I need to talk to these people about this issue” ብዬ አሰብኩኝ። የሆነ ነገር ማድረግ ይኖርብኛል አልኩኝና ያ ሰውዬ የላከልኝን ማስታወቂያ ደግሜ አየሁት። “You know what I’m gonna do it I’m going to register so that I can create an awareness” አልኩት።

ከዛም February ላይ እሁድ ቀን ተመዘገብኩ። ውድድሩ ይደረግ የነበረው May ላይ ስለነበር ከቤተሰቦቼ ጋር ለማውራት 3 ወር አለኝ ብዬ አሰብኩ። Mr gay World እንደዛ ነው እንግዲህ join ያደረኩት። At least I need to create visibility, I need to fight and I need to tell my friends story ብዬ አስቤ ነው።

ይህ ሲሆን ግን የጓደኛዬን ታሪክ ለማንም የነገርኩ አይመስለኝም። ምክንያቱም ነገሮች እስኪረጋጉ ቢወራ ጥሩ አይሆንም ብዬ ስላሰብኩ ቤተሰቦቹ ሰላም እስኪሆኑ ድረስ መናገር እንደማልችል ተሰማኝ።

ግን በመሃል ምን ተፈጠረ  መሰልህ የልጅነት ነገር! በወቅቱ terms and conditions ሚባል ነገር አለ ታዲያ እኔ በዛን ወቅት መመዝገቤን እንጂ ፎቶዬን እና ስሜን publicly እንዲጠቀሙ ፍቃድ የሰጠሁ አልመሰለኝም ነበር። በዚህም ምክንያት ጉዳዩ በደንብ ጎልቶ እንዲወጣና out of my control ሆኖ ብዙ ሰዎች ጋር እንዲደርስ ሆነ ማለት ነው። እና ወድድሩን የተቀላቀልኩበት ጉዞዬ ይህን ይመስላል እንግዲህ።

ኖር:- Thank you so much for sharing!. ይህን ታሪክ ማጋራት በራሱ በወቅቱ የነበረዉን ሃዘን እና ክብደቱን መልሶ መኖር ነው። በመሃል ትንሽ ፋታ መውሰድ ከፈለክ እንደዛ ማድረግ እንችላለን።

ሮቤል:- No I am good, አውርቼውም ስለማላቅ it's a good thing really, it needed to be told, it needed to be said. ሳላወራው የቆየሁትም ያው የሰዎችን መብት ከማክበርም አንፃር ነበር። ነገር ግን አሁን መነገር አለበት። ሰው ቢሰማው መልካም ነው ብዬ አምናለሁ። ኢትዮጵያም ይሁን ከኢትዮጵያ ዉጭ ያሉ ሰዎች ይህን ታሪክ ሲያነቡ ሰው በዚህም ልክ በገዛ ልጁ ላይ ሊጨክን እንደሚችል እንዲያውቁ እና እንዲማሩበትም ጭምር ነው የምፈልገው። ከኛ ኮሚኒት ዉጪ የሆኑ ሰዎችም ሲያነቡት በራስ ስህተት የገዛ ልጅህን ማጣትም እንዳለ እንዲያውቁ እና ከረፈደ ፀፀት ይድኑ ዘንድ ነው።

ኖር:- በጣም ልክ ነህ ዛሬም ድረስ ባንድም በሌላም መንገድ እየሆነ ያለ ጉዳይ ነው።  አሁን ሰያሜ አግኝተንለታል "conversion therapy" እንለዋለን እንጂ  በዛ ወቅትም የሆነው እራሱ conversion therapy ነው። ፀበል ወሰዶ ሰዎችን ከማንነታቸው ለመቀየር መሞከር ዛሬም ድረስ የሚደረግ ነገር ነው። ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ታሪኩን ማጋራትህ ትክክል ነው። ብዙ ሰዎች ሳይፈልጉ ከኢትዮጵያዊነታቸው፣ ከቤተሰባቸው እንዲሁም ከሃይማኖታቸው እና ከማንነታቸው መሃል አንዱን እንዲመርጡ ተገደዋል። እራሳቸዉን ሆኖ መኖር ምርጫ ሳይሆን ቀርቶ ተገደው እራሳቸዉን ሳይሆኑ እንዲኖሩ ሆነዋል። እኔ በዛ ወድድር ለመሳተፍ ምን እንዳነሳሳህ አላውቅም ነበር እና ታሪኩም  አጋርተኸን ምክንያትህን ማወቄ እንደው ምን አነሳሰቶት ይሆን ለሚለው ጥያቄዬ ምልስ  እንዳገኝ ረድቶኛል።

ሮቤል:-የሆነ ቅዳሜ ቀን ጠዋት ተነስቼ የወሰንኩት ነገር የሚመስላቸውም ጓደኞች አሉኝ (......ሳቅ)

ኖር:- Yeah but this is so powerful! እና ሌላው ቅድም ጠቅሰህ ያለፍከው ነገር ነበር፣ ቀድሞ ዉድድሩ ላይ የነበሩት ሁለት ጥቁሮች ብቻ ነበሩ ስትል ነበር እና አንተም ስትሳተፍ ደግሞ ከኢትዮጵያዊነትህም ተጨማሪ አፍሪካንም ጭምር ወክለህ ነው ብዬ አምናለሁ። በዛ ነጭ በበዛበት ወድድር ዉስጥ እንደ አንድ ጥቁር ኩዊር ግለሰብ የነበረህ ተሞክሮ እንዴት ነበር?

ሮቤል:-እኔ ሚመስለኝ ምን መሰለህ፣ እንደኛ ሰዎች በድብቅ ስለሚኖሩ እና ስለ እኛ የሚናገር ምንም ዶክመንት ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያ ዉስጥ ጌይ የለም ብሎ ለማውራት ይመቻቸዋል። ያ እንዳለ ሆኖ ከእኔ በፊት ብዙ እራሳቸዉን ተቀብለው out ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ጉዳዩ ሚዲያ ላይ ሲወጣ ለመጀምሪያ ጊዜ ሶስት ጥቁር አፍሪካውያን Mr. Gay world ላይ ተወዳደሩ መባሉ እኔ የመጀመሪያው ጌይ ኢትዮጵያዊ የሆንኩ አስመስለው እንዲያወሩ ዕድል ሰጣቸው።

እውነቱን ለመናገር በወቅቱ ምንም ሪሰርች አልሰራሁም ነበር። ከመጀመሪያ ጥቁር አፍሪካውያን አንዱ መሆኔንም አላውቅም ነበር። እንደኛ ልጅነትም አለ 24 ዓመቴ እንደመሆኑ መጠንም ይመስለኛል ብዙም እውቀት አልነበረኝም። ከዚህ በፊት ማን ተሳተፈ ምንስ ሆኖ ነበር የሚለዉን ለማየትም አላሰብኩም። ዜናው ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ጥቁር አፍሪካዊያን Mr.Gay world ላይ ተሳተፉ እንደኛው ዙምባቡዌ ፣ እንደኛው ናሚቢያ እና አንደኛው ኢትዮጵያዊ ይላል።

ከዛ ዙምባቤያዊው ከሃገሩ መንግስት ማስጠንቀቂያ ተሰጠው “ወድድሩን የማታቆም ከሆነ ቤተሰቦችህ ላይ አደጋ ይደርሳል” የሚል ማስጠንቀቂያ ከዙምባብዌ መንግሥት ደርሰው። በእኔ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ቤተሰቦቼ አከባቢ ሄደው የተጠየቁት ጥያቄዎች ምናምን ነበሩ። እናም ነገሮች ምን ያህል ከቁጥጥር ዉጪ እንደነበሩ በዚህም ማየት ትችላለህ።

ጌዮች ከውጪ ነው የመጡት? ጠጪ ናቸው፣ አጫሽ ናቸው የሚል narrative or stereotype ነበረ። የኔን ታሪክ ሲሰሙ

ደግሞ አልጠጣም፣ አላጨስም፣ ያደኩት ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው። ከነሱ narrative ጋር አልገጥም አላቸው። ብቻ ኢትዮጵያ የነበሩ ሰዎች እንዴ ልደታ ነው የተወለደው እዚ ነው እዛ እያሉ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንኳ ሳይኖራቸው  ዜና ላይ ወጣ ሬዲዮ ላይም ተነገረ። ያኔ ደቡብ አፍሪካ፣ ፕሪቶሪያ ነበር የምኖረው። ብዙ ኢትዮጲያውያን ያሉባት ከተማ ነች። ይህ ዜና እዛ መሰራጨቱ ደግሞ ለኔ ሌላ ስጋት ነበር። ምክንያቱም ቤተሰቦቼ ከሚሰሙበት ነገር ጋር deal የማደርገው ነገር እንዳለ ሆነ የዚህኛው መጨመር ደግሞ ጉዳዩን አባሰው።

ጌይ መሆን ከነጭነት ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም። ሁሉም የሰው ዘር ጌይ ሊሆን ይችላል ይህም እድል የመጣው አፍሪካ ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ በመደረጉ ብቻ ነው። በፊት የተደረገባቸው ሃገራት ፊሊፒንስ ወይም የአውሮፓ ሃገራት ምናምን ስለነበረ ነው። ከ 33 ሀገር ሰዎች ተወክለው ነበር የመጡት። ጥቁሮቹ ከሶስት ሁለት  ቀረን እኔ እና ናሚብያዊው ማለት ነው። ናሚቢያ በወቅቱ የኲዊውር ሰው መብት በህግ ደረጃ አልተፈቀደም ነበር።

ነገር ግን ናሚብያዊው ወዳጄ ሃገሩ ላይ ወድድር አድርጎ ተመርጦ ነው የመጣው። እነሱ ጋር ወድድሩ ተፈቅዶ ስለነበር ስለዚህ ብቸኛው አዲሱ ሰው እኔ ብቻ ነበርኩ። ደቡብ አፍሪካን የወከለው ልጅ ነጭ ነው he was one of the good friend I have.... Democratic alliance የሚባል የፖሊቲካ ድርጅት ተወካይ ነበር። እድሜው ልጅ ቢሆንም politically driven የሆነ ልጅ ነበር። እንዲሁም ቤተሰቦቹ ተቀብለዉት ነበር እና ነገሮች ለሱ ቀላል ነበሩ። ብቻ ትንሽ ከበድ የሚልም ነበር ምክንያቱም ጥቁር ሆኖ እዛጋ መገኘት በራሱ የራሱ challenge አለው። እንደገናም ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ሙሉ ጥቁር የኲዊር ማህበረሰብን እንድትወክል ትገደዳለህ! እናም አንዳንዴ ያንን ሁሉ መሰፈርት እሟልተህ በልብ ሙሉነት ነፃነት ተሰምቶህ ለማድረግ ትቸገራለህ።

አንድ የማልዋሽህ ነገር በወቅቱ “I don’t care about anything I will do me” ያልኩበትም ጊዜ ነበር። እኔ እራሴን ሆኜ ነው መወከል ያለብኝ ብዬ ወሰንኩት። ሀበሾችም እንዴት ኢትዮጵያዊያን ወከለ ምናምን ሲሉኝ I

am gay Ethiopian አልኩ እንጂ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ጌይ ነው አላልኩም ብዬ መለሰኩ። ብቻ tough ነበር። በርግጥ እንዳሁኑ ማህበራዊ ሚዲያዉም ስላልነበረ ሰዎች ባጠቃላይ በኩዊር ጉዳይም ሆነ በፖለቲካ ጉዳይ የነበራቸው ንቃት እና awareness አናሳ እንደመሆኑ ትንሽ ቀለል ቢልም፣ እንደዛም ሆኖ ግን እንደ ጥቁር ሰው እዛጋ መገኘት ግን በጣም tough ነበር። በሰዓቱ ውድድሩ ደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ላይ መሆኑ ጉዳዩ ብዙ ሰዎች ጋር ይደርሳል በሚል ብዙ ሰዎች በጣም ደስተኛ ነበሩ። Yeah, so it has a good side and bad side to it... ነገር ግን ውድድሩ ላይ you don't feel that ጥቁርነቴን የሚያስታውስህ ወይም ጥቁርነቴን ተንተርሶ የመጣ ምንም የደረሰብኝ ነገር አልነበረም።

እኔ ምንም ያየሁት ችግር አልነበረም። ያው የኔ ታሪክ ለየት ብሎም ስለመጣሁ ይሆናል ሁሉም ሰው መልካም አቀባበል ሲሰጠኝ ነበር። ደስተኛ እንድሆን እና ድጋፍ እንዳለኝ እንዲሰማኝ ነበር ሲያደርጉ የነበረው። ጥቁር ከመሆኔ ጋር ተያይዞ ወድድሩ ላይ ምንም የገጠመኝ መጥፎ ነገር አልነበረም።

ኖር:- ያው በተለይ በኛ ሀገር አፈ-ታሪኮች አሉ። ብዙ ግዜ ደግሞ እንደ አንድ ኩዊር ሰው ስለራሳችን የምናውቀው ሌሎች ሰዎች የሚነግሩንን ነገሮች ነው። ሁሉም የሚነገረን ነገር እና ስለራሳችን የምንሰማው ደግሞ መጥፎ ነው። ያንተ እዚህ ወድድር ላይ መሳተፍ ሲሰማ እና ታሪክህ ሲታወቅ ደግሞ ያንን narrative ይቃረናል። እንደገናም ወድድሩ story ቢኖረውም እንኳን የተገደበ እና እነሱ በሚፈልጉት መልኩ የተቀረፀ እንደመሆኑ አንተ የራስህ personal experience እንዳይኖርህ አርጓል ብዬ አምናለሁ። ለምሳሌ አንዱ headline "two gay Africans" yemilew neber! እናም ምን ልልህ ነው እንዳንዴ ሰዎች frame የሚያደርጉት እና የኛ የኑሮ ተሞክሮ ይለያያል፣ እናም mismatch ይፈጠራል። አንተ ይሄን አይነቱን ችግር እንዴት አስታርቀህ አለፍከው? አልከበደህም?

ሮቤል:-I think ከግላዊ መገለጫ ይልቅ የፓለቲካዊ ይዘት ነበረው። የእኛ እዛ ውድድር ላይ መሆን በተለይ እኔን በዜና አውታሮቻቸው አጥብቀው ይፈልጉኝ ነበር። ምክንያቱም ደቡብ አፍሪካ African Union መቀመጫ መሆን ትፈልግ ነበር። ከሰብዓዊ

ሙብት አንፃር ከአፍሪካ ህብረት ካፒታል ሃገር መምጣቴ “look at them. They aren’t representing all of Africa. They don’t acknowledge one of theirs. They can’t even protect one of theirs. Look at how his family is treating him. Nobody is protecting him” እያሉ ትልልቅ የፖለቲካ የዜና አውታሮች ሌላ በውስጥ ማውራት የፈለጉትን ፖለቲካ መጠቀሚያ እድርገውታል።

በዚህ ሁሉ መሃል ግን እንዴት ተቋቋምኩት? ለሚለው፣ በዛን ወቅት አለኝ የምለው ነገር ሁሉ ሄዶ ቤተሰቤን ጨምሮ ሄዶ ብቸኛው የቀረኝ ነገር እምነቴ ብቻ ነበር። I know I sound crazy, literary እኔን በኔ እነቴ የማይቀበል የቤተክርሰቲያን አባል ነበርኩኝ። ግን በዛ ሁሉ መሃል እኔን የሚያሳሰበኝም ያስጨንቀኝም የነበረው ከሞትኩኝ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር መኖር የሚለው አላማ ነው። ፈጣሪንም እናቱንም እብዝቼ እወዳቸዋለሁ። ኢትዮጵያም እያለሁ ሰው ነኝ እና መጨረሻዬ ምን ይሆን እያልኩ ነበር ፈጣሪን የምጠይቀው። በዛን ወቅት ብዙ ሊረዱኝ የፈለጉ ድርጅቶች እምነቱን ወይም ሃይማኖቱን ይተዋል ብለው ነበር የጠበቁት።

በፋይናንሻል ጉዳይ ከቤተሰቦቼ ስለተቆራረጥኩ በውድድሩ ምክንያት ብዙ ነገር ደርሶብኝ ነበር። ከቤቴ ወጥቼ ሰው ቤት መኖር ጀምሬ ነበር። ግን በዛ ሁሉ መሃል ውስጤ የነበረ የሚያፅናናኝ መንፈስ ነበር “እግዚአብሔር ልክ ነው ሁሉ መልካም ይሆናል እግዚአብሔር አይጥልህም ሮቤል” የሚል ኃይል ነበር ሚሰማኝ። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው በዛ ሁሉ ጉዞ ላይ ከእምነቴ ጋር በደንብ መጠጋቴ እኔን እግዚአብሔር እንደሚወደኝ፣ እንደሚቀበለኝ በደንብ ያረጋገጥኩበት ጊዜዬ ነበር። በጣም እፀልይ ነበረ ምንልበልህ ምግብ ላይኖር ይችላል፣ ጭንቀት አለው ብዙ ነገሮች በዉስጥህ ይመላለሳሉ፣ መሽቶ መንጋቱ ሁሉ ሃሳብ ይሆናል! ግን በዛ ጉዞ ዉስጥ እግዚአብሔርን አጥብቄ ተጠጋሁት! ዉስጤ በመተማመን እግዚአብሔር አለኝ ይል ነበር! ኃይል የሚሰጠኝ እና አለሁልህ የሚለኝ መንፈስ ነበር።

Yes there will be ups and down but የተሻለ ቀን ይሆናል ብዬ እንዳምን ብርታት አገኘሁ። የዘወትር ፀሎቴም የነበረው “ይሄ ሰራዬ ልዩነት ማያመጣ ከሆነ እንዲሁም የወንድም እህቶቼን

ህይወት የማይቀይር ከሆነ እባክህ ምራኝ። ፍንጭ ስጠኝ። አንተ ለኔ የመረጥክልኝ ይህ ከሆነ ግን ወደፊት መራመዴን አላቆምም ባንተ እታመናለሁ" እያልኩ ነበር የምፀልየው።

So everyday things start moving and ድቅድቅ ያሉ ጨለማዎች እየቀለሉ we are here now!.

በዛ ሰዓት ላይ ለእራሴ የነበርኩት ብቸኛ ሰው እራሴ ብቻ ነበርኩ። ከውድድሩ በኋላ therapy እና counseling ማግኘት ቻልኩ። በዛ ወጀቡ በበዛበት ሰዓት በጣም በተቸገርኩበት ሰዓት፣ ቤተሰቦችህ ሲተዉህ፣ ኢትዮጵያ የምታቃቸው የቅርቤ በምትላቸው ሰዎች ሲዘጉህ፣ የተሰማኝ የነበረው ጠዋት ላይ ተነስቼ እርቃኔን ጨለማ ዉስጥ እራሴን ብቻዬን እንዳገኘሁት ነበር። ከራሴ ሌላ ማንም አልነበረኝም እናም እንዴት እራሴን እንስቼው ወደፊት መራመድ እንዳለብኝ ተማርኩበት።

በብርሃን የነበረው ነገር ሁሉ ውሸት እንደሆነ ያወኩበት፣ ቤተሰብ ምናምን conditional እንደሆነ፣ አብሮህ ያለው ሰው፣ ያፈቀረህ ሰው፣ እንዳንዴ ያገባህ ሰው ጥሎህ ሊሄድ እንደሚችል፣ ለሰው ያለህ እምነት ባልጠበከው ሁኔታና በግዜ ሊሰበር እንደሚችል ተማርኩ።But I just kept going forward, holding on to my spiritual things that kept me moving forward.

በህይወቴ በብዛት ከምጠየቃቸው ጥያቄዎች አንዱ "ራስህን ለማጥፋት አሰበህ ታውቃለህ ወይ?" የሚለው ነው።

ለማመን ቢከብድም እንደዚህ አይነት ሃሳብ አንድም ቀን ኖሮኝ አያውቅም። ሁሌም ነገ ቀላል ይሆናል ብዬ ነበር የማሰበው። አሁን ወደ ካናዳ የሄደ አንድ ጓደኛ አለኝ እና በወቅቱ ምን ይለኝ ነበር በዚህ ሁሉ ነገር ዉስጥ እያለፍክ ይሄን ሁሉ ዜና እና የሚወራዉን ወሬ እያየህ ስንገናኝ ግን ዛሬም ደስተኛ ነህ። ትስቃለህ፣ ትጫወታለህ፣ አመለካከትህ ቀና ነው። እንዴት ነው እንዲህ ምሆንልህ ይለኝ ነበር። እኔ ያኔም ዛሬ እናንተን እንደማወራው ነበርኩ። መናደድ እና መበሳጨት ምን ይሰጠኛል ብዬ አስብ ነበር። እግዚአብሔር ከኔ ጋር እንዳለ አውቃለሁ! በጣም የማርያም ወዳጅ ነኝ እግዚአብሔር ከነእናቱ ከኔ ጋር

እንዳለ ጨርሶ እርግጠኛ ነበርኩ። መንፈሳዊዉ ሕይወቴ ነበር እኔን ይዞኝ የሄደው።

አሁን ይህን ለሚያነቡ ሰዎች ግን I am not an Orthodox anymore, I don't subscribe for any religion ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝ እና ከእናቱ ጋር ያለኝ ግንኙነት ምንም አልተቀየረም። ዛሬም ድረስ በ እግዚአብሔር ፍፁም እምነቴ የፀና ነው። ለእኔ ነገ የተሻለ ቀን ይሆናል ብዬ ፀንቼ እንድቆም ያደረገኝ እና የጠበቀኝ፣ grounded ያደረገኝ እምነት እና መንፈሳዊ ነገር ነው።

ኖር:- Beautiful! It's religion and spirituality, it's a personal experience with God, your personal relationship with what you believe in. But often times institutionalized ሲሆን church ምናምን ሲመጣ ግን you're told what to believe, how to feel, why you should do this and why you shouldn't that.

So I mean it's beautiful to see how the one that is somehow supposedly: the church that was pushing you away not the religion right? It was people who were pushing you not God, and I think having that clarity and that faith themed with spirituality, I think that saved your life right in a way. So now we are going to sort of wrapup, So I am going to bring you to the Now. And you know we've been talking about how the narratives are created especially right now: tik tok, social media it's completely a different world, So how are you navigating that nowadays? It is still a narrative that hasn't been stopped till today right? They still find a way to speak of their false narratives in different ways, so how are you navigating that right now?

ሮቤል:- ለምሳሌ እኔ ቲክቶክ አካውንቱ ነበረኝ። የሰዎችን ፖስት ኢያለው ስቃለው። በCOVID ግዜም እንድመምጣቱ አዝናንቶኛል ብዙ

ነገርም ተጠቅሜበታለሁ። ብዙ ነገር ተምሬያለሁ፣ ብዙ እውቀት አግኝቼበታለሁ፣ ብዙ መረጃ በአጭር ሰዓት አግኝቸበታለሁ። I think የአዕምሮአችን attention span አቅም በጣም short period ናት እና ቲክቶክ እሱን ነው የተጠቀመው። በአስር ደቂቃ ሰዎችን አስተምሮ መፅሐፍ ከማንበብ ገላገሉኝ አልኩ። ብዙ ነገር አግንቼበታለሁ እና ያ መልካም ጎኑ ነው።

ከዛ ግን 2023 የተፈጠረው ነገር ብዙ ጓደኞቼ ያለፍላጎታቸው ፎቷችው ተለቀቀባቸው። እርሱንም ያደረገው አንድ የኛው ኮሚኒቲ አካል ነው ብዬ አምናለሁ። ሁኔታው በጣም መጥፎ ነበር። አጠገቤ የነበሩ ጓደኞቼን ማጣታቸው ሁሉ መሰሎኝ ነበር። ሁኔታው ጎድቷቸዉም ነበር። አሜሪካ ላይ ስለኖርን አውሮፓ ላይ ስለኖር ምዕራቡ ዓለም ላይ ስለኖርክ ሰዎች ምንም የማይሆኑ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን የሆነ ሰው ፓወርህን ሲነጥቅህ you feel like shit! ከራስህ ፍቃድ ዉጪ ብዙ ነገሮች ይሆኑብሃል እና ያንን ሳየው ደግሞ ቲክቶክን እፈራው ነበር። But instagram makes me feel at home so many people are positive about it and some are even sharing their side of stories.

ከዛ “club house” የሚባል app ነበር። 2020 ላይ የኮቪድ ግዜ፣ ለመጀመሪያ ግዜ ከውድድሩ ሰባት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ከሚጠሉኝ ከሚሰድቡኝ ጋር ንግግር እንዲኖረኝ ሆንኩኝ። ያንን ንግግር ሳደርግ ብዙ ለማዳመጥ ፍቃደኛ የሆኑ ሰዎች እንዳሉ ተረዳሁ። የሚሳደቡ ሰዎች እንዳሉ ሆኖ ማለት ነው። የሆነ ነገር ስታደርግ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ወይም የሆነ ቦታ ላይ ማሳካት የምንፈልገው የራሳችን ግብ አለን። ከሚጮኸው ሰው ይልቅ ያንተን መልዕክት መሰማት የሚፈልጉ እና ሊደርሳቸው የሚችል ብዙ ሰዎች አሉ። ቢያንስ ለጥያቄ ትንሽ ነጥብ ከጣልክ in the next day build up ታደርገዋለህ! እናም በዚህ ረገድ ደግሞ ተስፋ አሳይቶኛል ማህበራዊ ሚዲያ።

ቲክቶክ ላይ July አካባቢ ነው የመጣሁት። ብዙ ሰው አላስተዋለም ነበር። አብዛኞቹ ያዩኝ ሰዎች የማደርገውን ነገር አይወዱትም። ሀበሾች የስድብ ምልልስ ነው የሚፈልጉት። ግን እኔ እነሱ የፈለጉትን ቢያሰቡ አይመለከተኝም የሚሳደቡትን አላወራም። አሁን ወደ ሁለት ወር ሆኖኛል live መግባት

ከጀመርኩ አለን ሾው’ንም ወደዛ ወሰጄአለሁ። ብዙ የማህበረሰባችንን ሰዎችን መጋበዝ እና ታሪካቸውን ማውራት ጀምረናል።

ሌላው ደሞ እኛን የማይወድን ሰዎች ለመጀመሪያ ግዜ ቪዲዮ ከፍተው ሲያወሩ ሃሳባቸዉን ባልወደዉም ለምን አሰባችሁ ማለት አልችልም። ግን when you challenge their crazy thought ground ሲሆኑ ታየዋለህ። የእምነት ሰዎቻችሁ ሰብከት እድንገደል እድንሰደድ ወይም እድንገለል ነው are you going to do anything about it? ብዬ ሰጠይቃቸው “yeah that’s not fair” ምናምን ይሉሃል so yeah you see ብዙ ግዜ እንተላለፋለን ብዬ እሰባለሁ።

ብዙ ሥራ ይፈልጋል ግን ደግሞ ሁሌም አቅሙ ያለው ሰው we need to engage a conversation ብዬ አምናለሁ። ይህን ሰል ግን ማንነቱን ይፋ አድርጎ ሚኖር ሰው ሁሉ ይህን ያድርግ ወይም ማድረግ ይችላል ማለቴ አይደለም:: የምንችል ሰዎች ግን ይህን ማድረጉ ጥሩ ነው።

እዚ ላይ ሌላ የታዘብኩት ነግር እራሴን አስተሳሰቤ በጣም westernized ሆኜ ነው ያገኘሁት:: ለምሳሌ በእኔ እና በዙሪያዬ ያሉ ጓደኞቼ ዘንድ ሴት ልጅ ስትለከፍ ሰናይ how dare he do that እንላለን! ሀገር ቤት የራሴ ኮሚኒት የሆኑ ማቃቸው ሰዎች ጋር ደውዬ ሳረጋገጥ እዛ ደግሞ ለነሱም ጭምር አሁንም ኖርማል ነው። በግዜ ሂደት ብዙ ነገር ተማርከው። አውሮፓ እና አሜሪካ ላይ ስንኖር ብዙ ሰለመብትህ እና ሰለ ሰዎች መብት ትማራለህ። ሃገር ቤት ያለው ሰው ግን ገና አሁንም እዛ ጋር አልደረሰም። ሰለሰዎች መብት ያለን ግንዛቤ ኋላ ቀር ነው። እነዚ ፕላትፎሞች ደግሞ እንዴት ብዬ ድልድይ ልሁን ብዬ እንድል አድርጎኛል።

Heterosexual ለሆነ ሰው እና ሃይማኖተኛ ለሆነ ሀበሻ overwhelming ሊሆን ይችላል። እናም እንዲህ የሆነን ባህላዊ ሀበሻ ሰውን በሚረዳው እና በሚገባው አማርኛ ካልነገርካቸው እንተላለፋለን።:።ሰለዚህ እንዴት አድርጌ እንዲረዳኝ ላድርግ ብዬ ማሰብ እንድጀምር ሆኛለሁ። Yes ሰለመብቴ እና በመብቴ ዙሪያ አልደራደርም። ያለሁበት ሃገር

ላይ መብት ስላለኝ ግን በዚህ ሁኔታ ተመልሼ ኢትዮጵያ ብሄድ ይህ አይነት ሰው ቢገጥመኝ በጥፊ ነው የሚለኝ። ይመታኛል፣ ያሰገድለኛል that is fact that is the truth. ያንን ሰው እንዴት ነው challenge የማደርገው ብዬ ሳሰብ ቢያንስ ሃሳቤን ለማስተለልፍ እና ለሰዎች ተደራሽ ለመሆን መታገሉ ጥሩ ነው ብዬ አሰባለሁ።

I have big respect በተለይ social media ላይ እነ ዲዲ ፣ ላላ እንዲሁም ሙሴ እና ሮቤል የሚባሉ ልጆች they create a narrative ሰው እንደሆንን ሌላው እንዲረዳ። የሚሰድቧቸው ሰዎች ቢኖሩም። አሁን እነ ላላን እነ ዲዲን ከሁለት መቶ ሺ ሰው በላይ ነው follow የሚያደርጋቸው። ቢጠሏቸውም ይከተላቸዋል። People are learning and adding some knowledge እና I would say pushing back is a good thing, yes it's exhausting ለሁሉም ሰው አይደለም። ለእኔ social media, I see its lots of negative aspect of it but tiktok make me to wake up በተለይ ኢትዮጵያዊው ኮሚኒቲ የቱ ጋር እንዳለ እኔ የት ጋር እንዳለው ጓደኞቼ የት እንዳሉ እና የሆነ bridge ካላገኘንለት ተላልፈን ነው የምንሄደው። እና what I see it the past two months having a conversation drain ያደርግሃል but you need to have that conversation they need to see it and hear about it.

ለምሳሌ አንዳንዶች ለመሳደብ ይመጣሉ ነገር ግን እኔ ጋር መሳደብ አይቻልም ከተሳደባችሁ mute አደርጋችኋለሁ፣ ጥያቄ ካላችሁ ግን ጠይቁኝ መልሳላሁ ሰል ያዳምጣሉ። ሰለ እራሴ ሰነግራቸው ከዚህ እድሜ ጀምሬ እንዲ ነኝ፣ እንዲ ነበርኩ፣ እንዲ ነው ሲሰማኝ የነበረው፣ ታሪኬ ይህ ነው ሰላቸው "hmm" ይላሉ ግራ ይገባቸዋል። በዛ ዘመን ኢትዮጲያዊ ሮል ሞዴል የምንለው የለንም ነበር። ሰለ ጌይነት ሰለ lgbtq ሰለ ኩዊር ኮሚኒቲ የሚያወራ ሰው አልነበረም። በእኛ ቋንቋ፣ አሁን ለእኛ ሰዎች ወተን በአማርኛ ሰናወራቸው understand በሚያደርጉት መንገድ እኔ እኮ አጠገባችሁ ነበርኩ I was walking the walk with you but you didn't see me እላቸዋለሁ። እናንተ እንዲህ አይነት ሰዎች ይገደሉ ይሰቀሉ

ስትሉ ነበር ሰው ደግሞ ይህን እየሰማ አምኖ ማንነቱን ሊናገር አይችልም ስትላቸው እግዚአብሔር እኮ እሱን አይወድም ብለው ለሰለሰ ሲሉ ታያለህ።

ለሰለሰ አሉ ማለት ግን ተቀየሩ ማለት አይደለም but I believe ይሄ በተለይ ውጪ ወተው የሚሳደቧቸው ሰድቦችን መቀነሰ እና ማቆም ይጀምራል። ለእኔ clap back topic አድርጌ የተነሳውት ቲክቶክ ላይ መዝሙር ነው የሚለጥፈው። መዝሙሩ ላይ ሄደው ኮሜንት ያደርጋሉ ያቺን ኮሜንት እንደገና አንሰቼ የሚሳደቧትን መዝሙር እሰራበታለሁ ወይ በዘፈን እሰራበታለሁ ለራሳቸው እራሳቸው በራሳቸው engage እንዲያደርጉ እና እብደታቸው እየቀነሰ ሲሄድ ታየዋለህ። እናም አዎ መልካም ጎኖች አሉት እርግጥ ነው እንዳንዴ በጣም ወደታች ይዞን የሚወርዱ ሰዎችም ሁኔታዎችም ይኖራሉ ግን ተሰፋ ሰጥቶኛል። በተለይ ቲክቶክ ላይ ከሌላው እፕ ለየት ይላል። ማለት ኢትዮጵያዊ እና ኤርትራዊው ሰላለ ድምፅ ያለው ሰው ወጥቶ መናገር አለበት። መልክህን ሳታሳይ ብዙ ሃሳቦችህን ማውራት ትችላለህ።

ብዙ ወንድም እና እህቶችም አሉን ደግሞ በጭራሽ እዛ ላይ መጥተው ሃሳባቸዉን እና ሰድባቸውን challenge ያደርጋሉ ብዬ ያላሰብኩትን በጣም ጎበዝ ሰዎች አሉ። ይህ ደግሞ ተሰፋ አለ ማህበራዊ ሚዲያው ጥሩ ነገር ሊሰጠኝ ይችላል ብዬ እንዳሰብ አድርጎኛል። እኔ ኮሜንቶቹን ሳይ I don’t take it personal የማያቀኝ እብድ ሰው ይሳደባል፣ ሰደበኝ ብዬ አልደባደብም I will never take it personally የተሳደቡትን ሰዎች ግን ሰድባቸውን አደባባይ አውጥቼ እንዲ ተብያለሁ እኔ ደግሞ በመዝሙር ነው የምመልሰላቹ ብዬ ለራሳቸው ሰጣቸዋለሁ። እሰካሁን ባለው እንደዛ ነው ማደርገው። እናም ማህበራዊ ሚዲያ እንዴት መጠቀም እንዳለብህ ማወቅ እና ራስህን ማዘጋጀት አለብህ፣ psychologically, emotionally, mentally you need to prepare እንደዛ ካልሆነ የእንዳንድ ሰው ኮሜንት ሊሰብርህ ይችላል።

ኖር:- አዎ በርግጥም እያደገ የመጣ ነገር ነው። ከፌሰቡክ ከፌክ አካውንት ምናምን አሁን ላይ ደግሞ ሰዎች online ላይ

ሆነው ያወራሉ። እንዳልከው መሰዳደቡም ቢሆን negative ሊሆን ይችላል ግን እየተሳደቡም its breaking their perception በተለይ የነላላ የነ ዲዲ ላይ አንቺ ሴት አይደለሽም ወንድ ነሽ ይላሉ ግን that statement by self is a very paradoxical አይደለ? ወንድ አይደለሽም እያሉ ግን "አንቺ" እያሉ ነው የሚያወሩት at least enforce and acknowledge ያደርጉታል።

If you go back in to the time machine 2012 you were one of the only people that was visible so now in the present day we have more people that are creating awareness putting themselves out there, and choosing to share their life experience as well. የእነሱን እዛ የደረሱበት ትግል ታሪኮች አሏቸው and we are seeing more and more people. ግን ዛሬም ድረስ መመላለሱ ልክ ያልሆኑ እና ያልተቀየሩ ትርክቶች አሉ spin የሚደረጉ። የተለያዩ ታሪኮች እና ሀሜት የሚመስሉ በዉሸት የተቀናበሩ ወሬዎች አሉ፣ ለምሳሌ ፋሪስ የወር አበባ ማየት ጀመረ ይላሉ.....

ሮቤል፡- የምርህን ነው?....oooh my God!

ኖር፡- እዋ Facebook ላይ ባህሩ እና ፋሪስ ተጋብተዋል እና አንድ ላይ እየኖሩ ነው የሚሉ አሉ፣ እገሌ ከዘማሪነት ወደ ጌይ ተቀየረ የሚሉ አሉ። ይህን ትርክት ሚጠቀሙት ሰዎችን capture ለማድረግ ነው። በተለይ አሁን አሁን የ እኛ story popular ሆኗል። ያንን የተቀናበረ ነገር ባወሩ ጊዜ በጣም ተደራሽ ይሆንላቸዋል እና ትኩረት የሚስብ ሆኗል። ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ጉዳዮች ሲነሱ መልሰን መልስ ለመሰጠት እንቸገራለን ወይም ደግሞ እኛም እራሱ እራሳችንን ፈልጎ በማግኘቱ ስለተጠመድን እና እራሳችን ላይ መሰራት ስለነበረብን ጊዜ አልበረንም። አሁን ግን ሰዎች ወጥተዉ እነሱ ጋር ያለዉን እውነታ ማጋራትም ይችላሉ እንደገናም አንዱ ላንዱ መቆም ይችላል እና እሱ መልካም ነገር ነው።

በመጨረሻም መጨመር ምትፈልገው እና ማለት ምትፈልገው ነገር አለ?

ሮቤል፦ ይህን ሃሳብ አምጥታችሁ በመስራታችሁ በጣም ምስጋና ይገባችኋል። በርግጥ አሁን አሁን ለብዙዎቻችን ማንበብ ችግር እየሆነ እየመጣ ነው ግን ደግሞ መፃፍ የሚችሉ ሰዎች ተጨንቀው ይህን ፅፈው ለታሪክ ሊተርፍ በሚችል መልኩ ማስቀመጣቸው በጣም ደስ የሚያሰኝ ነው። እኔም እንኳ ቲክቶክ ላይ ስፅፍ ወይም ስለ lgbtq ነገሮች ስናወራ በአማርኛ አይወራም። ሳላውቀው ስለ lgbtq ወይም ስለ ራሴ issue ሳወራ እንግሊዘኛ ነው የሚቀለኝ። ሳላውቀው ድሮ ኢትዮጵያ ሳለው ደብዳቤ ሳረቅ ለምውለው ልጅ ዛሬ አማርኛ አስተርጓሚ ፈላጊ ሆኛለሁ። እኔ በእንግሊዝኛ የፃፍኩትን በአማርኛ match የሚያደርግልኝ ሰው ፈልግልኝ ብዬህ ሁሉ አቃለሁ እና እናንተ ደግሞ አሁን በአማርኛ መፃፋቹ እና ዶክመንት ማድረጋችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሰዎች ወደፊትም ለሚሰሩ ሰዎች ትልቅ ነገር ነው እየሰራችሁ ያላችሁት።

የሰዎች ታሪክ ሲወራ I believe የእያንዳንዳችን የምናስቀምጠው አሻራ ነው ለሌሎቹ ብርሃን የሚሆነው። እንደኛዉ ልላችሁ የምወደው ነገር አንዳንዴ ብዙ ሰው ላያነበው ላያየው ይችል ይሆናል ነገር ግን ተስፋ አትቁረጡ እናም ቀጥሉበት። እናንተ ባመናችሁት ልክ ብዙ ሰው ባያየው እና እንዳሰባችሁት ባይሆን እንኳ ታሪካችንን ባንዘፍነው እና ባናወራዉም በናንተ ዘንድ ለታሪክ እንዲቀር ሆኗል እና ለሱም በጣም ትልቅ ምስጋና አለኝ። ምክንያቱም ሰውን መቀየር የምንችለው ባለን በአቅማችን ነውና አንዱ ያወራል አንዱ ይፅፋል፣ አዕምሮን መቀየር የምንፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወንድም እህቶቻችን በሰላም መተንፈስ አለባቸው ብለን ስለምናምን ነው። እኔ እዚህ ያለሁበት ሀገር ላይ ሆኜ ምንም ሳላወራ መኖር እችላለሁ ግን እናንተ ታሪካችንን እየዘገባችሁ እያስቀመጣችሁ እንዲሁም acknowledge እያደረጋችሁ ነው እና ለሱም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ሌላው ልሰጣችሁ ያሰብኩት የቤት ሥራ አለ። የቤት ስራው ምንድነው ከሁለታችሁ አንዳችሁ ወይም ሁለታችሁም አንድ ቀን እለን ሾው ላይ ፊታችሁን ሳታሳዩ ስለዚህ መጽሃፍ ለምን እንደጀመራችሁት እንዳታወሩ ፈልጋለሁ። ምክንያቱም ብዙ ያልተሰሙ ታሪኮች አሉ እና የእኛ ኮሚኒቲ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም

ሰዎች ገብተው ቢያነቡት ይጠቀማሉ ብዬ ነው የማስበው እና የሆነ ቀን እንግዶቼ እንድትሆኑ እፈልጋለሁ።

ኖር፡- አዎ በሚገባ ይቻላል፣ በጣም ደስ ይለናል አንዳችን እንገኛለን።

ሮቤል፡- ይህን ውይይት ስላደርግን በእውነቱ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል። ለኔ ዛሬ ላይ ከናንተ ጋር መገናኘት ችዬ ማውራቱም ትልቅ ነገር ነው። በአካል ባንገናኝም ይህ አይነት access ኖሮ ደግሞ ማውራት መቻላችን ከኮሚኒቲያችን ጋር ከመገናኘት አልፎ ትምህርትም ሊሆን የሚችል፣ ነገ ተነገወዲያ መጥትዉ የሚያመሳክሩትን እውቀት ሰላወራን እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል። ከልቤ በጣም አመሰግናለሁ ለሰጣችሁኝ እጅግ የሚያምር ጊዜ።

ኖር፡- እኛም ስለሰጠኸን ግዜ እንዲሁም ስላጋራኸን እጅግ የሚያምር እና አስተማሪ ታሪክ በጣም አድርገን እናመሰግናለን!



# Reflections on love and relationship

The following conversation is meant to be an exercise in reflection on **love and relationship**. All that it requires is that you and your partner give your complete attention and awareness to this moment, to the room you are sitting in and to each other.

For this conversation you will need:

*A phone or recorder (make sure it is on do not disturb)*

*A candle.*

*Cushions (optional)*

***Make space for the silence, the nervous giggle or blush. These are just guiding questions so let your answers flow however they come.***

Begin by sitting on the floor, *press record*, light the candle and close your eyes. Bring your awareness to your breath, how does it feel to be in your body right now? Let the feeling permeate throughout your being.

Take this moment of stillness and quiet before you start your conversation, you both deserve it.

Reach out and hold your partner's hand, how does their touch make you feel? Stay here for as long as you want and when you are ready, you can start the conversation:

Are you ready?

*Mm-hmm.*

Okay. So, the first prompt here

*So I read it?*

Yeah, you read it.

**“What is your first memory of each other? Give space to whatever comes up.”**

So what’s your first memory of me?

*My first memory of you is, um, at the restaurant. I had arrived. I was nervous. I sat on the balcony. You weren’t there, I thought I was first. I texted you, you said you were upstairs, and so I went upstairs, and I immediately saw you in your orange jacket and a smile on your face. And we hugged and sat down. And then just started talking and talking for a couple hours.*

Yeah, like three hours?

*Yes.*

Yeah. I mean, I think it was the same thing for me. I was sitting upstairs . Uh, and you, uh, you walked in with your white T-shirt and black jeans, like, and then we hugged, yeah?

*Yes.*

Um, I do remember you being nervous for the most part. Uh, but there were times where you were not, like, looking, not looking at me in the eyes or, like, you would just shy away....

*Uh... Yeah.*

**“How does the love you have for each other shape your everyday interaction?”**

*You can start.*

Hmm. Your everyday interaction. I mean, for me, I mean, we’re not, like, people that, like, texts all the time or everything, but we do, like, check in on each other when we’re not, uh, together. Um, but, I mean, I think for me, when we’re spending time with each other, it does, like, I don’t know how to phrase it exactly. But, um, I don’t know.....

You can say something as I try to articulate what I’m trying to say...

*I think the love I have for you is, um, very comfortable. And so, our everyday interactions are very comfortable. I’m myself- Not stressing about things or how I am in front of you, or um... And like you said, with the texting, there are also just check-ins I know are more than enough, um, or enough. And Yeah, the love I have for you just brings out that comfort.*

That’s so sweet. I mean, the same for me, I think. It just makes things easier for me. I also do feel comfortable. I’ve just said this before, like most of my cards are, like out on the table, from the get-go, right?

*Yeah.*

Well, I’m not trying to impress you in the sense that, you know, I don’t have to be somebody that I’m not or try to overextend myself. I could just simply just reach out.... You know what I mean? I don’t wanna get into the specifics, but it made this year very special for me because I’m also in a very transitional moment in my life. So, having someone there that I can rely on, that I

can, um, spend time with, like then also just gives me energy to face the things that I'm going through. Not that I'm going through like a bad thing.

*Mm-hmm.*

But like, you know, just like energy to, you know, go through them. To know that, you have love, uh, you're loved, you're cared for. And yeah, that feeling does make me feel like I'm not going through things on my own, and that I have the support that I need in my life. So, that makes every day good.

*Cute.*

**How do you make space for your sorrow?**

*I feel like I haven't had very much sorrow. I mean, I'm trying to think of the lowest moments I've had this year since meeting you and nothing really comes to mind except for a, like a bad day. Um... And I guess we make space for them by always addressing how we're feeling, um, what's bothering us or what's bothering me, what's on my mind and then I always feel better after doing that.*

I mean, for me, I think I did have, like, a couple of months where I was just feeling a bit out of sorts. And I think having you around, not as a form of distraction, but having somebody there next to you while you're going through something, and then just, you know, making space for that has been very important for me. And it's in the little things. It's not necessarily about, like... yes, of course, being open, opening up and talking about things is important, but just it's in the little things like, if I'm having a nightmare at night, knowing that you're next to me.

*Mm-hmm.*

You know what I mean?

*Yeah.*

So for me, I think it's just holding the sorrow itself by myself. But then knowing that I'm not also at the same time holding that sorrow and pain by myself. Like does that make sense?

*Yes, it does.*

**What are your shared dreams and hopes?**

*Um, I think stability, which I have, in terms of emotional stability, but I think stability in all ways, financial. Um, dreams are just progression, progression with our connection and our relationship, progression in both of our careers.. Those are my main dreams and hopes.*

I mean, for me as well, I think this year has been important for me to find stability, right? And, um, and also kinda like opening myself up after being closed off for many reasons, ma- mostly because of pain, you know.

*Mm-hmm.*

Um, and part of me opening up and then like bringing down the walls around me is manifesting in many ways in my life. And one of it is our relationship, which is part of my hope and dreams in a way, you know what I mean?

*Mm-hmm.*

This is something that I wanted for myself to be able to, like open up more and then find that stability in my life and then find a partner that I can do this life with. Yeah.

So in that sense, I feel like I'm already in that place. But just like you said, stability and both of us being able to kinda, uh, go forward in whatever it is that we're working towards and then being there for each other in the best way that we can. So, I guess that's... that's that.

*Yeah. Same here.*

We can end this with a kiss ahaha.

I love you.

*I love you too.*



# ነጸብራቅ፡-
# የአዘጋጆች ወግ

አናኒያ:- Hey!

ዛክ፦ ሰላም ሰላም!

አናኒያ፦ I’m so happy we’re doing this Zac. ስለ ፕሮጀክቱ እንዲህ ቁጭ ብለን በጥልቀት ያወራን አይመስለኝም። ሁልጊዜ በሥራ ተወጥረን በቀጣይ ምን ይሰራ በሚለው ላይ ብቻ ስለምናተኩር፣ አሁን ጊዜ ወስደን ያለፉትን ሦስት ዓመታት መለስ ብለን ማየታችን ጥሩ ነው።

ዛክ፦ እኔም ደስ ብሎኛል። መጽሐፉን የማዘጋጀቱ ሂደት ምን እንደሚመስል ለአንባቢያን ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚ ይመስለኛል። የዚህ ጥራዝ ጭብጥ “ንጸብራቅ” እንደመሆኑ መጠን፣ እኛ መለስ ብለን ሐሳባችንን ካላካፈልን ነገሩ ሙሉ አይሆንም።

አናኒያ:- Exactly. So we can start from the first issue ! የመጀረያው ርዕሳችን የተመሳሳይ ፆታ ፌሽታ የሚል ነበር።

ዛክ:- Yeah queer joy!

አናኒያ:- Can we talk about your memories of working on this first issue?

ዛክ:- አዎ! በእውነቱ የኖርን የመጀምሪያ እትም ስንሰራ እኔ ትንሽ የተጣበበ የህይወት አጋጣሚ ላይ ነበርኩ። በተጨናነቀ ሰዓት ዉስጥ ሆኜ የሰራሁት ሥራ ነው። ከዛ ግን ያ ግዜ አልፎ ስራው ሲያልቅ ደግሞ እጅግ የተደሰትኩበትን ሥራ ሆነ።

የሥራው ባህሪ ሆኖ ከተለያዩ ግለሰቦች ነው ታሪኮችን ስንሰበስብ የነበረው እና የሆነ ታሪክ ሲላክልኝ በጣም ደስ ይለኛ ነበር። አንድ ታሪክ ኤዲት አድርገን ባጠናቀቅን ቁጥር ከፍተኛ ደስታ ይሰማኝ ነበር። ብቻ ባጠቃላይ ስለዚህ ዕትም ሳስብ እሱ ነው ትዝ የሚለኝ። እኛም አብረን መስራት ስንጀምር የመጀመሪያችን ነበር ታስታውሰ እንደሆነ።

አናኒያ:- አዎ በደንብ አስታውሳለሁ! ለኔም ትውስታው ተመሳሳይ ነው። በወቅቱ transition period ላይ ነበርኩ። እንዲሁም ሙሉ አቅሜን እና ጊዜዬን የሚፈልጉ ሌሎች አድካሚ

የሆኑ ፕሮጀክቶች እጄ ላይ ነበሩ። የምሰራዉን ነገር ሁሉ ለምን እሰራዋለሁ ብዬ እራሴን የጠየኩብት ጊዜም ነበር። በተጨማሪም ከግል ሕይወትም እንዲሁም ከሰራም ጋር ተያይዞ ችግሮች የነበሩበት ግዜ ስለነበረ ትንሽ confused ነበርኩኝ።

እዚህ ፕሮጀክት ላይ መሰራቴ ግን ከሆነ አዲስ አሰራር ጋር ነው ያስተዋወቀኝ። ከዚህ በፊት እኔም ተመሳሳይ የእርት ስራዎችን የሰራሁ ቢሆንም እንዲሁም ፅሁፎች አጋርቼ ባውቅም፣ በዚህኛው ጎራ ሆኖ የሌሎችን ታሪክ ኤዲት ማድረጉ፣ ለአንባቢ በሚሰብ መልኩ ማዘጋጀቱ እና ባጠቃላይ polish አድርጎ ማቅረቡ የመጀመሪያ ስራዬ እንደመሆኑ መጠን ከፍተኛ ደስታ ነበረው። መሰራት የምፈልገው ይሄ ነው ብዬ እንዳስብ ያደረገኝ እና ምን መሰራት እንደምወድ clarity እንዲኖረኝ ያደረገኝ ግዜ ነበር። ሌላም የማልረሳው ነገር በዚህ ሥራ ላይ ስንሳተፍ የነበርነው ሁላችንም ትንሽ አስቸጋሪ ጊዜ ዉስጥ እንደነበርን ነው።

ዛክ፡- አዎ እውነት ነው ጥሩ ያልሆነ ባይባልም transition period ሊባል የሚችል ሁኔታ ዉስጥ ነበርን። እኔ ለምሳሌ በጣም አድካሚ ሥራ ነበር የምሰራው እና ከጥዋት 12 ሰዓት እስከ ሌሊቱ 6 ሰዓት ሥራ ላይ ልሆን እችላለሁ። እናም ታሪኮቹን ኤዲት አደርግ የነበረው ሌሊት ከስራ መልስ ነበር። ነገር ግን እንደዛም ሆኖ ድካሙ አይታወቀኝም ነበር። ደስ ብሎኝ ነበር የምሰራው። አብረውኝ የሚሰሩት ልጆች በየራሳቸው ፈተና ውስጥ ሆነውም ለሥራው የሰጡት ሙሉ ኃይል የሚደነቅ ነበር። ያንን ጊዜ ሳስታውሰው ሁሌም ደስ ይለኛል።

እናኒያ፡- ይመስለኛል የሆነ sense of relief ነበረው። People say “it is good to keep yourself busy and occupied” በርግጥ ጤናማ ያልሆነ ጎንም ሊኖረው ይችላል ምክንያቱም እንዳንዴ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታም ለመርሳት እራሳቸውን በሌላ ጉዳይ ሊወጥሩ ይችላሉ። ግን በሌላ በኩል ስታየው ደግሞ እንዳንዴ በህይወትህ ብዙ በጎ ያልሆኑ ነገሮች እየተካሄዱም ቢሆን በመሃል ደግሞ እጅግ መረጋጋትን ደስታን የሚሰጡ እንዲሁም እየሆነ ያለዉን ረስተህ ሰላምህን እንድታገኝ የሚረዱ ጉዳዮች አሉ። ይመስለኛል ይሄ ሥራ ለሁላችንም ሰላማችንን የምናገኝበት ነበር። በተጨማሪም ሁላችንም በየግላችን ብዙ የሰራነው ቢኖርም እንዲህ ተገናኝተን ይህን

ሥራ ስንሰራ የመጀመሪያ እንደመሆኑ መጠን ትልቅ ደስታን የፈጠረልን ይመስለኛል።

ሌላኛው ማስታውሰው ደግሞ ሙሉ ስራዉን ኦንላይን ነበር የሰራነው።

ዛክ:- ልክ ነው ተጀምሮ እስኪያልቅ ሙሉ በሙሉ ኦንላይን ነበር የሰራነው ማንም ሰው አብሮ አልነበረም ሁላችንም የተለያየ ቦታ ሆነን ነው የሰራነው። እናም የሰዓቱ ልዩነት በጣም አስቸጋሪ ነበር። እንዱ ሊተኛ ሲል አንዱ ገና ከ እንቅልፉ እየነቃ ነው እና ሁላችንም የተለያየ ዓለም ክፍል ሆነን መሰራቱ ሌላ አስቸጋሪ ነገር ነበር።

አናኒያ:- አሁን ሳስበው በዛ አይነት ሁኔታ ዉስጥም ቢሆንም ሁላችንም የየግላችንን ልምድ አጣምረን ኖር የመጀመሪያዉ ቢሆንም በጥሩ መልክ ለ አንባቢው አስተዋውቀን ነበር ብዬ አምናለሁ እና በጣም ዉጤታማ ሥራ ነበር። ሌላ አንተ ምታስታውሳቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ምን ነበሩ?

ዛክ፦ ቻሌንጁ ጋር ከመግባቴ በፊት ሌላ ማለት የምፈልገው እዚህኛው እትም ላይ ከየትኛዉም ጊዜ በተሻለ የ community ተሳትፎ በጣም ከፍተኛ ነበረ። በጣም ብዙ ታሪኮች ነበሩ የመጡልን፣ ሁሉም ሰው ታሪኩን ለማጋራት ከፍተኛ ጉጉት ነበረው እናም ደስ ይል ነበር።

አናኒያ:- Yeah but also we did a good marketing promotion for it, I think we had a proper marketing strategy. And I remember what we did on the release was also a surprise release type of situation.

ዛክ:- እንደተረዳሁት ከመውጣቱ በፊት ሰዎች ምን እንደሆነ በደንብ አላወቁም ነበር።

አናኒያ:- ጥሩ ማርኬቲንግ ስትራቴጂ ነበር። እኛ የምንሰራው የኩሽናዉን ሥራ ነው፣ ሰዎች ታሪክ ያጋሩናል እኛ ደግሞ ያንን እንደግብአት ተጠቅመን ከሽነን ማቅረብ ነው ስራችን። የኖር የመጀመሪያዉ እትም ላይ ስናስተዋውቅ የነበረበት መንገድም እሱ ነበር። ትዝ ይለኛል "ኖር በሰላለች" እያልን ያስተዋወቅነው።

በሚገርም ኃይል ነበር የተሰራው ከግራፊክስ ዲዛይኑ፣ ከኤድቲንጉ፣ ከታሪኩ እና ከዝግጅቱም ባሻገር መጽሃፉ ሊወጣ አከባቢ የነበሩት ሰራዎች እንዲሁም ከወጣም በኋላ የተወሰንን ሰዎች ተሰብሰበን ዝግጅት ነበረን፣ እንዲሁም በመድረኩ ላይ የተወሰኑ ታሪኮችም ተነበው ነበር እና እጅግ በጣም ድንቅ ግዜ ነበር። መጽሃፉን ጀምሮ ለመጨረስ አራት ወር የፈጀብን ይመስለኛል።

ዛክ:- እዋ አራት ወር ነው የፈጀብን። ለኔ ደግሞ ሌላኛው ደስታ የነበረው በዚህ አይነት ሥራ ዉስጥ ለመጀመሪያ ግዜ መሳተፌ ነበር። ምናልባት ከዛ በፊት የሰራሁት ሥራ ቢኖርም እዚህ ዉስጥ ከነበረኝ ተሳትፎ እና ልምድ አንፃር በአብዛኛው መልኩ ይህን አይነት ሥራ ስሰራ የመጀመሪያዬ ነው ብዬ እንዳስብ አርጎኛል።

እናኒያ:- Yeah you had *fresh* energy!

ዛክ:- እዋ ከሥራው በፊት ቀድመን መተዋወቃችን ብዙ ነገር አቅልሎልኝ ቶሎ ነበር ሁሉንም ነገር የለምድኩት እና የተዋሃድኩት። ከዛ በፊት እንዲህ አይነት ሥራ በተወሰነ መልኩ የሰራሁኝ ቢሆንም እዚህኛው ላይ የነበረኝ ተሞክሮ እና ልምድ በብዙ መልኩ የመጀመሪያዬ ነው ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል።

እናኒያ:- አሁን ደግሞ ወደ ተግዳሮቶቹ እንለፍ። በርግጥ ተግዳሮት ብሎ ማስቀመጥ ትንሽ ትርጉሙን ሊያዛባው ይችላል። ነገር ግን ተግዳሮት ስል ምን ማለቴ መሰለህ ይሆናሉ ብለን ያልጠበቅናቸው እና ቀድመን ያላየናቸውን ጉዳዮች ማለቴ ነው። ስራው በሚሰራ ግዜ ከብዙ ሰዎች ጋር ማውራት፣ ታሪክ መሰብሰብ፣ እንዲሁም የመጽሃፉን ይዘት አስረድቶ ለዛ በሚሆን መልኩ ሰዎች ታሪካቸዉን እንዲያሰናዱ ማድረግን ይፈልግ ነበርና በዛ ሂደት ዉስጥ የነበረው ተግዳሮት ምን ነበር? ለአንባቢዎች የመጀመሪያው ጉዞ ምን ይመስል እንደነበር በዛው ብታስረዳ?

ዛክ:- ስራዉን ስንጀምር እራሳችን ያስቀመጥነው ቻሌንጅ ነበር። አራት እትም ለመስራት አስበን ነበር የተነሳነዉ። በየዓመቱ አንድ አንድ እያደረግን እናም በመጀመሪያ እሱን ግብ መምታት መቻሉም አንዱ ቻሌንጅ ነበር። ከባዱ ቻሌንጅ እሱ ባይሆንም አንዱ ቻሌንጅ ግን እሱ ነበር የታቀደውን ግብ መምታት ስለነበረብን።

ሌላኛው ቻሌንጅ፣ አንዳንድ ሰው ታሪኩን መናገር ይችላል እንጂ መጻፍ አይችልም። እንዲሁም ደግሞ እኛ ካሰብነው ጭብጥ ጋር የማይገናኙ ብዙ ታሪኮችም ይመጡ ነበር። ለምሳሌ የመጀመሪያው እትም ጭብጥ የዜጎች ፌሽታ ወይም Queer joy ነበር። ይደርሱን የነበሩት ታሪኮች ግን አብዛኞቹ ጭብጡን ያልተረዱ ነበሩ። አርባ እና ከዛ በላይ ታሪክ ቢመጣም ከዛ ዉስጥ ጭብጡን ያገናዘበ የሚሆነው አስራ አምስት ታሪክ ቢሆን ነው። እሱም አንዱ ተግዳሮት ነበር። ከዚህም ጋር ተያይዞ ደግሞ ታሪካቸውን አጋርተውን ሳናሳትመው ሰንቀር ሚቀየሙ ብዙ ሰዎችም ነበሩና እሱም ደግሞ ከባለታርኮቹ ቅሬታን ስለሚያመጣ አንድ እራሱን የቻለ ቻሌንጅ ነበር። ታሪክ የመሰንብሰብ ሃልፊነቱ ሙሉ በሙሉ የኔ ሥራ ስለነበር ቅሬታ በቀጥታ ሚደርሰኝ እኔ ነበርኩኝ እና እሱ ትንሽ ከባድ ነበር።

ሌላኛው ደግሞ ምን መሰለህ የተወሰኑ በአካል የማውቃቸው ጓደኞቼን ታሪኮቻቸውን እንዲያጋሩና እንዲሳተፉ ምጠይቃቸው ያሉ ቢሆንም አብዛኛውን ታሪኮች የምሰበስበው በፌስቡክ አማካኝነት ነበር። ታዲያ በዚህ መሃል ሰህተት ሰርቻለው ብዬ የማሰበው አንዱ ነገር በፌስቡክ ላገኘኋቸው ሰዎች የምሰጠውን ያህል ትኩረት በአካል ለማውቃቸው ሰዎች ወይም የቅርቤ ለምላቸው ሰዎች ሰጥቻለሁ ብዬ አላምንም።

እናኒያ:- ለምን?

ዛክ:- የቅርቤ ስለሆኑና support system አላቸው ብዬ ስለማምን ይመስለኛል። ወደቅድሙ ሰመለሰ ጽሑፉ ከታተመ በኋላ ሁሉንም ሰው ስሜቱን ጠይቃለሁ፣ ነገር ግን ቅድም እንዳልኩህ ጓደኞቼን ወይም በቅርብ የማውቃቸዉን ሰዎች ከአንዴ በላይ አልጠየኩም ነበር። እኔ የማሰበው የፅሁፉ ጭብጥ የዜጋ ፌሽታ ቢሆንም እንኳን ታሪካቸዉን በሚያጋሩ ግዜ ግን ሰዎች ከባድ የሆኑ ትውስታዎቻቸዉን ሊቀሰቅሱ ይችላሉ። ትውስታቸውን መቀሰቀሱ ሚፈጥርባቸው ጫና ይኖራል ብዬ ስለነበር የበለጠ ተኩረት አድርጌ የማወራው በደንብ የማላውቃቸውን ሰዎች ነበር። ቅድም እንዳልኩት የቅርብ የምላቸው ሰዎች እኔ እንኳን ባላዋራቸው ሌሎች በቅርበት የሚያወሩት ሰው አለ ብዬ ሰላሰብኩ ነበር። ይህ ግምት ግን ልክ አልነበረም።

ለምሳሌ በዚህንኛው እትም ከሮበል ጋር በነበረን ጭውውት የጓደኛውን ሕልፈት መስማቴ ምንም ያልጠበቁት ነገር ነበር። ምክንያቱም ስንጀምር እኛ ልናወራ የነበረው ስለ ቁንጅና ዉድድር ነው እና እእምሮህ እንደዛ አይነት አሳዛኝ ታሪክ አይጠብቅም። ሌሎች ሰዎችም ደስታቸዉን እያጋሩህ እንኳ በመሃል ያልጠበከዉን አሳዛኝ ታሪክ ልትሰማ ትችላለህ እና እንደዛ አይነት ሁኔታዎች ላይ የበለጠ ትኩረት አድርጌ ያን አይነት ታሪክ ላጋሩኝ ሰዎች የበለጠ ክትትል አደርግ ነበር።

ሌላኛው ደግሞ ምንድነው ይህን ነገር ሲጀመር የሚያዝናና መስሎኝ ነበር አሁን ግን ሥራ ሆነብኝ ያሉኝ ሰዎችም ነበሩ። ደጋግሜ እዚህ ጋር አስተካክሉት እዚህ ጋር ደግሞ ይህን ጨምሩ ስል። እናም ባጠቃላይ ለሁሉም ተሳታፊ ተመጣጣኝ ያልሆነ/ ትኩረት ነው የሰጠሁት እሱ ሌላኛው ጥፋቴ እና ቻሌንጅ ነበር።

አናኒያ:- እርግጥ ፕሮጀክት ስትሰራ በሚኖሩህ ግኑኝነቶች ዉስጥ ግጭቶች ይኖራሉ። ያው ሁሉም የሚመጣው ታሪክ ምንም ፈጠራ የሌለበት ሙሉ በሙሉ ከህይዎት የተቀዳ እውነታኛ ታሪክ እንደመሆኑ መጠን ከዜጋ ታሪክ ባሻገርም ብዙ ሌሎች ጉዳዮችንም ያስከተለ ይሆናል።

ሰው እንደመሆናችን ዉስብስብ ፍጥረት ነን እና ታሪካችንም በዛው ልክ ዉስብስብ እና ብዙ ጥግጋትን የሚነካ ይሆናል፣ እንዲሁም ያንዳንዱ አስደሳች ያንዳንዱ ደግሞ አሳዛኝ ይሆናል። እንደ አንድ ዜጋ ሰው ደግሞ የሁላችንም የሕይወት ልምድ ድርብርቦሽ ይለያያል። እናም ይህን የመሳሰሉት የሕይወት እና እንደግለሰብም ያለን ባህሪ ፕሮጀክቱ ሲጀመር እና ሲያልቅ ያለንን ግኑኝነት መልኩን ሊቀይሩት እና ውስስብ ሊያደርጉት ይችላሉ። እንደ አዘጋጅ ሁላችንም የራሳችን ተጠያቂነት እና ኃላፊነት ቢኖረንም የወጣነው ከማህበረሰቡ እንደመሆኑ መጠን ፕሮጀክቱ ሲጀመር እና ሲያልቅ የሚኖረን ግኑኝነትም እንደዛው ውስስብ ሊሆን ይችላል።

ቅድም አንተም ስትል እንደነበረው በወቅቱ ሃሳቡ አዲስ እንደመሆኑ እና ሰዎች ደግሞ በበሃሪያችን አዲስ ነገርን ከመውደዳችን የተነሳ በጣም ብዙ ታሪኮች ይመጡ ነበር። እኛም በተቻለን መጠን ታሪኮቹን ለማካተት ጉጉት አድሮብናል፣ ለምሳሌ ከሚመጡት ታሪኮች ግማሹ የሚዳስሰው ስለወሲብ

ነበር። ጭብጡ ደግሞ የዜጋ ፌሽታ እንደመሆኑ መጠን ወሲብም በራሱ አንዱ የደስታ ምንጭ ነው እና አይ ይቅር ብለህ ልታስቀረው አትችልም። ይህን ተረድተን በተቻለን መጠንም ታሪኮችን ሳንመርጥ ባለታሪኮቹ ጭብጡን ተረድተው በፃፉበት መንገድ ለማስቀመጥ ሞክረናል። ያው ጭብጡ ይህ ነው ብለህ ከተናገርክ በኋላ ሰዎች እንዴት ይረዱታል በሚለው ላይ ስልጣን የለህም እና ሰዎች በተለያየ መንገድ ተረድተው ታሪካቸዉን ያስቀምጣሉ። ያንን ማስታረቅ እና የሁሉንም መረዳት ባማከለ መልኩ ማስቀመጥም አንዱ ቻሌንጅ ነው።

ለምሳሌ በሁለታኛው እና ሶስተኛው እትም ላይ ብዙ ለሰዎች የምንሰጣቸው አስተያየቶች ነበሩ። ጭብጡን ቅርጹን ካወጣንና ካሳወቅናቸው በኋላ ታሪኩ ሲደርሰን ደግሞ የራሳችንን ግምገማ አርገን የፀሃፊዎቹን የመረዳት ነፃነት ባልነካ መልኩ ታሪኩ ጭብጡን ይመጥናል አይመጥንም የሚለዉን እናያለን።

ቅድም አንተም ስትል እንደነበረው ሰዎች ታሪካችንን መናገር እንችላለን እንጂ አብዛኞቻችን ታሪካችንን መፃፍ አንችልም! እርግጥ ነው ይሄ ሁላችንም የምንረዳው ጉዳይ ነው። ሁሉም ሰው ከተለያየ ሥራ እንዲሁም ከተለያየ የትምህርት ደረጃ የመጣ ነው። ሁሉም ሰው ጊዜ አይኖረዉም። አንዳንዴ በሥራና በሕይወት ዉጥረት ዉስጥ ሆነህ የራስህን ሃሳብ ሰብስበህ ወደ ፅሁፍ መቀየር ትልቅ መስጠትም ጭምር ነዉ።

በተመሳሳይ ጊዜ አንዱ የ ኖር ግብም ታሪክ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ እንዴት አድርጎ ታሪኩን ማውጣት እና መፃፍ እንደሚችል ማስተማርም ማበረታታትም ጭምር ነዉ። እናም አንዳንድ ፅሁፎች የመዋቅር ጉድለት ይኖራቸዋል፣ ለምሳሌ መግቢያ፣ ሐተታ እና መደምደሚያ የሌላቸው ታሪኮች ይኖራሉ። አንዳንዱ ደግሞ እሱንም አሟልቶ የሆነ ቦታ ላይ ሃሳቡ በቂ ማብራሪያ ላይኖረው ይችላል። የቃላት ወይም የፊደል ግድፈት ሊኖረው ይችላል። በዚህም ላይ ይህ ቢስተካከል፣ እዚህ ጋር ይህ ቢወጣ፣ እዚህ ጋር ደግሞ ይህ በደንብ ቢብራራ፣ እዚህ ጋር ደግሞ ይህ ቢጨመርበት ብለን ሃሳብ እንሰጣለን።

ስለዚህ ስራው የጭብጡን ግብ መምታት ብቻ ሳይሆን የታሪኩን ጉልበት በደንብ ማውጣት እና ባለታርኮቹንም በደንብ

ሃሳባቸውን ያስቀምጡ ዘንድ ማበረታታት ነዉ። ታዲያ በዚህ መሃል ሰዎች ታሪካቸዉን በደንብ ሳቢ በሆነ መንገድ እና ቆንጆ ቅርፅ ባለው መልኩ እንዲያጋሩ በማድረግ ሂደት ዉስጥ ብዙ ንግግሮች እና ምልልሶች ስለሚኖሩ ለአንዳንድ ሰዎች አስልቺ እና የቤት ስራ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም ያለንብት ዘመን የሶሻል ሚዲያ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች አጫጭር ፅሁፎችን ማጋራት ላይ ጎበዝ ናቸው። ይህ ሶሻል ሚዲያ ያስለመደን አጫጭር ነገር ደግሞ እንዲህ አይነት ረጅም ታሪክን ማጋራት ሲኖርብን የራሱን ችግር አምጥቷል። በዚህም የተነሳ አንዳንድ ታሪኮች ላይ መቆራረጥ እና ቀጣይነት ማጣት ይኖር ነበር። ባጠቃላይ የፅሁፉን ሰዋሰው፣ ስረዓተ ነጥብ፣ የፊደል ግድፈት እና የቃላት ግድፈትን ከማስተካከል ባሻገር ፍሰቱንም ማስተካከል ከባለታሪኮቹ ጋር በነበረን ዉይይት ዉስጥ አስፈላጊ ነበር።

የመጀመሪያው እትም ላይ ግን ብዙ ታሪኮችን ለማጋራት ካለን ፍላጎት እና ሃሳቦችን ለማብዛት ካለን ጉጉት የተነሳ ሁሉንም ታሪኮች በሚባል ደረጃ አስገብተን ነበር። ኋላ ታዲያ አንዳንድ ታሪኮች ላይ ወቀሳም ገጥሞናል። እንዲሁም አንዳንዶቹን ታሪኮች እኛ ከተረዳንበት መንገድ በተለየ መንገድ ሰዎች ሊረዱት እንደሚችሉ አለማሰባችን ሌላው አስተያየት ያመጣ ጉዳይ ሆኖ ነበር። እኛ ያተኮርነው በነበረን ጊዜ ዉስጥ ብዙ ሃሳቦችን መዳሰስ እና ብዙ ታሪኮችን ተደራሽ ማድረግ ላይ ቢሆንም አንዳንድ ታሪኮች የተለያየ ትርጓሜ ሊኖራቸው እንደሚችል አለማሰባችን እና አለማጥራታችንም ሌላው ተግዳሮት ነበር።

በወቅቱ ከታሪኩ ጀርባ ያሉ ሰዎች እንዲሁም እኛም የየራሳችን የሕይወት ትግል ነበረብን። ይህ በቂ ምክንያት ባይሆንም እንኳ እኛም በወቅቱ በጣም በሥራ መጣበባችን የራሱ ተፅዕኖ ቢኖረዉም ሰዎች ደግሞ የሚያዩት ያለቀዉን የመጨረሻዉን ሥራ ነውና ያንን ሥራ በተገቢው መልኩ አፅድቶ ማቅረቡ ላይ ስህተቶች ነበሩ።

ዛክ:- የመጀመሪያው እትም ልዩ የነበረው ከሁሉም አቅጣጫ የመጣውን ፅሁፍ እንዳለ የማቅረብ ዉሳኔያችን ነበር። ካደረግናቸው ዉይይቶች አንዱ የነበረው “ሁሉም ሰው ጥሩ

ፀሐፊ ሊሆን አይችልም። ሁሉም ሰው ግን የራሱ ልዩ ታሪክ አለው” ስለዚህም ይህን ታሪካቸውን ፅፈው ያጋሩት ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍል የተገኙ ሰዎች ናቸው የሚያነቡትም እንደዛው የሚል ነበር ስለዚህ ሀሳባችን የነበረው ሁሉንም ፅሁፍ እንዳለ ማውጣት ነበር። አንዳንዶቹን እንዳለ ምንም ሳንጨምር ሳንቀንስ ያወጣናቸውም ታሪኮች ነበሩ።

እናኒያ:- አዎ ይህን ስላነሳህ ደስ ብሎኛል! በወቅቱ ከተሰጡን አስተያየቶች አንዱ የነበረው emoji ለምን ተጠቀማችሁ የሚል ነበር። እርግጥ ጽሑፍ የራሱ ሕግና ስረዓት አለው። ነገር ግን እኛ ልናስተጋባ የወደድን የነበረው ጸሃፊዎቹ ታሪኩን ሲፅፉ የነበሩበትን ስሜት ሊያስተጋቡ የወደዱት በኢሞጅዉም ጭምር ነዉ ብለን ስላሰብን ኢሞጅውን ሳናወጣ አሳትመን ነበር። በወቅቱ እጅግ ደስ የሚለው ደግሞ ከየአቅጣጫው ብዙ ሰው ታሪኩን አጋርቶን ነበር እና የጽሑፍን ሕግ ባያሟላም እንኳ የጸሓፊውን ስሜት ያስተጋባል ብለን ያሰብነውን ታሪክ እንዳለ አቅርበን ነበር ።

ዛክ:- እውነት ነዉ በጣም ደስ የሚሉ እና ከሁሉም LGBT+ community በሚባል ደረጃ የቀረቡ ብዙ ታሪኮች ነበሩ።

እናኒያ:- እርሱን ስትል እንደዉም ሌላም ነገር እንዳስታውስ ጥሩ ዕድል ስጠኸኝ። ብዙ ግዜ እኛ ሀገር ብቻ ሳይሆን ዓለምም ዙሪያ ላይ ተቃርኖም ይሁን ድጋፍ ብዙ ትኩረት የሚሰጠው የወንድ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሰዎች ጉዳይ ነዉ። ታድያ እኛም በወቅቱ አጋጣሚዉን ተጠቅመን ከ Gay ታሪክ በተጨማሪ ሌሎች ማህበረሰቡን የሚወክሉ ሰዎችንም ታሪክ አሰገብተናል። ሀሳባችንም የነበረው የሁሉንም LGBT+ ሰዎችን ታሪክ ማካተት ነበር። በርግጥ ግን ሁሉም በበቂ ሁኔታ አልተወከለም። ሞክረን ሳይሳካ ቀርቶ እንጂ የጥረት ማነስ ግን አልነበረም።

ዛክ፦ ከዛም ባሻገር ቋንቋንም በተመለከተ የመጀመሪያዉ እና ሁለተኛው እትም ላይ በተለይም የመጀምሪያው ላይ በቋንቋም በታሪክ አይነትም ጥሩ ሰብጥር ነበር። የአምርኛ ፣ አፋን ኦሮሞ ፣ ትግሪኛ እና እንግሊዘኛ ታሪኮች ነበሩ እንዲሁም የገጠርም የከተማም ታሪኮች ነበሩ እና ልዩ ልዩ ታሪኮች ነበሩት። በርግጥ የተለያየ ቋንቋን በማካተት ሂደት ውስጥ ከሁሉም ቋንቋ እኩል ተሳታፊ ባናገኝም ጥሩ ሙከራ ግን አድርገን ነበረ።

ይህንኑ ልምድ ሁለተኛው እና ሶስተኛው እትም ላይ ለመጠቀም ሞክረናል፣ ነገር ግን ሶስተኛው ላይ እኛ ሙከራዉን ባናቋረጥም እንኳ በተለመደው መልክ ሊሄድ አልቻለም። እኛም ለሁሉም ተደራሽ ለመሆን ካለን ፍላጎትም ይመስለኛል ሁሉምንም አይነት ካልገባ ሞቼ እገኛለሁ አይነት ስሜት ተፈጥሮብን ነበር። አንዳንዴ ግን ከሌለ ደግሞ የለም ነዉ። ሁሉንም የማስገባት ግዴታ የለብህም የአንዱ ታሪክ ለብዙ ሰው አስተማሪ ሊሆን ስለሚችል።

ከዛም ባሻገር ብዙ ግዜ ታሪኮችን የምሰበስበው እኔ እንደመሆኔ መጠን በዙሪያዬ ወንድ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ይበዛሉ። ለምሳሌ ፌስቡኬን ብታይ አብዛኛው ሰው ወንድ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ነዉ። እሱም አንዱ ተግዳሮት ይሆናል። ነገር ግን በየትኛዉም እትም LBQ (lesbian, bisexual, and queer) የሆኑ ሰዎችን እንዲሁም በቅርብ የማገኛቸውንም ጭምር ታሪካቸውን ያጋሩ ዘንድ እጠይቃለሁ። በመጀመሪያ ሁሉም ሰው ማጋራት ሚፈልገው ታሪክ ላይኖረው ይችላል፣ ሁለተኛ ደግሞ ሰው በወቅቱ ካለበት ሁኔታ አንፃር እድሉ ቢሰጠውም ወይ ላይመቸው ወይ ላይፈልግ ይችላል። ስለዚህ አንዳንዴ አንዱ እትም ላይ በተለየ የ ጌይ ጉዳይ ቢበዛ አንዱን sexuality ከአንዱ አስበልጦ የማየት ጉዳይ ሳይሆን በወቅቱ የተገኘዉን ማህበረሰቡን ይጠቅማል ብለን ያሰብነውን ታሪክ ማጋራት ስለወደድን ነዉ።

እናኒያ:- በርግጥ አንዳንዴ በሂደት መሰላቸትም ይመጣል። የመጀመሪያው እትም ላይ ሁሉም ሰው ታሪኩን ለማጋራት በወደደው ልክ ሁለተኛ ሶስተኛ እያለ ሲመጣ ስሜቱ እና ፍላጎቱ እኩል ላይሆን ይችላል። አንዳንዴ ፅሁፉ በደንብ ተደራሽ እየሆነ በመጣ ቁጥር ከመላመድ ሚመጣ መሰልቸትም ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ በቃ በዚህኛው ካላደርስኩት በሌላኛው እትም አደርሰዋለሁ እያሉ ለነገ ማሳደርም ሊሆን ይችላል። እነዚህ ነገሮች መፈጠራቸው ግን በየትኛውም ፕሮጀክት ላይ የሚያጋጥም ተፈጥሯዊ ሂደት እንደመሆኑ ምንም መጥፎ ጎን የለዉም። ይሄ cycle ሁሌም የሚኖር ነዉ። መጀምሪያ አከባቢ ያለው ደስታ እና ጉጉት እንደዛው ጣሪያ እንደነካ አይቆይም በጊዜ ሂደት ይወርዳል። አንተም እንደ አዘጋጅ በዚህ ግዜ ነዉ ቆም ብለህ ምን መቀየር እንዲሁም ምን መጨመር እና መቀነስ እንዳለብህ የምትወስነው።

ከዚህም ተነስቼ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በፊት የራሴን ፅሁፎች ኤዲት ከማድረግ ባለፈ እና ትምህርት ቤት ከተማርኩት ባለፈ መፃፍ ኤዲት የማድረግ ሌላ ልምድ የለኝም። በግዜ ሂደት ግን የመጀመሪያ እትም ሁለተኛ እትም እያልን በመጣን ቁጥር የበለጠ ተሻሽዬ ብዙ ነገር ተምሬያለሁ። ይሄም ለውጥ በጊዜ ሂደት የሰራው ጥራት ላይ እየታየ መቷል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም አዲስ የሆነው እትም ምንጊዜም ከበፊቱ በተሻለ መልኩ ጥራት ኖሮት ነበር ይታተም የነበረው። ለምሳሌ ወደ ታሪኮቹም ስንመጣ ከበፊቱ እትም በተሻለ ለብዙ ታሪኮች ዕድል እንሰጣለን በተሻለ ጥራት ማቅረብ ይቻላል ብለን ስለምናምን። በርግጥ ሁሉም ታሪኮች ሊያልፉ አይችሉም አንዳንድ ታሪኮች የራሳቸው ችግር ያለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ ወይ ደግሞ በወቅቱ ከታሰበው ጭብጥ ጋር የማይሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዛክ:- ምናልባት ችግር ያለበት ታሪክ ስንል ግልፅ ለማድረግ ያህል አንዳንዶቹ ታሪኮች ለአቅመ አዳም ካልደረሱ ልጆች ጋር ወሲባዊ ግኑኝነትን ስለ ማድረግ ይሆናሉ። አንዳንዱ ደግሞ ትንሽ ጠንከር ባለ እና አስገድዶ መድፈር በሚመስልም መንገድ የተፃፈ ሊሆን ይችላል፣ እንዲሁም የሌሎችን ሰዎች ክብር በሚነካ እና ስድብ አዘል በሆነ መንገድ የሚጻፉ ታሪኮችም አሉ እና problematic ታሪኮች ስንል እነዚህን ማለታችን ነዉ።

እናኒያ:- እዋ በተሻለ ግልፅ ስላደረከው አመሰግናለሁ። ያው በአብዛኛው ይህን አይነት ፕሮጀክት ሲሰራ የማህበረሰቡን complicated nature የበለጠ ያወጣዋል። የመምረጥ መብቱ ኖሮን ካሰብነው ጭብጥ ጋር የሚሄድ ታሪክ ብንመርጥም ወይም ቅድም ያነሳናቸውን አይነት ችግር ያለባቸውን ታሪክ ብናስወግድም እኛ የመረጥነው ታሪክ ሙሉ በሙሉ ማህበረሰቡን ይወክላል ማለት አይደልም። በጣም ውስብስብ እንደመሆናችን መጠን እኛ ጋር የሚደርሱት ታሪኮችም ሙሉ በሙሉ ማህበርሰቡን ይገልፃሉ ብለን አናምንም። የተመረጡት ደግሞ ተደራሽ ለመሆን ብቁ ሆኑ እንጂ ቅድም እንዳልኩህ ማህበረሰቡን ሙሉ በሙሉ ሚወክሉ ላይሆኑ ይችላሉ።

እርግጥ አንዳንድ ጉዳዮችን መርጠን አይ ይሄ አይመጥንም ብንልም ነገር ግን ልናወራበቸው እና ልንወያይባቸው የሚያስፈልጉ ብዙ ጉዳዮችም እንዳሉ እናምናለን። ከላይ

ላነሳነው አንዳንድ ታሪኮች ላይ አሉ ላልናቸው ችግሮች ቦታ መስጠት እና የበለጠ ተስሚነት እንዲያገኙ ማድረግ ጥሩ አይደለም ብለን ብናምንም ሌሎች ደግሞ ከታሪኩ ይማሩ ዘንድ ለመጽሐፋ ባንመርጣቸውም እንኳን ትክክለኛ ቦታ ላይ ግን በጉዳዩ ዙሪያ ማውራቱ እና መወያየቱ ደግሞ አስፈላጊ ነዉ።

ወደ መጽሃፋ ስንመለስ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስካሁን ባሉት ዉስጥ ብዙ አስደሳችም፣ አሳዛኝም፣ አስተማሪም፣ ወስብስብ የሆኑ ታሪኮች ነበሩት።

ዛክ:- እውነቱን ለመናገር አሁን ላይ መጽሃፎቹን ከፍቼ ሳያቸው እራሱ ከፍተኛ ደስታ ነዉ ሚሰማኝ…. ሳቅ ።

አናኒያ:- ለምሳሌ የሄኖክ ታሪክ ለምን እንደሆነ ባላውቅም በጣም የምወደው ታሪክ ነዉ! ታሪኩ ስለ ፍቅር ግንኙነት አጀማመርና ስላልተጠበቀ ፍጻሜው የሚተርክ እጅግ ብልህነት የተሞላበት ሥራ ነው። አጻጻፉ በጣም ማራኪ ከመሆኑ የተነሳ፣ ገጠመኙን በዝርዝር ከማስረዳት ባለፈ ነገሩን የሚገልጽበት መንገድ እጅግ ረቂቅና ሳቢ ነው። የውስጥ ስሜቱን የሚገልጽበት መንገድ ደግሞ አብራችሁት እንዳላችሁ ያህል እንዲሰማችሁ ያደርጋል። ታሪኩን ሳነብ ‘ይህን ነገር በዚህ መልኩ ለመግለጽ እንዴት ሊታየው ቻለ?’ ብዬ ራሴን የጠየቅኩባቸው ክፍሎች ነበሩ። ለምሳሌ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ብንመለከት:

> “ዝም ያለ እሁድ ከረፋዱ 4 ሰዓት አይነት ፊት ነው ያለው። ጉድ ነው ዛሬ አልኩ በልቤ።”
>
> “የሆነ ግንቦት ወር እሁድ ከሰዓት ነፋስ የሌለበት ቀን አይነት ፊት። ኤጭ።”

እኔም በልቤ ‘ይህ ሰውዬ እሁድን እንዴት ቢወዳት?’ ብዬ ራሴን እስከመጠየቅ ደርሻለሁ (ለሳቅ)።

በተመሳሳይ ጊዜ ግን ታሪኩ ብዙ ስሜቶችን ይዳስሳል first date ያለውን ያንን ፍርሃት እና ደስታ የቀላቀለ ስሜት፣ በቶሎ በፍቅር መውደቅ ጋር የሚመጣውን የስውነት መነቃቃት፣ ቅናት፣ ያለመተማመን ስሜት እና የልብ ስብራትን ሁሉ በጥልቀት ይነካል።

"ቻዋ ብዬው ነው የምሄደው? ልቀፈው? ቁጭ ባለበት ጥዬው ልሂድ? ዛሬ ለመጨረሻ ጊዜ አብረን ነው ማደር ያለብን? እቅፌ ላፅናናው? ራሴን በማይረቡ ጥያቄዎች አጣደፍኩት። አይዞህ ልለው ፈለኩ... እኔን ብሎ አይዞህ ባይ። ድንቄም አይዞህ ባይ እቴ።" ብሎ ይቀጥላል።

ዛክ:- እኔም ከምወዳቸው መሃል አንዱ ነዉ! ታሪኩ የተጻፈበት መንገድ በጣም ጥሩ ነበር። አርትስቲክ የሆኑ አገላለፆች ነበሩትና ሲነበብ አይሰለችቹ አንዳንድ አገላለፆችን ለመጥቀስ ያህል:

"ከፊቱ ላይ ምንም ነገር ማንበብ አይቻልም... ዝም ያለ እሁድ ከረፋዱ 4 ሰዓት አይነት ፊት ነው ያለው። ጉድ ነው ዛሬ አልኩ በልቤ።" ይላል።

ሌላው Queer culture የሚለውን theme በደንብ ነበር የገለፀው። በተለይ ከ dating app ጋር በተገናኘ ሳናስበው የምናደርጋቸውን ነገሮች እሱ ጠቅሷቸው አልፏል። ለምሳሌ መግቢያው አካባቢ እንዲህ ይላል:

"መጀመሪያ የተዋወቅነው በዴቲንግ አፕ ነበር። ፎቶና ስልክ ከተለዋወጥን በኋላ ለትንሽ ጊዜ አውርተን ተጠፋፋን።" ይቀጥልና "በየት በኩል ልታጠፍ ሲለኝ ከህልሜ ባነንኩ። እዚሁ ጣለኝ ብዬ ወረድኩ። ልወርድ ስል እቅቅቅቅፍ ተደራረግን። ጉንጭ አይሉት ከንፈር ብቻ በጉንጭና ከንፈር ድንበር ላይ ተሳሰመን ከመኪናው ወረድኩ። በሩን ስዘጋው ይቅርታ ስምህን አለኝ.... ሁለታችንም ሳቅን ይህን ሁሉ ጊዜ ስም አልተለዋወጥንም ነበር።"

ይህ የሚያሳየን ሁለት ነገር አለ ብዬ አስባለው። አንድ ለ hook up ስንገናኝ ስለራሳችን ብዙ ኢንፎርሜሽኖችን አንለዋወጥም የሚለውን ነው። ሌላው በዜጋው የተለመደው ደግሞ ለመጀመሪያ ግዜ ሰዎችን ስናገኝ ከመደበኛው ስማችን ውጪ ያለውን የዜጋ ስም ወይም የውሸት ስም ነው የምንለዋወጠው እና አንዳንዴ ትንሽ እስክንላመድ ለጥንቃቄ ሲባል ስም እና አድራሻ መቀያየርን avoid የማድረግ ልማዳችንን ያሳያል።

እናኒያ:- ሥሜቶቹን የሚገልጽበትን መንገድ ወደዋለዉ።

ዛክ:- አዋ! በርግጥ ለኔ የመጀመሪያው እትም ላይ ቤት ለምቦሳ ቁጥር አንድ እስከ ሶስት ያለው ቪክቶር ጌታ የፃፈው ታሪክ በጣም በጣም በጣም የምወደው ነዉ!። መዓት ነገር ነዉ ዉስጡ ያለው እያንዳንዱ አንቀፅ የራሱ ትልቅ ሃሳብ ያለውና በራሱ ታሪክ ይወጣዋል ብዬ አምናለሁ። ስለማህበረሰቡ፣ ስለፍቅራችን፣ ስለጓዳኛነታችን፣ ስለፓርቲ፣ ስለመረዳዳት እንዲሁም ስለራሱ የፍቅር ታሪክ ፅፏል እና በደንብ የታጨቀ ብዙ መልዕክት እና ታሪክን ያዘለ ነው። ማህበርሰቡን በደንብ ይገልፃል ብዬ ማስበው ስለሆነ በጣም የምወደው ነዉ።

የቪክተር ጌታ ታሪክ መክፈቻችንም ነበር አንደኛ እትም ላይ።

እናኒያ:- እንደውም ካነሳኸው አይቀር የቪክተር ጌታ ታሪክ ብዙ ነገሮች ነበሩት። አንድ፣ ከራስ ጋር ያለ ግጭትን እንዲሁም ሃይስኩል ዉስጥ ያለ ጥቃትን ተቋቁሞ እራስን ፈልጎ ማግኘትን ይዳስሳል። እንዴት የተለየ እንደነበር እና የተለየ በመሆኑ ደግሞ መልሶ እንዴት ማንነቱን ፈልጎ ለማግኘት እንደረዳው ያሳያል። እንደገናም ደግሞ ስለመነጠል ያወራል ለምሳሌ:

> "እኔ ግን ከምኑም ፆታ ምንም አይነት ጓደኛ ሳይኖረኝ የትምህርት ቤቱ ደረጃ ላይ ብቻዬን ቁጭ ብዬ እሱን ከማድነቅ ውጪ ምንም ማድረግ አልቻልኩም። ወኔው አልነበረኝም።"

የሚል አረፍተ ነገር አለ፣ እዚህ ላይ ስለወደደው ልጅ ቢያወራም እንኳ በተመሳሳይ ግዜ ደግሞ ስለመነጠልና ስለብቸኝነት ያወራል። ከዛ ዝቅ ብሎ ደግሞ ስለ bullying የሚያወራበትም ክፍልም አለ።

> "ልጅ እያለሁ ገና ትምህርት ቤት ሲቀላቅሉኝ የስሜ ቅጥያው ሴቱ ሆነ። እንትና ሴቱ። እንትና ሴታሴቱ። ምንም አድርጌ አልነበረም ግን ከሌሎች ወንድ ህፃናት ለየት ባለ መልኩ መልኬ እና ቁመናዬ ወንድ ቢመስልም በባህሪዬ ግን የሴቶች ብቻ ተብሎ የተፈረጀውን ስላንፀባረኩ ነበር።" ብሎ ይቀጥላል።

ዛክ:- ከዛ ደግሞ የሚቀበሉትን ሰዎች ሲያገኝ ስለነበረው ፍርሃት እንዲህ ሲል ይገልጻል

“ከአመታት በኋላ በአጋጣሚ ዜጎች ስብስብ ብለው የሚገናኙበት ቦታ ሁለት ጥንዶች ቀጥረውኝ ተገኘሁ። ጥንድ ጥንድ ሆነው ሲያምሩ። ስንት ጊዜ አብራችሁ ቆያችሁ? እንዴት ተዋወቃችሁ? ምናምን እያልኩ እየጠየኩ ድክም አረኳቸው። ከዛ ውስጥ ሁለቱ እኔ ከመጣሁበት የቤተሰብ ሃይማኖት ስለነበሩም ደስ አለኝ። በዚህ ሁሉ ደስታ እና ጉጉት መሃል ግን ወባ እናቱ ላይ እንደወጣችበት ሰው ሰውነቴ እየተንቀጠቀጠ ነበር። እግሬ ጠረጴዛውን እንዳይነካ እና ያዘዝነው መጠጥ እና ብርጭቆ ተንገጫግጮ እንዳልዋረድ ስታገል ትዝ ይለኛል።”

ትምህርት ቤት ዉስጥ ሲሰደብበት የነበረው ሴታሴትነት ልክ የራሱን ሰዎች ሲያገኝ ደግሞ ተቃራኒ ሆኖ በደስታ ሚቀላለዱበት ጉዳይ ሆኖ ሲያገኘው ደስ ሲሰኝ እንመለከታለን። ለምሳሌ ጓደኞቹን ሊያገኝ ሲሄድ ከፃፋቸው አንዱ እንዲህ ይላል:

“ብዙ ዜጎች ሲያልፉ ሲያገድሙ ሰላም ሲባባሉ እያየሁ ሃሴት አገኘሁ። በህይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ ስተነፍስ ተሰማኝ። እረፍት። ሰላም ሲባባሉ አክስቶቼ እና ዘመድ ቤት ሲመጣ ጉንጫቸውን እንደሚሳሳሙት ወንዶች ሆነው እምጿ እምጿ ጉንጫቸው ላይ ሲሳሳሙ፣ የተወሰኑት እንደፍላጎታቸው እንዴት ነሽ እንዴት ነሽ ሲባባሉ እና ሲያወሩ እና ሲተራረቡ እያየሁ በቃ ጠፍቶብኝ ስፈልገው የነበረው ቤቴ የገባሁ ያህል ተሰማኝ። ሰላም።

ከቀጥ ጓደኞቼ ጋር ቢራ እና ድራፍት ሰንለጋ አሹቅ እና ዱቤ ሽንብራ የለመድኩ ሰውዬ አሁን ድራፍት እና ቢራ በፍሬንች ፍራይስ እና ካቻፕ እየበላሁ እራሴን አገኘሁት። አንዱ ቀይ እድሜ ከኔ ሚያንስ የደስ ደስ ያለው አጠር ያለ ልጅ መጣ። ሁሉንም ጉንጭ ስሞ እኔ ጋር ሲደርስ “ማነሽ ደግሞ!?” ብሎ እኔም ጉንጬን ተሳምኩ። ግራ መጋባቱም እንደ ወገን ተቆጥሬ ገና በአንድ ቀን እንደ ሁሉም የመታየቴ ደስታም የተለየ ስሜት ፈጠረብኝ። እኔ ስንት አመት ሰደብቃት የኖርኳትን ሴታሴትነቴን ከእርምጃው ጀምሮ ከድምፁ ከአቀማመጡ አገላለፁ

> ይዟት ነው የመጣው። እንደ ልዩ ፍጥረት አፌን ከፍቼ አየዋለሁ። ሰው እራሱን ሲሆን ለካ እንዲህ ያምራል።”
> ይላል

ይቺ አንድ አንቀፅ እንኳን ማትሆን ሁለትና ሶስት አረፍተ ነገር ቀደም ሲል እንድትገለልና ‘መኖር አይገባህም’ እንድትባል ያደረገህ ማንነትህ፣ ዛሬ ‘አንተ ከእኛ አንዱ ነህ’ ተብለህ ለመቀበልህ ምክንያት ሲሆን የሚሰማው ደስታ ልዩና ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። ሙሉ ማንነትን ይዞ በማህበረሰብ ውስጥ መታቀፍ የሚሰጠው እርካታ ወደር የለውም።

እናኒያ:- በተመሳሳይ ግዜ ደግሞ የሚያመጣዉም ግራ መጋባት ደግሞ አለ

ዛክ:- መጀመሪያ ሲሆን በተለይ አዋ

የባለፈዉ እትም ላይም ኤደን ሳሙኤል ስለ coming out የጻፈችው አጭር ጽሁፍ is one of my favorite. ኤክስፒሪያንሷን እንዲህ ነበር ያስቀመጠችዉ

> “ፍቅረኛዬን በተለያየ አጋጣሚ የቅርብ ጓደኛ እያልኩ ማስተዋወቁ ያሳዝናል። ሁሉም ፍቅረኛዬ እያሉ የሚያወሩለት ወንድ አለ… እኔ ያንን ማድረግ ባለመቻሌ ያበሳጨኛ ነበር። የሆነ ቀን መክሊትን አንድ የምነግርሽ ነገር አለ ብዬ ሰሚራ ፍቅረኛዬ እንደሆነች ነገርኳት። “እውቃለሁ ካንቺ ይምጣ ብዬ እንጂ ያላችሁ ግንኙነት ከእኔና ከብሩክ ጋር በምን ይለያል” ብላ ገላገለችኝ። ቀለል አድርጋ መቀበሏ ሲገርመኛ አክብራ፣ ከራሷ ይምጣ ብላ፣ ያየችውንና የጠረጠረችውን ማቆየቷ አይደንቅም?”

ተቀባይነትን፣ መፈቀር እና እንክብካቤ ማግኘት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ይህም በብዙ መንገዶች ይገለጻል። ሆኖም ግን የመገለል ፍርሃቱ እና ጭንቀቱ እውነተኛ ነው።

እናኒያ:- Exactly! አንተ ምታውቀው እና የምትጠብቀው ነገር ሌላ ነዉ። ሰዎቹ ቢቀበሉህም እንኳ እንዲሁም እራሳቸውን መሆናቹውም ጭምር ፍራቻ ዉስጥ ይከትሃል ልክ አይደለም ብለህ እንድታስብም ሊያደርግህ ይችላል።

ዛክ:- አዎ ልክ ነዉ አንተ ስታድግ ሴታሰትነት ሚወደድ ነገር አይደለም ተብለህ ነዉ ያደከው እና አሁን ደግሞ በሴታሴትነቱ የማያፍር እና አንተንም ሙሉ በሙሉ በኩራት ሚቀበልህ ሰው ስታገኝ አይ ይህ ነገር ልክ አይደለም ብለህ እንድታስብ ያደርግሃል። ደስታ ሊሰማህ ሲገባህ አንተ ዘመንህን ያሳለፍከው ደግሞ በመቆጠብ እና በመደበቅ ስለሆነ እሱን ልምድህን መተው ይከብድሃል።

እናኒያ:- በትክክል! አንድ “Gay men and insult” የሚል መፃፍ ላይ ያነበብኩት ታሪክ ትዝ አለኝ፣ ሌላ ፅሁፍ ላይም የተጠቀምኩበት ይመስለኛል። ምን ይላል መሰለህ ጌይ መሆንን ማህበረሰቡ ሲያስተምርህ እንደ ስድብ እና ፀያፍ ነገር አድርጎ ነዉ። ታዲያ አንተም ስታድግ አእምሮህ ጌይ መሆንን እነሱ እንደነገሩት አድርጎ ነዉ ሚቀበለው። በርግጥ እንደግለሰብ ሁሉም ለየት ያለ እንደሆነ ቢያውቅም እንዲሁም ስሜቱን ቢረዳም ለዛ ማንነትህ የሰጡትን ስያሜ “ቡሽቲ” በሚል ወይም “ሴታሴት” በሚል ሴትም ከሆነች ደግሞ “ወንዳወንድ” “እንደሴት አትሆኚም” የሚሉ ስድቦችን ነዉ። በርግጥ ከጊዜ በኋላ የራሳችን አረዳድ እየኖረን የሚመጣ ቢሆንም ግን ደግሞ ማንነታችን እንደመልካም ነገር እና የኩራት ምንጭ አርገው በሚረዱ ሰዎች እና ጓደኞች አከባቢ መሆን ደግሞ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። እና እንዳልከው የቪክተር ጌታ ታሪክ በአንድ ነጠላ አንቀፅ ወይም ታሪክ ብዙ ቦታዎችን የሚዳስስ ደስ የሚል ታሪክ ነዉ። ከዛ ባሻገር ድንቅ የሆነ የታሪክ አፃፃፍ እና እንደምሳሌ ምትጠቀምበትም ጭምር ነዉ። እያንዳዱ ክፍል የሚዳስሰው ነገር የተለያየ ሆኖ እንኳን ፍሰቱን እና ቀጣይነቱን ግን አይሰትም የት ጋር ጀምሮ የት ጋር ማቆም እንዳለበት በደንብ የሚያቅ ጥሩ ተደርጎ የተፃፈ ታሪክ ነበር።

በርግጥ አንዳንድ ታሪኮችን ቀደም ብለህ ስታውቃቸውም ለመረዳት ቀላል ሚሆኑ ይመስለኛል።

ዛክ:- ሰዎቹን ስለምናውቃቸውም ይመስለኛል፣ ለምሳሌ እኔ ከሶስተኛው እትም ጁጁ ስለጓደኝነት የፃፈው ታሪክ ደግሞ በጣም የምወደው ታሪክ ነዉ። ምክንያቱን አብዛኞቹን በታሪኩ ዉስጥ ሚጠቀሱ ሰዎችን እና ሁኔታዎችን መገመት ስለምችል እና ስለሚገባኝ ይመስለኛል።

አናኒያ:- Yeah 100%! እኔ ስለማውቀው I can connect the dots ፈገግታ። ለምሳሌ ቪክቶር የሆነ ቦታ የሚያወራው ፓርቲ እና ሌላ ታሪክ ላይ ደግሞ ሌላ ሰው ስለ ላባ ግሩፕ የሚያወራው የተያያዘ ታሪክ ነዉ። እኔ ላባ ግሩፕ ምን እንደሆነ ስለማውቅ ነጥቦቹን አገናኝና እረዳለሁ። ከዛም ባሻገር ደግሞ እንደማህበረሰብ ታሪኮቻችንም የሆነ ቦታ ላይ ሊገናኙ ይችላሉ። ለምሳሌ ላባን ብዙ ሰው በታሪኩ ዉስጥ እንስቶታል እና ይሄ ሚያሳይህ ከታሪኩ መገናኘት ባሻገር ባለ ታሪኮቹም በሆነ አጋጣሚ የሆነ ቦታ ተገናኝተው ሊሆን እንደሚችል ነዉ። ለዚህ ሌላ ማሳያ የሚሆነዉ ደግሞ እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችን እንገናኝበት እና ጊዜ እናሳልፍበት የነበረው የዮሐንስ ቤትን የሚያስታውሱ ታሪኮችም ተጽፈዋል።

እንባቢያን ከታሪኮቹ ጋር ጥልቅ ቁርኝት ሊኖራቸው፣ አልፎ ተርፎም ባለታሪኮቹን በአጋጣሚ ሊያውቋቸው ይችላሉ። ለምሳሌ አንዱ የኦሮምኛ ታሪክ፣ በፌስቡክ ስለነበረ ጓደኝነት እና ግንኙነት በዝርዝር ያወራል።

ዛክ:- አዎ እሱን ታሪክ ሳነበው ለኔም እሁን ያልከው ስሜት ነበረው እሱ እዛ ታሪክ ላይ ሚጠቅሳቸው አብዛኞቹ ሰዎች ለኔም ጓደኛ እና ብዙ ያስተማሩኝ ሰዎች ናቸው እና ታሪኩን ሳነበው ከኔ ልምድም ጋር አመሳሰዬ ነበር።

ይህ ጽሁፍ የወጣዉ ሁለተኛው እትም ላይ ነበር። Bona Nado ታሪኩን በአራት ክፈረሎች ከፋፍሎ በአፋን ኦሮሞ ፅፎልን ነበር። የታሪኩን ተደራሽነት ለማስፋት እኛም ወደ አማርኛ ተርጉመን ሁለቱንም አካተን ነበር ያወጣነው። እዚህ ጽሑፍ ምዕራፍ ሦስት ላይ አብዛኞቻችን የምናውቃቸውን እና አክቲቭዝምን Facebook ላይ ያስጀመሩትን ሰዎች እንዲህ ሲል ይጠቅሳል:

> “Haasaafi maree daqiiqaa torbaatamaa booda “Guardian angel” akkas naan jedhe. “Amma bar’uu gaariirratti kufteetta. Bilbila kana akka cufteen Facebook odeeffannoo kee dhugaa hin qabne tokko bani. Maqaankoo “abalu” jedhama. Eega

> bantee booda sakatta'ii na hiriyoomfadhu. Itti aansuun kuusaa hiriyootakoo seeniitii namoota "Victor Geta, Happy Addis, Robel, Tegbabi Wetat, Boche Doche Bino, Nathy Nati, Selemo Fikre, Kamal Fitsum... Jedhaman hiriyoomfadhu..." bilbila cufe."

ቦኒቸ ቦና ይህን ጽሑፍ እንዲህ ተርጉሞታል

> "ከሰባ ደቂቃ ወሬና ውይይት በኋላ "ጠባቂ መልኣኬ" እንዲህ አለኝ " አሁን ጥሩ መዳፍ ላይ ወድቀሃል። ይህን ስልክ እንደዘጋህ አንድ ሰላንተ ትክክለኛ መረጃ የማይገልጽ የውሸት ፌስቡክ አካውንት ክፈት። ስሜ እገሌ ይባላል። ከከፈትክ በኋላ ፈልገህ ጓደኛ አድርገኝ፤፤ በመቀጠልም ከጓደኞቼ ዝርዝር ውስጥ ግባና Victor Geta, Happy Addis, Robel Hailu, Tegbabi Wetat, Boche Doche Bino, Nathy Nathy, Solomon Fiker, Kamal Fitsum..... የሚባሉ ሰዎችን ፈልገህ ጓደኛህ አድርግ… ስልኩ ተዘጋ።"

በዋናነት የሚተርከው፣ አንድ በአጋጣሚ ያገኘው ሰው የዉሸት የፌስቡክ አካውንት እንዲከፍት እንዴት እንደመከረውና ይህም አዲስ ዓለም እንደከፈተለት እና ይህም ራሱን ይበልጥ እንዲረዳ ብቻ ሳይሆን የማኅበረሰብ አካል እንደሆነ እንዲሰማውም እንደረዳዉ ነዉ።

እናኒያ:- የሁላችንም ገጠመኝ ይመስለኛል እሱ!

ዛክ:- እዋ ልክ ነዉ።

እናኒያ:- በያንዳንዱ እትም ላይ ጭብጡ ቢለያይም እንኳን ታሪኮቹ ብዙ ጊዜ ዞረው ሲገናኙ ታያለህ። እርግጥ ነዉ ለያንዳንዱ እትም እኛ ሰራዉን ለመስራት ምቹ ይሆን ዘንድ የተለያየ ጭብጥ እንሰጣለን።

ዛክ:- እሱን ስናደርግ ያልተነሱ ታሪኮችም ይነሱ ዘንድ ታሳቢ አድርገን ነዉ።

አናኒያ:- አዎ እሱም ሌላኛው ዋናው ጉዳይ ነዉ፣ ሆኖም ግን ቅድም እንዳልኩት ታሪኮቹ ዞረው ሲገናኙ እና አንዳንድ ቦታ ስለተመሳሳይ ቦታ እያወሩ ሁለቱም የየራሳቸውን የተለያየ ልምድ ሲያጋሩም ታያለህ። እንደገናም ባንተ ሕይወት ዉስጥ ተፅዕኖ የነበረው ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ ሰው ላይም ያንኑ ተፅኖ ሲያሳድር ልታገኝ ትችላለህ።

ለምሳሌ እኔን ብትወስደኝ አንዳንድ ታሪኮች በተፃፉ ጊዜ ሳይሆን በጊዜው ሲሆኑ በቅርብ የነበርኩኝ ሰው ስለነበርኩ ታሪኮቹን ሳነብ እዛ ቦታ ላይ ተመልሼ ደግሜ የመገኘት ያህል ስሜት አለው። ስራዬም ሪሰርች እንደመሆኑ እና የምሰራበትም ጉዳይ LGBTQ+ internet culture and identity የተመለከተ እንደመሆኑ ሲከሰቱ የነበሩትን ታሪኮች እንደገና ወደኋላ ተመልሶ የመቃኘት ያህል ስሜት ይሰማኛል።

ዛክ:- ለምሳሌ የጁጁን ታሪክን ሳነብ፣ የቦናን ታሪክ ሳነብ በጣም እንደዛ አይነት ስሜት ዉስጥ እንድገባና ሰዎችን እንዳስታዉስ ወደኋላ ተመልሼ ደግሞ ትናንትን እንድቃኝ ሆኛለሁ።

አናኒያ:- አዎ ደስ የሚለው ነገር ምንድነው እነዚህ በወቅቱ ተፅኖ ሲፈጥሩ የነበሩ ወጣቶች በአንድም በሌላም መንገድ ስማቸው እዚህ መፃፍ ዉስጥ ሊጠቃለል እና ሊጠራ ችሏል። ታሪኮቹን ባነበብክ ቁጥር ደግሞ በብዙ ሰዎች ህይወት ላይ መልካም ተፅዕኖ ያሳደሩ ሰዎች እንደሆኑ ትረዳለህ።

እኛም እነዚህን ብዙ ሰው የጠቀሳቸውን ሰዎች ዕድል አግኝተን በተለያየ መንገድ ሁሉንም ባይሆን እንኳ ከአብዛኞቹ ጋር ልንገናኝ ችለን በዚህም ሆነ በቀደሙት እትሞች ልናካትታቸው ችለናል። ሰዎች ስለነሱ ካነሱት መልካም ጉዳዮች በተጨማሪ ደግሞ እራሳቸው ታሪካቸውን ማጋራት መቻላቸው ለአንባቢውም ለኛ ለአዘጋጆቹም እንዲሁም ለባለታሪኮችም ደስ የሚል ነገር ነዉ። እንዲሁም ደግሞ ይህም መፃፍ አንድ አማራጭ ሆኖ ዛሬም ድረስ ደግሞ እነሱ ልምዳቸውን ማካፈል መቻላቸው እና ለሰዎች መማሪያ መሆን መቻላቸው ሌላው በጣም ደስ የሚል ነገር ነዉ።

ዛክ:- ሌላ መጨመር የምፈልገው ነገር፣ በኦንላይንም ሆነ በአፍላይን ኢትዮጵያ ዉስጥ queer movement አለ ብለን ካሰብን

ያንን እንቅስቃሴ ከመሰረቱት ዉስጥ ሁሉንም ማካተት ባችል እንኳን አብዛኞቹን በነዚህ እትሞች ዉስጥ አካተናል። ስማቸውን በመጥቅስ እንዲሁም ታሪካቸውን በማጋራት ወይ ደግሞ በአሁኑ እትም እንዳደረግነው ቃለመጠይቅ በማድረግም ጭምር ታሪካቸውን ለመዳሰስ እና ለማጋራት ጥረት አድርገናል። በርግጥ “ኖርም” ወደፊት የእንቅስቃሴው አካል ነዉ የሚሆነው ነገር ግን ከ”ኖር” በፊት ደግሞ ብዙ ሰዎች አሉና አብዛኞቹን አካተናል ብዬ አስባለሁ።

እናኒያ:- በርግጥ ሁላችንም በተመሳሳይ ቦታ እና ሁኔታ ስለምንገኝ ቃል በቃል አሰበንበት ያደረግነው ነግር ባይሆን እንኳ ደግሞ ታሪካችን በራሱ የሚቆራኝ እንደመሆኑ የነሱ ታሪክ የምተወው አልነበረም እና ግዴታ ማካተትም ነበረብን።


ዛክ፦ ይህን ውይይት የሆነ ቦታ መቋጨት እንዳለብን ረሳነው መሰለኝ?

እናኒያ፦ መቋጨት አለብን አይደል? የአራት ዓመት ትውስታን በአንድ ሰዓት ውይይት መዳሰስ ቀላል አይደለም።

ዛክ፦ እሱ እውነት ነው ግን ማጠቃለል አለብን። በመጨረሻ ማለት የምንፈልገውን ነገር ብለን ብንቋጨውስ ?

እናኒያ:- እውነቱን ለመናገር፣ ምንም የምጨምረዉ ነገር የለም። ብዙ ነገሮችን የነካካን ቢመስለኝም ግን ደግሞ ገና ያልተባሉ ብዙ ነገሮች ያሉ ይመስለኛል። ምክንያቱም በጣም ብዙና የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያነሱ ጥልቅ ታሪኮች አሉን። I feel like we can talk about this forever so ቀሪውን ግን እንባቢያን ወደ ኋላ ተመልሰው ያለፉትን ጥራዞችና የዚህን እትም ታሪኮች እንዲያነቡ ብንተወው ይሻላል።

ዛክ፦ ልክ ነህ! ሪከርድ ማድረጉን እዚህ ጋር እናብቃና እኛ ወሬያችንን እንቀጥል።



# N’or: Design Process

**What is the creative process for designing the book?**

So first, it's about getting the main idea down, right? Like, figuring out what we're actually trying to deliver. Once we nail that core story, we need to make sure it connects with the audience.

It's all about balancing the story and the people reading it, who have their own backgrounds, vibes, and everything. The design has to line up with that and get the message across. Design is basically talking, so we want everyone to feel like they're part of the story, that they can see themselves in it and know they're not alone. It should build a sense of community and connection.

Since culture reflects groups of people, we wanted to highlight the local Ethiopian audience. That's why it was given that Ethiopic feel, but with a modern twist, blending the old with the new. We want it to bring back some good memories, too, like when you look at the illustrations, the textures should give you that sense of nostalgia.

**What was the Inspiration for the cover? And how do you think the design contributes to the book beyond just aesthetics?**

The cover is all about showing off how diverse the community is, especially the Ethiopian community, which fits the book's title perfectly! It has a cool, vintage vibe, think old-school textures and colors, but it's also packed with cultural details like rich textures and awesome character art. We really focused on making sure you see all the different ways people express themselves, their varied cultural backgrounds, and how they choose to look (from traditional headwear and clothes to modern styles and diverse hairstyles). It's diverse, but it all comes together beautifully.

Honestly, though "Don't judge a book by its cover" is totally overrated, and often used as a discouragement on the effort needed. It's not just about how it looks, but how it's presented. People are imaginative, so you need to guide the audience. Whether they agree with the design or not, it should definitely hint at the overall message of the story. The core idea is there; it's being told to the reader. So, a good design can be engaging. It can give a sense of recognition, something to remember, and a way for people to find themselves in the stories (and a little bit in the design). It's all about achieving that visual connection and understanding between the reader and the author or the way the stories are presented.

**What is the reasoning behind the color choices and illustrations?**

The illustration and colors were chosen to set the right vibe and communicate the book's themes, especially for folks reading it on a screen.

Color is the main tool for setting the mood and framing the whole look and message. Even though the colors are bright, the use of textures keeps them from feeling too wild. Since it's an ebook, the textures also give a cool, nostalgic feel, like an old physical book. Yellow is there for brightness, representing joy and the good stuff in the stories. Green anchors the picture, symbolizing nature and organic things, which mirrors the storytellers themselves. The dark, rich tones for the clothing keep the theme consistent and blend nicely with the characters' dark skin tones.

The different headwear, decors and fabrics show off diversity and personal style. The characters' body language is drawn in a way that doesn't box them in or define them too strictly. This was a conscious choice to make everyone

feel included, so no one feels like an outsider. It's one of the ways to create a sense of togetherness. The poses are meant to look relaxed, letting readers connect with the shared, abstract emotions across all three volumes.

**What are you trying to convey through the design elements? For example, with the use of the Berchuma?**

The design communicates a message of welcome, existence, love, joy, and belonging, centered on the name "Nor" and the "Berchuma" stool.

"Nor," a shortened Amharic word for "We live, We exist," is a welcoming term. Traditional responses vary: Christian is "BEgzer" ("With God"), and Non-Christian is "Belijochachin" ("With our children"). This establishes themes of *existence and welcome*. Rooted in queer culture, the concept emphasizes *deep connections in non-traditional family structures* ("child mother love"), advocating for belonging, loving, and caring.

The "Berchuma," an ancient Ethiopian wooden stool, physically embodies this welcome. Its design, three curved legs for balance and a circular seat, *signifies universal comfort and welcome, regardless of one's shape or form,* and however the seat is spun. The Berchuma also symbolizes a saved seat, what we call the *"10th" Concept of Inclusion*, connecting to the queer culture concept of "scoring 10s." The design features nine people and intentionally includes the reader as the tenth, completing the perfect "10" and reinforcing complete inclusion and belonging.

In terms of the round forms and circle symbolisms and application, the circle embodies qualities such as evenness, wholeness, smoothness, comfort, and a sense of ceremony and celebration. This symbolism is present

in various forms, including the *Berchuma* and *Rekebot* ("A Coffee Platter") ceremonial gatherings. It is utilized to bring people together, such as in a celebratory "group hug" as a farewell gesture, and as a dynamic invitation to gather in a circle that *signifies completeness, fulfillment, and joy*.

### How does the design language carry over from one version to another

The core message of each volume is conveyed not just through the characters themselves, but through the fundamental core conceptual idea of each volume. The first volume introduces a welcoming, open, and humble theme of queer joy, shared through various honorable adventures. The second volume centers on a theme of comfort within a gathered group, emphasizing the wholesomeness of friendship, reliance, and solace. The third volume culminates in a gesture of triumphant celebration and diverse, esteemed joy, reflecting and building upon the themes established in the preceding volumes.

### Beyond the cover, what other elements are included?

When designing, the focus wasn't just only on the character elements, but also used texture. To keep that nostalgic feel and make it easy to read, we went with a light paper texture combined with a serif font.

We also added illustrations. Initially, for the first edition, these were more individual sketches and drawings that tried to express the stories. Later, we shifted to a collective reflection to depict the stories thematically. For the third approach, we used the overall character of the covers throughout the volume to reflect the journey and how the stories might connect.


Now, about the typography for the book title “Nor”: we used Amharic lettering. It has these detailed lines with smooth edges and curves. This is meant to show the diversity. of paths, stories, and quality, all coming together, while keeping a mix of modern and retro that spans the past and present.

**What are some of the challenges, if any, in designing an ebook like N’or?**

Merging concepts and presenting them visually can be an ambitious and challenging endeavor, often making it difficult to maintain aesthetic and messaging continuity. Consequently, first round executions may not be as smooth as initially intended.

Another aspect that presents a challenge, yet is simultaneously rewarding, is maintaining continuity. This process offers a valuable opportunity for learning and exploring the best possibilities. The goal is to achieve a diverse range of expression while ensuring it remains aligned with the overall sense of unity, continuity, and coherence.

Ultimately, this entire experience was a significant learning opportunity to explore the combined abilities and to determine the best possible outcome, all while sustaining the initial creative energy across all volumes.



# Afterword

Queer people know how to tell a story!

Storytelling is one of our oldest forms of survival. It is how we preserve memories, pass on life-saving knowledge, and capture the richness of our lives. We have always known how to turn even our most painful experiences into something beautiful or funny. Our oral histories are rich, but they remain unwritten. This means some of the most important moments from our communities risk being forgotten or erased. Too often, our stories are told by others, stripped of their complexity, flattened into stereotypes that fail to capture our interior worlds.

N'or emerged in response to this. Originally envisioned as a four-part e-book series, the project was born out of a shared desire to create a written record that tells our stories on our own terms and in our languages. This volume, the fourth, stands as both a conclusion and a continuum, closing the circle while at the same time looking toward what may come next. This is why we chose reflection as the guiding concept for this edition. Reflection: as conversation, an exchange; a resonance, like sound or light bouncing off a surface. As mirror, a look back at who we are and how we show up in the world.

When we began working on this edition, we knew we wanted to depart from the essay and personal story format that had defined past issues. Instead, we turned to conversations, interviews and dialogues as modes of engagement. We wanted the team behind the project and our past contributors to be in conversation with the work itself, to revisit and re-examine what N'or has meant since its first publication in 2022.

Through reflection, we revisit the three central themes of our earlier volumes. The aim is not to rewrite but to ask new questions. What angles had we not yet seen? What

new readings emerge through this engagement? What, in this attempt at meaning-making, feels complete, and what remains open, unfinished, or unresolved? Because N'or has never been a collection of isolated stories. It is a body of work, interconnected across its multiple iterations.

N'or has always been an invitation.

It's the first thing you hear when entering a home: a word of welcome and a small but profound gesture of respect and care. In the first edition, we opened with the berchuma, inviting the reader to come sit with us as we processed what mattered to our community. We wanted to create a place where people release and share, where honesty, even when painful, could become healing. In the second edition, we gathered around coffee, sitting together to unpack what queer Ethiopian culture might mean. Does such a thing exist? What does it look like? How do those ideas of culture and identity collide or transform in each other's company? By the third issue, we found ourselves grounded in relationships, those intimate, everyday interactions that weave the fabric of our community. Romantic ties, friendships, and relationships forged through acts of mutual care.

And now, in this fourth edition, we come together once more, this time to sit in a circle and reflect. To look at what has come before us and to ask: When is it time to look back? How soon is too soon, and how long is long enough to see things anew? What glimpses of the future can we catch in doing so? What opens up if we see looking back as a return?

Reflection, at its core, is internal work. It cannot be demanded of others without first being practiced by oneself. By reflecting on the process of working on this

book, the team behind N'or invites the reader into the back of house, the space where the ideas take shape and the work that quietly unfolds. The process begins with collection, either through an open call or direct outreach. What follows is a period of engagement with writers, editors, and translators, through direct and multiple rounds of feedback. Editing, for N'or, has never been about correction but rather giving structure to ideas and deciding what must remain raw and what calls for refinement.

The design process extends this process visually, translating tone and feeling of the stories into the cover and layout. Each design choice, from the typography and illustrations to the texture of the pages, is deliberate. The visual language is meant to be familiar and draws inspiration from the aesthetics of old Amharic books. In doing so, it honours a lineage of print culture while situating N'or firmly within a contemporary digital context. The covers, in particular, shapeshift and adapt to the themes of the issue as part of a continued effort to capture our complexities, an attempt at world-building.

This edition unfolds mostly through interviews, returning to the themes grounding N'or since its inception: community, culture, and queer kinship. Conversations with figures who have shaped online queer culture are interspersed with reflective pieces from past contributors and editorial notes from the team. This creates a layered conversation between past and present, between the digital and the embodied.

To complete something is to honour its cycle. Each edition marks a phase in that motion: a gathering, a grounding, a release. To reflect, then, is not to close the work but to let it expand, to make space for change and transformation.

Perhaps conclusion isn't an ending at all. Maybe it's an opening...for yet another invitation.

N'or!

*With all my love,*

*Anania T*

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድመን፣ ፍርሃትን አሸንፋችሁ ታሪካችሁን ላካፈላችሁን እና የዚህ ታላቅ ሰነድ ዋና ባለቤቶች ለሆናችሁ ሁሉ የላቀ አክብሮት አለን። ለዚህኛው እትም ጥሪያችንን አክብራችሁ፣ ልባችሁን ከፍታችሁ ለውይይት ከእኛ ጋር የተቀመጣችሁ እንግዶቻችን፤ ድፍረታችሁ ለብዙዎች ብርሃን ነውና እናመሰግናለን።

በተጨማሪም፣ ሥራችንን በማንበብ፣ ገንቢ አስተያየታችሁን በመለገስ እና በዚህ ጉዞ ላይ አብራችሁን በመቆም ለምትበረታቱን የቅርብ ደጋፊዎቻችን በሙሉ—እናንተ የጉዟችን የጀርባ አጥንቶች ናችሁ።

ያለ እናንተ ያልተገደበ ድጋፍ እና ተሳትፎ ይህ ጉዞ እዚህ አይደርስም ነበር። ቃላት ከሚገልጹት በላይ ከልብ እናመሰግናለን!

“አጠገቤ የነበሩ ጓደኞቼን ማጣታቸው ሁሉ መስሎኝ ነበር። ሁኔታው ጎድቷቸዉም ነበር። አሜሪካ ላይ ስለኖርን አውሮፓ ላይ ስለኖርን ምዕራቡ ዓለም ላይ ስለኖርክ ሰዎች ምንም የማይሆኑ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን የሆነ ሰው ፓወርህን ሲነጥቅህ you feel like shit! ከራስህ ፍቃድ ዉጪ ብዙ ነገሮች ይሆኑብሃል እና ያንን ሳየው ደግሞ ቲክቶክን እፈራው ነበር።”

ሮቤል ሃይሉ /ከመጽሀፉ የተወሰደ/

“መጀመሪያ ለመተዋወቅ መድረክን ፈጠርን ከዛ መተማመን ሲፈጠር በአካል መገናኘት ይመጣል። ሰውን ለማግኘት ቀላል መድረክ ያደረገው እሱ ነበር። ድንገት ወተህ ትምህርት ቤት ሄደህ ወይም ኳስ ስታይ ወይም እድር ውስጥ ሰፈር ውስጥ ሄደህ ሰውን የምትገናኝበት ነገር አልበረም። ሁሉም ጥጉን ይዞ ተደብቆ ነው ያለው ወይ ግንባሩ ላይ “እከሌ ዜጋ ነው” የሚል አይተህ ሄደህ የምትተዋወቀው ነገር አልነበረም። ስለዚህ ኦንላይን በጣም ወሳኝ ነበር።”

ሃፒ አዲስ /ከመጽሀፉ የተወሰደ/

“የሚደግፍህ ምንም ነገር የለም። አብዛኛውን ሥራ የምትሰራው ራስህ ነህ። ሁልግዜ ብዙ ትግል አለ። አንተ ብትዘናጋ ተው ብሎ የሚመክርህ ምናልባት ዜጋ ጓደኞች አጠገብህ ካሉ እንጂ ምንም ነገር የለም። የሚመራህ የሚያማክርህ ሰው በዙሪያህ ብዙ የለም። ከቀጥም ሰው ጋር እንዳታወራ እዚ relationship ውስጥ እንደሆንክም አይታወቅም relationship አለህ እንዴ ልትባል ሁሉ ትችላለህ ነገሮችን በተለያየ perspective ማየት አትችልም ሙሉ ለሙሉ የራስህ ጥረት ነው።”

ጀይ /ከመጽሀፉ የተወሰደ/



N’or © 2026
Published by YEDI/የዲ
Addis Ababa, Ethiopia